አዕማድ መጻሕፍት

ቁጥር 30

ትንሣኤ ክርስቶስ

በቃል ኪዳን ዘለዓለም



ከብርሃነ ሕይወት መጻሕፍት

አዲስ አበባ

2004 ዓ.ም.

ማስታወሻ

በ"አዕማድ መጻሕፍት" ውስጥ የሚገኙት ጥቅሶች በ1954 ዓ.ም. በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ ታርሞ ከታተመው መጽሐፍ ቅዱስ፣ በ1980 ዓ.ም. በቀላል አማርኛ ከተዘጋጀው ትርጉምና በ1993 ዓ.ም. ከታተመው አዲሱ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም (አ.መ.ት.) የተጠቀሱ ሲሆን፣ ዐልፎ ዐልፎ የፊደል ወይም የሥርዐተ ነጥብ ዕርማት ተደርጓል።

በቀድሞው ትርጉም ለሚጠቀሙ አንባብያን በተለይ ከመዝሙረ ዳዊት ሲጠቀስ፣ አብዛኛውን ጊዜ በቅንፍ ውስጥ ያለውን ቍጥር የሚያመለክት መሆኑን ማሳሰብ እንፈልጋለን።

"አዕማድ መጻሕፍት" በተባለው ጠቅላላ ስም የክርስትናን ሃይማኖት የሚገልጡ አርባ ስምንት ተከታታይ መጻሕፍትን ለማሳተም ታቅዷል። እንደ አዕማድ ሁሉ ክርስቲያን በሃይማኖቱ እንዲጸና ሊደግፉት የሚችሉ እነዚህ መጻሕፍት በአራት ክፍሎች ይከፈላሉ:-

1. የብሉይ ኪዳን ታሪክና ፍች

2. የሐዲስ ኪዳን ታሪክና ፍች

3. የክርስቲያን ሃይማኖት ትምህርት

4. የክርስቲያን ኑሮ ትምህርት

"አዕማድ መጻሕፍት" መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ እውነተኛውን የክርስትና ትምህርት ያስተምራሉ እንጂ ወደ አንድ ክፍለ ሃይማኖት የሚያደሉ አይደሉም።

አንባቢው ከዚህ መጽሐፍ ያገኘውን ቁም ነገር ተከታታዮቹን መጻሕፍት አንብቦ በማገናዘብ እንደሚጠቀምበት ተስፋ እናደርጋለን።

የሽፋን ሥዕልና የንድፍ ቅጂ በወንድወሰን ገ/ትንሣኤ።

ማውጫ

ምዕራፍ አርእስት

ገጽ

መቅድም

ምዕራፍ 1 ትንሣኤ ክርስቶስን እንዴት እንመለከተዋለን? 6

ምዕራፍ 2 ስለ ትንሣኤ ክርስቶስ የተነገረው ትንቢት 11

ምዕራፍ 3 የክርስቶስን መሞትና መቀበር በዐይን ያዩ ምስክሮች 25

ምዕራፍ 4 የትንሣኤ ክርስቶስን እውነተኛነት የሚያረጋግጡ ሕያዋን ማስረጃዎች 42

ምዕራፍ 5 ከሙታን ከተነሣው ከጌታችን ኢየሱስ ጋር የተገናኙ የዐይን ምስክሮች 67

ምዕራፍ 6 የትንሣኤ ክርስቶስን ትክክለኛነት የሚያረጋግጡ ተጨማሪ ምስክሮች 97

ምዕራፍ 7 የትንሣኤ ክርስቶስ ማእከልነት 111

ምዕራፍ 8 ትንሣኤ ክርስቶስ ሁሉን ይለውጣል! 131

ምዕራፍ 9 ትንሣኤ ክርስቶስ የተስፋችን ዋስትና ነው 147

ምዕራፍ 10 "እንግዲህ ሂዱና..." 173

ጥያቄዎች 186

መቅድም

ብዙዎቻችን በትንሣኤ ክርስቶስ የምናምነው ሳናስብ እንዲሁ ዝም ብለን ነው፤ ይሁን እንጂ የክርስቲያን እምነት መሠረታዊ እውነት፣ የአራት ወንጌሎች ቁንጮ ሐሳብ፣ የሐዋርያት ስብከት ማእከልም እርሱ ነው፤ ትንሣኤ ክርስቶስ በክርስቲያን የሃይማኖት መግለጫዎች ሁሉ ተገልጾ ይገኛል። ትንሣኤ ክርስቶስ ከሌለ ክርስቲያንነት የለም።

ትንሣኤ ክርስቶስ ለሐዋርያት ሕያው የሆነ ክሥተት ነበረ፤ እነርሱ ከሙታን ከተነሣው ኢየሱስ ጋር በአካል ተገናኝተዋልና፤ "ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን፣ በዐይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም፣ እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን" ብሎአል ሐዋርያው ዮሐንስ፤ 1ዮሐ. 1፥1። የዐዲስ ኪዳን ጸሓፊዎች የዐይን ምስክሮች በመሆን ያዩትንና የሰሙትን ወይም ከዐይን ምስክሮች የተሰጠውን መግለጫ በመስማት፣ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጽፈዋል።

የትንሣኤው ጊዜ ገና ቅርብ ጊዜ ስለ ነበረ፣ ከትንሣኤው ጋር የሚዛመዱ ቦታዎች የሚታወቁ ስለ ሆኑ፣ የዐዲስ ኪዳን ጸሓፊዎች ስለ ድርጊቶች ቅደም ተከተል፣ የዐይን ምስክሮቹም በየጊዜው በትክክል ወዴት እንደ ሄዱ ለማመልከት ብዙ አልተጨነቁም። ስለዚህ አቀራረባቸው ከዘመናዊ የታሪክ ጸሓፊዎች አቀራረብ ይለያል፤ ቢሆንም አጻጻፋቸው ያልተወሳሰበና ከወቅቱ ሁኔታ የተነሣ ድንገት ከራሳቸው የፈለቀ ሐሳብን የሚገልጽ በመሆኑ፣ ያቀረቡአቸው ማስረጃዎች በይበልጥ የሚያሳምኑ ናቸው።

እንግዲህ ከዚህ መጽሐፍ የጌታችንን ትንሣኤ ልብ አድርጋችሁ እንድትመለከቱ፣ ስለ ትንሣኤውም የተሰጡትን ማስረጃዎች በጥንቃቄ እንድትመረምሩ አንባብያንን እንጋብዛችኋለን፤ ይህን ስታደርጉ በተለይ በምዕራፍ 3 እና 4 "Easter Enigma" በመባል ከሚታወቀው መጽሐፍ በፈቃድ የተቀዱ የተወሰኑ አስተሳሰቦች፣ ንድፎችና ካርታ ዕገዛ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ይታመናል። የዐይን ምስክሮችን በሐሳብ ተከተሉ፤ ያዩትን ለማየት፣ የሰሙትንም ለመስማት ጥረት አድርጉ፤ በእነርሱ ላይ ስለ ደረሰው ተጽዕኖ ዐስቡ፤ ልባችሁ እስከሚነካ ድረስ ስለ ተፈጸመው ታላቅ ክሥተት ውጤትና ትርጉም በመንፈስ ከሐዋርያት ጋር አሰላስሉ። አንባብያን ሆይ፤ የክርስቶስ ትንሣኤ ሕይወታችሁን እንዲለውጥ እግዚአብሔርን ለምኑ።

በመጽሐፉ መጨረሻ ለግል ጥናት ወይም ለቡድን ውይይት ሊጠቅሙ በሚችሉበት መንገድ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ላይ ተመሥርተው የቀረቡ ጥያቄዎች ይገኛሉ።

በመጽሐፉ ውስጥ ከሚከተሉት ምንጮች የተወሰኑ ሐሳቦች ተጠቅሰዋል:-

1. J. Wenham: *Easter Enigma:* Paternoster, 1992.
2. S. Allbery: *Lifted: Experiencing the Resurrection Life:* IVP, 2010.
3. M. Green: *Man Alive:* IVP, 1967.
4. J. McDowell: *The Resurrection Factor:* Alpha, 2000.
5. Matthew Henry's Commentary on the whole Bible: Marshall Pickering, 1967.
6. ክርስቲያንነት:- ጆን ስቶት:- ኢቫሉ 2006።

ምዕራፍ 1

ትንሣኤ ክርስቶስን እንዴት እንመለከተዋለን?

ማርክሳዊ አመለካከት የነበረው አንድ መስኮባዊ ምሁር በብዛት ለተሰበሰበ ሕዝብ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ንግግር አደረገ። ንግግሩ ረጅም ጊዜን የወሰደ ሲሆን፣ ዐላማው የክርስቶስን ትንሣኤ ዝቅ አድርጎና አቃልሎ ማቅረብ ነበር። በመጨረሻ አንድ ኦርቶዶክሳዊ ቄስ ስለ ቀረበው ንግግር ተነሥተው አስተያየት ለመስጠት እንዲፈቀድላቸው ጠየቁ። ለአስተያየቱ ዐምስት ደቂቃ ብቻ ቢፈቀድላቸውም፣ እርሳቸው "ዐምስት ሰኮንድ ይበቃኛል" አሉ፤ ወደ ሕዝቡ ዙረው፣ "ክርስቶስ ተነሥቷል" ብለው ከፍ ባለ ድምፅ በምሥራቅ ኦርቶዶክሳውያን ዘንድ የተለመደውን የፋሲካ ሰላምታ አቀረቡ፤ ሕዝቡም በታላቅ ጩኸት፣ "ሃሌሉያ! ክርስቶስ በእውነት ተነሥቷል" ብሎ መለሰ።

ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የክርስቶስ ትንሣኤ የክርስቲያናዊ ምስክርነት መሠረት ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቷል! የሮም ታሪክና የዓለም ዘመናዊ ታሪክ ሊቅ ማቲው አርኖልድ፣ "እውነትን ለማስተዋል ለሚፈልግ ቅን ሰው፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ከሰጠን የላቀ ታላቅ ምልክት ሌላ፣ በዓለም ታሪክ ሁሉ ከፍ ባለ ልዩ ልዩ ዐይነት ማስረጃ የተረጋገጠ ድርጊትን አላውቅም"[1] ብሎአል። በከፍተኛ ማዕረግ ያገለገለ አንድ የሕግ ዐዋቂ፣ "በዓለም ሁሉ ላይ ብልኅ የሆነ ማንኛውም ዳኛ፣ የትንሣኤ ታሪክ እውነተኛ መሆኑን ከመደገፍ በቀር ሌላ የፍርድ ውሳኔ መስጠት አይችልም"[2] አለ።

ይሁን እንጂ ሰው ሁሉ የክርስቶስን ትንሣኤ በዚህ ዐይነት መንፈስ አይመለከተውም። ኧርነስት ረኖ የተባለው ፈረንሳዊ ሊቅ፣ "ተአምር ፈጽሞ የለም፤ ስለዚህ ክርስቶስ ከሙታን አልተነሣም" ከሚለው አመለካከት ተነሥቶ ስለ ክርስቶስ ሕይወት ያደረገውን ምርመራ የጀመረ መሆኑን ገለጠ። የረኖ ውሳኔ አስቀድሞ በተገመተ የፍልስፍና አስተያየት ላይ የተመሠረተ ነበረና በሕግ ፊት ተቀባይነትን ከቶ ሊያገኝ አይችልም።

[1] በJ. McDowell "The Resurrection Factor" በገጽ 21 የተጠቀሰ።

[2] Ibid ገጽ 23።

አንዳንድ ሰዎችን በክርስቶስ ትንሣኤ እንዳያምኑ የሚያደርጋቸው የፍልስፍና አስተሳሰባቸው ቢሆንም፣ ለሌሎች ዕንቅፋት የሚሆንባቸው ደግሞ ሃይማኖታቸው ነው፤ ለምሳሌ፣ በቁርአን ውስጥ ተጽፎ በሚገኘው አንድ የታወቀ አንቀጽ መሠረት ኢየሱስ ሳይሰቀል በእግዚአብሔር በቀጥታ ወደ ሰማይ እንደ ተወሰደ የሃይማኖቱ ተከታዮች ያምናሉ፤ "አይሁድ፣ 'የማርያምን ልጅ፣ የአላኽ መልእክተኛ ክርስቶስ ኢየሱስን ገደልን' ብለው ፎከሩ። ቢሆንም የገደሉት መሰላቸው እንጂ አልገደሉትም፤ አልሰቀሉትምም፤ እንደ ገደሉት የሚናገሩት (አይሁድና መልእክቱን የሚያምኑ ክርስቲያኖች) ስለሚጠራጠሩ ስለ ነገሩ በርግጥ አያውቁም፤ ይልቁንም አላኽ ለራሱ አስነሣው፤ አላኽ በጎይል ከፍ ያለ፣ በጥበብ የተሞላ ነውና"[3]። ጥንታዊው ሙስሊም ሊቅ ኢብን አበአስ፣ "አላኽ ነቢዩን ወደ ሰማይ ለማስነሣት በፈለገ ጊዜ፣ ኢየሱስ ከጠጉሩ ውሃ እየተንጠባጠበ ወደ ደቀ መዛሙርቱ ቀረበ። በቤት ውስጥ ዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ነበሩ፤ እንዲህ አላቸው፣ 'በእኔ ከምታምኑት አንዳንዶቻችሁ በእኔ የነበራችሁን እምነት ዐሥራ ሁለት ጊዜ ትተዋላችሁ።' ቀጥሎም፣ 'እኔን መስሎ በእኔ ፈንታ የሚገደልና በሰማይ ከእኔ ጋር ለመኖር ፈቃደኛ የሚሆን ማን ነው?' ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው። ከሁሉም ታናሽ የሆነው ሲነሣ፣ ኢየሱስ፣ 'ተቀመጥ' አለው። ኢየሱስ ሁለተኛ ጊዜ ሲጠይቅ፣ በፊት የተነሣው ወጣት እንደ ገና ተነሥቶ፣ 'ፈቃደኛ እኔ ነኝ' ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም፣ 'የምትተካኝ አንተ ነህ' አለው። ወጣቱ ኢየሱስን ይመስላል፤ ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ከቤት ወደ ሰማይ ተወሰደ። አይሁድ መጥተው ኢየሱስን የሚመስለውን ሰው አገኙ፤ ከገደሉት በኋላም ሰቀሉት"[4] ብሎ ተናገረ ይባላል። እንግዲህ አብዛኞች ሙስሊሞች በኢየሱስ ፈንታ ሌላ ሰው እንደ ተሰቀለ፣ ኢየሱስ ራሱ ግን ሳይሞት በቀጥታ ወደ ሰማይ እንዳረገ ያምናሉ። ይህ እምነት ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በተጻፈው ማስረጃ ላይ ሳይሆን፣ ስለ ቁርአን ባላቸው ሃይማኖታዊ አመለካከት ላይ የተመሠረተ ነው።

[3] ቁርአን፣ 4ኛ ሱራ (ምዕራፍ) ቁ.157-158 በ'አብዱላ ዩሱፍ አሊ' የተተረጐመ።

[4] Ibn Katheep፤ Stories of the Prophets: from Adam to Muhammad, 2nd edition ገጽ 349-350 የተተረጐመ።

በዘመናችን፣ በሳይንስ ያልተረጋገጠ ማንኛውንም ነገር መቀበል እንደማይቻል የሚያስቡ ሰዎች ብዙ ናቸው። "የክርስቶስን ትንሣኤ በሳይንስ መሠረት ማረጋገጥ ትችላላችሁን?" ብሎ አንድ ሰው ቢጠይቅ፣ እውነተኛው መልስ፣ "አንችልም" መሆን አለበት። የሳይንስ ማረጋገጫ፣ በጠያቂው ሰው ፊት ድርጊቱን በድጋሚ በማሳየት ላይ የተመሠረተ ነው፤ የአንድ መላምት ሙከራ ሳይቋረጥ ሲቀጥል የተገኘውን መረጃ መሰብሰብ የሳይንስ አንድ መሠረታዊ አሠራር ነው። የዘመናዊ ሳይንስ አሠራር ደጋግሞ በሚፈጸሙ ድርጊቶች ወይም እውነቶች ብቻ ተመርኩዞ ሊከናወን የሚችል ነው፤ እንግዲህ በዓለም ታሪክ ሂደት አንድ ጊዜ የተፈጸመው የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ሳይንሳዊ ምርመራ የሚመለከተው አይደለም።

በእምነትና በዓለም ታሪክ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመረምረው የትምህርተ መለኮት ሊቅ ቮልፍሃርት ፓንንበርግ፣ "የኢየሱስ ትንሣኤ መፈጸም አለመፈጸም ታሪካዊ ጥያቄ ነው፤ ከዚህ መሸሽ አንችልም፤ ስለዚህ ጥያቄው በታሪካዊ ደረጃ ክርክር ተደርጎ እንዲወሰን ያስፈልጋል"[5] ብሎአል። የክርስቶስ ትንሣኤ በዓለም ታሪክ እንደ ተፈጸመ ሌላ ክሥተት ሁሉ በተመሳሳይ መስፈርት እንዲገመገም ያስፈልጋል። የጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን እምነት በዓለም ታሪክ በተፈጸሙ ድርጊቶች ላይ የተመሠረተ ነበር፤ ለምሳሌ፣ ክርስቶስ ራሱ ሕያው መሆኑን ለደቀ መዛሙርቱ ያሳያቸው "በብዙ ማስረጃ" መሆኑን ቅዱስ ሉቃስ ገልጾአል። ለ"ማስረጃ" የተጠቀመበት ቃል "ተክመሪዮን" (tekmierion) ማለት መታየት የሚችሉ ማረጋገጫዎች ማለት ነው።

ታሪክ ጸሓፊው ሮናልድ ሳይደር፣ "ከልምዳችን ውጭ ነው ለተባለ ክሥተት በቂ ማስረጃ እንዲሰጥ ለመጠየቅ መብት ቢኖረንም፣ አንድ ክሥተት እውነተኛ መሆን አለመሆኑን በውሱን ልምዳችን ተጠቅመን ፍርድ ለመስጠት እንደፍርም። ለናዝሬቱ ኢየሱስ ትንሣኤ ጥሩ ማስረጃ አለን ባይ ነኝ።"[6] በተጨማሪ ታሪክ ጸሓፊው ፊልጶስ

[5] ከWolfhart Pannenberg: "A Dialogue on Christ's Resurrection".
[6] Ronald Sider: "A Case for Easter".

ሻፍ፣ "የታሪክ ጸሓፊ ዐላማ፣ አስቀድሞ ከነበሩት ሐሳቦች ታሪክን ፈጥሮ እንደ ፍላጎቱ መለወጥ ሳይሆን፣ ከሚገኘው የተሻለ ልዩ ልዩ ማስረጃ አንጻር ታሪኩን አቅርቦ ታሪኩ ለራሱ እንዲናገር መፍቀድ ነው።"[7]

ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ማስረጃ የሚሰጠው ዋና ታሪካዊ ምንጭ ዐዲስ ኪዳን ነው፤ ስለዚህ የዐዲስ ኪዳን ጸሓፊዎች የሰጡትን መረጃ በጥንቃቄ መመልከትና ማመዛዘን ይገባናል። ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ምንም ዐይነት የይፋ ዐዋጅ አልተሰጠም፤ ስለ ትንሣኤው የሚናገሩት በወቅቱ የነበሩ ሰዎች (ቅዱስ ማቴዎስና ቅዱስ ዮሐንስ) ናቸው፤ ወይም ደግሞ የዐይን ምስክሮችን የሚያውቁ ሌሎች ሰዎች (ቅዱስ ጳውሎስ)። እያንዳንዱ የወንጌል ጸሓፊ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ የግል አመለካከት አለው። አራት ሰዎች ከየአቅጣጫው የአንድን ሕንጻ ምንነት እንዲገልጡ ቢጠየቁ፣ ሕንጻውን ከሰሜን አቅጣጫ ሆኖ የሚመለከተው ሰው መግለጫ ከደቡብ አቅጣጫ ከሚያየው ሰው መግለጫ በልዩ ልዩ ነገር ይለያል፤ ከምሥራቅና ከምዕራብ ሕንጻውን የሚመለከቱ ሰዎች አስተያየትም ከሌሎች የተለየ ይሆናል፤ ሕንጻው አንድ በመሆኑ እያንዳንዱ ተመልካች ከራሱ አቋም ተነሥቶ ስለ ሕንጻው የሚናገረው እውነት ነው። እንደዚሁ በአራቱ ወንጌላውያን ስለ ትንሣኤ የተነገሩትን ሐሳቦች ጎን ለጎን ብናነጻጽር የሚጋጩ ሊመስለን ይችላል። ታሪኩን ከእያንዳንዱ ወንጌላዊ አመለካከት አኳያ ለመረዳት ስንሞክር ግን ምናልባት መፍትሔ እናገኛለን።

አራቱ ወንጌላውያን፣ ልዩ ልዩ ሰዎች በክርስቶስ ትንሣኤ እንዴት እንደ ተነኩ፣ እንዴትም እንደ ተሰማቸው ይገልጡልናል። ትንሣኤው በማንኛውም ዘመን ለምንኖር አንባብያን እንዲናገር ስለሚፈልጉ የተወሰነን መልስ እንድንሰጥ ይጋብዙናል።

አራቱ ወንጌላውያን፣ በትንሣኤው ወቅት የተፈጸሙትን ድርጊቶች ሲገልጹ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ትንሣኤው ከሰጠን ማስረጃ በላይ በክርስቶስ የተገለጠለትን የትንሣኤውን መለኮታዊ ትርጉም ያቀርብልናል፤ በተጨማሪም የክርስቶስ ትንሣኤ ሕይወቱን እንዴት

[7] Philip Schaff: "History of the Christian Church", vol.1, p.175.

እንደ ለወጠው፣ ይኸውም ለአሁንና ለወደፊት ምን ትርጉም እንዳለው ያሰረዳናል።

ይህ መጽሐፍ የክርስቶስን ትንሣኤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ አመለካከት እንዲያጤነው አንባቢውን ለመርዳት ይሞክራል፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆነ ባዕድ ምንጭን በጥልቀት መመርመር ወይም ትንሣኤውን የሚቃወሙ ተቺዎችን ክርክር በዝርዝር መመልከት ከዚህ መጽሐፍ የአቀራረብ ባሕርይ ውጭ ነው። የመጽሐፉ ዐላማ፣ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ለተጻፈው እውነት ሁሉ ሕይወትን መስጠት፣ የትንሣኤው ማስረጃዎች ተስማሚ መሆናቸውን ማሳየትና ትንሣኤውን በይበልጥ እንዲያስተውሉት፣ በሕይወታቸውም ተግባራዊ እንዲያደርጉት አንባብያንን ማነሣሣት ነው። የተፈጸሙ ድርጊቶችን ያዩትን፣ ሕያው ከሆነው ከክርስቶስ ጋር የተገናኙትንም ደቀ መዛሙርት እንድንከተላቸው እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ አማካይነት ይጋብዘናል፤ በጥርጣሬአቸው፣ በፍርሀታቸው፣ በናፍቆታቸውና በደስታቸው ላይ እንድንሳተፍም ያደፋፍረናል። ይህን ታላቅ ትምህርት ስናጠና፣ የክርስቶስ ሐዋርያትና ሌሎች ደቀ መዛሙርት እንዳደረጉት ሁሉ፣ እኛም ከሙታን ከተነሣው ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እንድንገናኝ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ይርዳን!

ምዕራፍ 2

ስለ ትንሣኤ ክርስቶስ የተነገረው ትንቢት

ጊዜው የሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ምሽት ገደማ ነበረ፤ የናዝሬቱ ኢየሱስ ከተሰቀለ ሦስተኛ ቀን ሆኖታል። ዐሥራ አንዱ የኢየሱስ ሐዋርያትና ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ጥቂቶቹ፣ አይሁድን ፈርተው በአንድ ትልቅ ቤት ሰገነት ላይ ተሰብስበው ስምዖን ጴጥሮስ በነገራቸው ዜና ላይ እርስ በርስ በጉጉት ይወያዩ ነበር። በድንገት በሩ ተከፈተ፤ ቀለዮጳ የተባለው ደቀ መዝሙርና ጓደኛው ትንፋሽ እያጠራቸው ፈጥነው ገቡ። ምንም እንኳ የምሽት ጊዜ ቢሆንም፣ ያዩትንና የሰሙትን ለዐሥራ አንዱ ለመመስከር ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ከኤማሁስ ወደ ኢየሩሳሌም የ11 ኪሎ ሜትር መንገድ ተመልሰው መጥተው ነበር። ዐሥራ አንዱም፣ "ጌታ በእውነት ተነሥቷል ለስምዖንም ታይቷል" (ሉቃ. 24፥34) በማለት ተቀበሏቸው። እነርሱም በመንገድ ላይ ጌታችን ኢየሱስ ከቅዱሳት መጻሕፍት ምን እንዳስረዳቸው፣ እንጀራውንም በቄረሰ ጊዜ እንዴት እንደ ተገለጠላቸው ተረኩላቸው።

"ይህንም ሲነጋገሩ፣ ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ፣ ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው" (24፥36)። ደቀ መዛሙርቱ ደንግጠው መንፈስ ያዩ መሰላቸው፤ ጌታችን ግን እጆቹንና እግሮቹን መርምረው እርሱ ራሱ መሆኑን እንዲያውቁ ጋበዛቸው፤ ቀጥሎም ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቍራሽ በፊታቸው በላ። "እርሱም ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው"፤ 24፥44-45።

ጌታችን ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በሰጠው መግለጫ፣ የመሲሑ መሞትና ከሙታን መነሣት ድንገተኛ አለመሆኑን አስረዳቸው፤ እንደ እግዚአብሔር ዕቅድ መፈጸሙ በብሉይ ኪዳንም ተገልጦ ነበር። ብሉይ ኪዳን ለክርስቲያኖች ከፍ ያለ ዋጋና አስፈላጊነት እንዳለው ከሚያስቈጥሩ ምክንያቶች ይህ አንዱና ዋናው ነው፤ ይኸውም፣

በብሉይ ኪዳን በትንቢት የተነገረው በዐዲስ ኪዳን ይፈጸማል የሚለው ነው። እንግዲህ፣ "ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን" በተረጐመላቸው ጊዜ፣ ጌታችን ወደ ኤማሁስ ለሚሄዱ ደቀ መዛሙርት ምን ሊያስተምራቸው ዐሰቡ ይሆን? ሁለቱ ደቀ መዛሙርት በኋላ፣ "በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን?" ስለ ተባባሉ፣ ትምህርቱ የሚያስደንቅ እንደ ሆነ እናውቃለን፤ ሉቃ. 24፥27።

ትንሣኤ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን

በጌታችን የደረሰበት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተጽፎ እንደሚገኝ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ከራሱ ሰምተናል። ይልቁንም ጌታችን በመስቀል መንገድ መሄዱ የግድ አስፈላጊ እንደ ሆነ የታወቀበት አንዱ ትልቁ ምክንያት፣ "ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ" (ሉቃ. 24፥44) የሚለውን በግልጽ መናገሩ ነው፤ መጻሕፍቱ የአብ ፈቃድ መገለጫ ነበሩና። በዕለተ ሐሙስ ከእርሱ ጋር ለተሰበሰቡት ደቀ መዛሙርት፣ "ከዐመፀኞች ጋር ተቈጠረ ተብሎ የተጻፈው በእኔ ሊፈጸም ግድ ነው" አላቸው፤ ሉቃ. 22፥37፤ በጌቴሴማኒ ጌታችን ኢየሱስን ከወታደሮች እጅ ለማዳን በሰይፍ የሰው ጆሮ የቈረጠውን ደቀ መዝሙሩን ጴጥሮስን፣ "... አባቴን ብጠይቀው ከዐሥራ ሁለት ክፍለ ሰራዊት የሚበልጡ መላእክትን የማይሰድልኝ ይመስልሃልን? ይህ ቢሆን ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍት ይሆናል ያሉት ነገር እንዴት ይፈጸማል?" ብሎ ወቀሠው፤ ማቴ. 26፥53-54 (አ.መ.ት.)። "ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን?" በማለት ወደ ኤማሁስ የሚጓዙትን ደቀ መዛሙርት በፊት ስለ መሲሑ የተገለጠውን አስረዳቸው፤ ሉቃ. 24፥26።

ሐዋርያው ጳውሎስም፣ የመሲሑን (ክርስቶስ) ሞትና ትንሣኤ የሚያመለክተው ወንጌል አስቀድሞ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፈ ስለ መሆኑ፣ "መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረም፣ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ" (1ቆሮ. 15፥3-4) በማለት፣ ጌታ ያስተማረውን እውነት አስተጋባ።

ሁሉንም የብሉይ ኪዳን ዋና ዋና ክፍሎች ማለት "በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም" አንድ በአንድ መርምረን ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ የተጻፉትን እንመለከታለን፤ ይህን ስናደርግ፣ ጌታችንና ሐዋርያት ብሉይ ኪዳንን ሲተረጕሙ የሰጡትን መመሪያ መከተል እንጂ እንደ ራሳችን ሐሳብ በልዩ ልዩ ጥቅሶች ትንሣኤውን ምሳሌ በመመሰል ዘዴ ማመልከት አስፈላጊ አይደለም።

እንግዲህ የሙሴን ሕግና ነቢያትን፣ መዝሙራትንም ስንመረምር፣ መሲሑ ከሙታን እንደሚነሣ በሦስት ዐይነት መልክ ሲገለጥ እናያለን:-

1. አስቀድሞ በማመላከት

አስቀድሞ ማመላከት ማለት በታሪካዊ ክሥተት ወይም በሚታይ ሥርዐት ወደፊት ወደሚፈጸም ነገር ማመልከት ማለት ነው። ከብሉይ ኪዳን ሦስት ምሳሌዎችን በዐጭሩ እንመለከታለን:-

ሀ) የአብርሃምና የይስሐቅ ታሪክ፤ ዘፍ. 21-22

እግዚአብሔር ለሙታን ሕይወትን የሚሰጥ አምላክ እንደ ሆነ በአብርሃምና በይስሐቅ ታሪክ ሁለት ጊዜ ልናይ እንችላለን። የመጀመሪያው ጊዜ የይስሐቅን ልደት ሲያመለክት፣ ሁለተኛው ደግሞ የይስሐቅን መሠዋት ያመለክታል። ይስሐቅ ሳይወለድ አብርሃም ስለ ነበረበት ሁኔታ በዐዲስ ኪዳን ዋና ሐተታ የሚሰጠን ሐዋርያው ጳውሎስ ነው፤ "ለሙታን ሕይወትን በሚሰጥ የሌለውንም እንዳለ አድርጎ በሚጠራ ባመነበት በአምላክ ፊት የሁላችን አባት ነው" በማለት ስለ አብርሃም ከተናገረ በኋላ፣ ሐዋርያው የእግዚአብሔር ኀይል በአብርሃም ሰውነት እንዴት እውን እንደ ሆነ ይገልጣል፤ "ዘርህ እንዲሁ ሊሆን ነው እንደ ተባለ፣ ተስፋ ባልሆነው ጊዜ የብዙ አሕዛብ አባት እንዲሆን ተስፋ ይዞ አመነ። የመቶ ዓመትም ሽማግሌ ስለ ሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና የሣራ ማሕፀን ምውት መሆኑን በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ፤ ለእግዚአብሔርም ክብር እየሰጠ፣ የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል አጥብቆ እየተረዳ፣ በእምነት በረታ እንጂ በአለማመን ምክንያት በእግዚአብሔር ተስፋ ቃል አልተጠራጠረም"፤ ሮም 4፥18-21፤ ዕብ. 11፥11-12

ይመ.። ለሙታን ሕይወትን የሚሰጥ የትንሣኤ አምላክ ጎይል መጀመሪያ በራሱ ሰውነት ሲሠራ እንዲያውቅ እግዚአብሔር ሁኔታውን አመቻቸ። እንደ እግዚአብሔር ተስፋ ቃል ይስሐቅ በተወለደ ጊዜ፣ ለሙታን ሕይወትን የሚሰጥ አምላክ፣ "የሰጠውንም ተስፋ ደግሞ ሊፈጽም እንዲችል" አጥብቆ የተረዳው የአብርሃም እምነት ከንቱ አለመሆኑን አሳየ፤ ሮም 4፥21።

ሁለተኛው ጊዜ የአብርሃም እምነት እግዚአብሔር ለሙታን ሕይወትን መስጠት መቻሉን የሚገልጥበት ወቅት ነው፤ አብርሃም ልጁን መሥዋዕት አድርጎ በሞሪያ ምድር እንዲያቀርብ እግዚአብሔር የተናገረበትን ወቅት ይመለከታል። በዐዲስ ኪዳን ስለዚህ ጉዳይ የተጻፈው ሐተታ በዕብራውያን መልእክት ውስጥ ይገኛል፤ "አብርሃም በተፈተነበት ጊዜ ይስሐቅን በእምነት አቀረበ፤ እግዚአብሔር ከሙታን እንኳ ሊያስነሣው እንዲቻለው አስቦአልና፣ ከዚያም ደግሞ በምሳሌ አገኘው"፤ ዕብ. 11፥17-19። ብዙ ክርስቲያኖች ይህ ታሪክ በተለይ የክርስቶስን መሥዋዕታዊ ሞት በምሳሌ እንደሚገልጥ ያስባሉ፤ ይሁን እንጂ፣ የዐዲስ ኪዳን ትኵረት በትንሣኤው ላይ ነው። ከኬብሮን ወደ ሞሪያ በፈጀው ረጅም ጉዞ፣ አብርሃም ስለ እግዚአብሔር ማንነትና አሠራር ሳያስላስል አልቀረም፤ መሠረቱ በይስሐቅ መወለድ የተቀበለውን የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል መፈጸም ሲሆን፣ ምዉት ለሆነው ለራሱ ሰውነት፣ ለሣራም ምዉት ማሕፀን ሕይወትን የሰጠ እግዚአብሔር መሥዋዕት ተደርጎ ወይም ዐልፎ የተሰጠውን ልጃቸውን ከሙታን ሊያስነሣው አይችልምን? ይችላል እንጂ! ሁለቱም ሁኔታዎች ሰው የማይችላቸው ነገሮች አልነበሩምን? እግዚአብሔር ግን ሁሉን እንደሚችል "ኤልሻዳይ" አምላክ ለአብርሃም አልተገለጠለትምን? በእግዚአብሔር ፈቃድ አብርሃምና ይስሐቅ ከነአገልጋዮቻቸው ወደ ሞሪያ አካባቢ የደረሱበት "ሦስተኛው ቀን" ነበረ። በጉዞው ላይ በተገነዘባቸው ሐሳቦች ተጽናንቶ፣ አብርሃም አገልጋዮቹን፣ "አህያውን ይዛችሁ ከዚህ ቆዩ፤ እኔና ልጄ ወደዚያ ሄደን እንሰግዳለን፣ ወደ እናንተም እንመለሳለን" አላቸው፤ ዘፍ. 22፥5። አባትና ልጅ አንድ ላይ ሲሄዱ፣ ስለ መሥዋዕት ለሚጠይቀው ልጁ አባቱ አብርሃም፣ "ልጄ ሆይ፣ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል" አለው፤

ቊ.8። አብርሃም እንደ እምነቱ ሆነለት፤ ልጁን ያርድ ዘንድ ቢላዋ ባነሣ ጊዜ፣ የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ አብርሃምን ጠራው፤ "አብርሃም አብርሃም አለው፤ እርሱም፣ እነሆኝ አለ። እርሱም፣ በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ፣ አንዳችም አታድርግበት፤ አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደ ሆንህ አሁን አውቄአለሁ"፤ ዘፍ. 22፥11-12። ቀጥሎም አብርሃም አሻቅቦ ሲመለከት፣ በቊጥቋጦ መካከል ቀንዶቹ የተጠላለፉ አንድ አውራ በግ አይቶ፣ በጉን በልጁ ፈንታ መሥዋዕት አድርጎ በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር አቀረበ። ልጁ ይስሐቅም ተነሥቶ በሕያውነት ከአባቱ ከአብርሃም ጋር ወደ አገልጋዮቹ፣ በኋላም ወደ እናቱ ወደ ሣራ ተመለሰ። ከሙታን በሚያስነሣው እግዚአብሔር ላይ አብርሃም የነበረው እምነት ከንቱ አልነበረም። ጌታችን ኢየሱስም፣ "አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤትን አደረገ፣ አየም ደስ አለው" ብሎ ለአይሁድ በመናገሩ፣ በምሳሌ በልጁ የተፈጸመበት ሁሉ ከዘሩ ወደሚወጣው መሲሕ እንደሚያመለክት አብርሃም ያስተዋለ ይመስላል።

ለ) በማስተስረያ ቀን ሕያው እንደ ሆነ የሚለቀቀው ፍየልና ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባው ሊቀ ካህናት፤ ዘሌ. 16

በሙሴ ዘመን በተሰጠው ሥርዐተ ሕግ ውስጥ በተለይ አንድ ሥርዐት የመሲሑን ትንሣኤ ከወዲሁ ያመለክታል፣ ይህም የማስተስረያ ወይም የስርየት ቀን ነው። በዚህ ዓመታዊ በዓል የእስራኤል ጉባኤ ሁሉ ሥራ እንዳይሠሩ፣ ምግብም እንዳይበሉ ተነግሯቸው ነበር፤ በእግዚአብሔር ፊት ተሰብስበው፣ ኀጢአታቸውንም ተናዝዘው በታረደ እንስሳ መሥዋዕት የእግዚአብሔርን ስርየት እንዲያገኙ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገብቶ ነበር። በሥርዐቱ ሂደት ከሙታን ወደሚነሣው ክርስቶስ የሚያመለክቱ ሁለት ነገሮች አሉ፤ እነርሱም፣ በሕይወት እንዳለ የሚለቀቀው ፍየልና ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባው ሊቀ ካህናት ናቸው።

የእግዚአብሔርን ሕዝብ የኀጢአት ስርየት የሚመለከቱ ወደ ሊቀ ካህናቱ የሚቀርቡ ፍየሎች ሁለት ነበሩ፤ ዕጣ ሲጣል አንዱ የእግዚአብሔር በመሆን ለኀጢአት መሥዋዕት ተደርጎ ይሠዋል፤

ሌላውም "ወደ ምድረ በዳ ተለቅቆ ማስተስረያ ይሆን ዘንድ" (ዘሌ. 16፥10 አ.መ.ት.) በእግዚአብሔር ፊት ከነሕይወቱ ይቀርባል። ሁለቱም ፍየሎች የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አንድ መሥዋዕት ከወዲሁ የሚያመለክቱ ናቸው፤ የታረደው ፍየል ስለ ኀጢአታችን የሞተውን ክርስቶስን ሲያሳይ፣ የሚለቀቀው ፍየልም ከሙታን የተነሣውን ክርስቶስን ያመለክታል፤ "እርሱ ስለ ኀጢአታችን እንዲሞት ዐልፎ ተሰጠ፤ እኛን ጻድቅ አድርጎ ለማቅረብም ከሞት ተነሣ"፤ ሮም 4፥25 አ.መ.ት.።

ሁለተኛው ፍየል በክርስቶስ ሞት አማካይነት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሁለት ታላላቅ እውነቶችን ያብራራልናል። የመጀመሪያው፣ ሊቀ ካህናቱ እጆቹን በፍየሉ ራስ ላይ ጭኖ የሕዝቡን ኀጢአት ሲናዘዝ፣ የሕዝቡ ኀጢአት ሁሉ በፍየሉ ላይ መተላለፉን በማሳየት፣ ጌታችን ኢየሱስ፣ "እርሱ ራሱ በሥጋው ኀጢአታችንን በዕንጨት ላይ ተሸከመ" ወደሚለው የሐዋርያው ጴጥሮስ ሐተታ ይመራናል፤ ይህም በነቢዩ ኢሳይያስ፣ "እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ" ተብሎ ስለ መሲሑ የተጻፈው የትንቢት ቃል ፍጻሜ ነው፤ ኢሳ. 53፥6፤ 1ጴጥ. 2፥24። ሁለተኛው እውነት፣ የእስራኤል ኀጢአት ሁሉ ወደ ፍየሉ ስለ ተላለፈ፣ ኀጢአታቸው ሁሉ ይወሰድላቸዋል፤ ወደ ተለየ፣ ሰው ወደማይኖርበት ቦታም ይወገዳል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ሥጋው በመሸከም፣ "የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ነው"፤ ኢሳ. 38፥17፤ ሚክ. 7፥19፤ ዕብ. 8፥12። "ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፣ እንዲሁ ኀጢአታችንን ከእኛ አራቀ" ተብሎአል፤ መዝ. 102(103)፥12።

አንደኛው ፍየል ከታረደ በኋላ፣ ሊቀ ካህናቱ፣ "ደሙንም ወደ መጋረጃው ውስጥ ያመጣዋል... በመክደኛውም ላይና በመክደኛውም ፊት ይረጨዋል"፤ ዘሌ. 16፥15። ይህን በማድረግ ሊቀ ካህናቱ በኀጢአተኞች ፈንታ መሥዋዕታዊ ሞት የመፈጸሙን ማስረጃ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባል። በምሳሌያዊ መንገድ ሥርዐቱ በየዓመቱ መደገም ነበረበት። የዕብራውያን ጸሓፊ፣ "ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀ ካህናት ሆኖ፣ በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሠራች ማለት ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች

ድንኳን የዘለዓለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም" በማለት፣ ክርስቶስ የመሥዋዕትነቱን ምልክቶች ተሸክሞ በእግዚአብሔር ፊት እንዲገኝልን ሕያው ሆኖ ወደ ሰማያዊቷ ድንኳን በማረግ፣ ምሳሌያዊውን የብሉይ ኪዳን ሥርዐት እንደ ፈጸመ ያስረዳናል፤ ዕብ. 9፥11-12። እንግዲህ መሥዋዕትን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ ሊቀ ካህናት፣ የታረደው ፍየልና በሕይወት ያለው ፍየል ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አስቀድሞ እንደሚያመላክቱ እናስተውላለን። እንደ አሮን ሳይሆን እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ዘለዓለማዊ የሆነው ሊቀ ካህናት መሲሑ ጌታችን ኢየሱስ ነው፤ ሐዋርያው ዮሐንስ በሰማይ በተከፈተው በር በኩል በእግዚአብሔር ዙፋን መካከል የታረደ የሚመስል በግ አየ፣ ቢሆንም በጉ ቆሞ ስለ ተገኘ ሕያው ነው፤ ራእ. 5፥6። በማስተስረያ ቀን የቀረቡ ሁለት ፍየሎች ታርዶ ከቆመው በግ ጋር ተጣምረው እናያለን። "ሕያውም እኔ ነኝ፣ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፣ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ሕያው ነኝ" ብሎአል ከሙታን የተነሣው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ ራእ. 1፥18። ይህ አስደናቂ ራእይ በዙፋኑ ዙሪያ የሚገኙትን ፍጡራን፣ ሽማግሌዎችና መላእክት ወደ ውዳሴና ወደ አምልኮ የመራቸው መሆኑ አያስገርምም!

ሐ) የነቢዩ ዮናስ በታላቅ ዓሣ መዋጥ፤ ዮና. ም.1-2

በነቢያት መካከል ዮናስ ልዩ ነበረ፤ ወደ አሕዛባዊት ከተማ ወደ ነነዌ ሄዶ በእርሷ ላይ እንዲሰብክ እግዚአብሔር ጠራው። ዮናስ ግን፣ እግዚአብሔር ቸር፣ ንስሓ ለሚገቡት ሰዎች ሁሉ ርኅሩኅ የሆነ አምላክ መሆኑን ስላወቀ፣ ምሕረትን ከእስራኤል ውጭ ለሆኑ አሕዛብ እንዲያደርግላቸው ስላልፈለገ፣ ከእግዚአብሔር ፊት ኰበለለ፤ ዮና. 1፥1-3፤ 4፥1-2። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እንምቢተኛ የነበረውን አገልጋይ ተከታተለው፤ በመጀመሪያ፣ ዮናስ የሚጓዝባትን መርከብ ለማሰጠም ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስን አስነሣ። ነቢዩ በዚህ ወቅት እግዚአብሔር እንደሚገሥጸው ተገንዝቦ፣ መርከበኞች ወደሚናወጠው ባሕር እንዲጥሉት መከራቸው። እዚያም በውሃ ውስጥ እግዚአብሔር ዮናስን እንዲውጥ ታላቅ ዓሣ አዘጋጅቶ ነበር። ዮናስ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣው ሆድ ውስጥ ሲገኝ፣ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ

ከመቃብሩ ውስጥ ወደ እግዚአብሔር እንደ ጸለየ ይነግረናል፤ “በመከራዬ ሳለሁ ወደ እምላኬ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፣ እርሱም ሰማኝ፤ በሲኦልም ሆድ ውስጥ ሆኜ ጮኽሁ፣ ቃሌንም አዳመጥህ።... አንተ ግን፣ አቤቱ አምላኬ፣ ሕይወቴን ከጕድጓዱ አወጣህ።... ደኅንነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው”፤ ዮና. 2፥3፣7፣10። የእግዚአብሔር ጸጋ አሠራር ታላቅ ምሳሌ፣ ለነነዌ የተሳካለት ሰባኪ፣ ወደ ክርስቶስም የሚያመለክት “ጥላ” ይሆን ዘንድ ነቢዩ ዮናስ ከእግዚአብሔር ምሕረትን አገኘ። “ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፣ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል” ብሎ ሲያስተምር፣ ጌታችን በመቀበሩና ሕያው ሆኖ በመነሣቱ ራሱን ከነቢዩ ዮናስ ጋር አነጻጸረ፤ ማቴ. 12፥40። አንባቢው፣ የጌታችን ሥጋ ከዐርብ ምሽት ጀምሮ እስከ እሑድ ማለዳ ብቻ በመቃብር ስለ ነበረ፣ እንዴት ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በምድር ልብ ውስጥ መሆን ይችላል? ብሎ ቢጠይቅ፣ በአይሁድ አመለካከት መሠረት የቀኑ 24 ሰዓት ማናቸውም ክፍለ ጊዜ እንደ አንድ ቀን ስለሚቈጠር ነው፣ ጌታችን “ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት” በመቃብር ቈየ ሊባል የተቻለው። ዮናስ ለራሱ ዐመፅ ተግሣጽን ተቀብሎ ሞቶ ተቀበረ፤ ዮናስ ለሰው ባልተለመደ “መቃብር” ውስጥ እንደ ነበረ፣ ክርስቶስ ከድንጋይ ተፈልፍሎ በተሠራና ገና ማንም ባልተቀበረበት መቃብር ውስጥ ተቀመጠ። ሁለቱም ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ነቢዩ ዮናስ ለአሕዛብ ንስሓን እንዲሰብኩ ሕያው ሆነው ከመቃብራቸው ተነሡ፤ “የነነዌ ሰዎች... በዮናስ ስብከት ንስሓ ገብተዋል” (ማቴ. 12፥41) ሲባል፣ ስለ መሲሑ፣ “የያዕቆብን ነገዶች እንድታስነሣ ከእስራኤልም የዳኑትን እንድትመልስ ባሪያዬ ትሆን ዘንድ እጅግ ቀላል ነገር ነውና እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኀኒት ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ ...” (ኢሳ. 49፥6) ተብሎ በትንቢት የተነገረው ተስፋ ቃል በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተፈጸመ፤ እርሱ፣ “ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር” መሆኑን መንፈስ ቅዱስ ለሽማግሌው ስምዖን ገለጠለት፤ ሉቃ. 2፥32።

2. አስቀድሞ በመናገር

ትንሣኤ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን በምሳሌ ብቻ ሳይሆን፣ አስቀድሞ በተነገረው ቃል በትንቢት መልክ መገለጡን መገንዘብ አለብን። እነዚህ የትንቢት ቃሎች በመዝሙረ ዳዊትና በነቢያት ተጽፈው ይገኛሉ። አስቀድሞ የተሰጡ ምሳሌዎች እንዲያመላክቱ እንዳደረግን ሁሉ፣ የትንቢት ቃሎች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የዐዲስ ኪዳን ጸሓፊዎች ስለ ትንሣኤ ክርስቶስ የተናገሩ መሆኑን እንደ ተረዱ ማረጋገጥ አለብን፤ ለምሳሌ፣ መዝ. 15(16)፥8-11 ስለ መሲሑ የተነገረው በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመው የትንቢት ቃል መሆኑን የምናውቀው፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ በበዓለ ኀምሳ ቀን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ በዚህ አቅጣጫ ስለ ተረጐመው ነው፤ “ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ፤ በቀኜ ነውና አልታወክም። ስለዚህ ልቤን ደስ አለው ምላሴም ሐሤት አደረገች፤ ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራለች፤ ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፣ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውምና። የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ፤ ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ፣ በቀኝህም የዘለዓለም ፍሥሓ አለ።” ሐዋርያው ጴጥሮስ በብዙ ሕዝብ ፊት ይህን የትንቢት ቃል፣ “ወንድሞች ሆይ፣ ስለ አባቶች አለቃ ስለ ዳዊት እንደ ሞተም እንደ ተቀበረም ለእናንተ በግልጥ እናገር ዘንድ ፍቀዱልኝ፤ መቃብሩም እስከ ዛሬ በእኛ ዘንድ ነው። ነቢይ ስለ ሆነ፣ ከወገቡም ፍሬ በዙፋኑ ያስቀምጥ ዘንድ እግዚአብሔር መሐላ እንደ ማለለት ስለ ዐወቀ፣ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ አስቀድሞ አይቶ፣ ነፍሱ በሲኦል እንዳልቀረች ሥጋውም መበስበስን እንዳላየ ተናገረ። ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን” በማለት ዐተተ፤ ሐ.ሥ. 2፥25-32፤ ሐዋርያው ጳውሎስም በጲስድያ በሰበከ ጊዜ መዝ. 15(16)፥10ን ጠቀሰ፤ ሐ.ሥ. 13፥35። በስብከቱ ሐዋርያው በተጨማሪ መዝ. 2፥7ን እና ኢሳ. 55፥3ን ጠቅሶ፣ እነዚህ የትንቢት ቃሎች በክርስቶስ እንደ ተፈጸሙ ያስረዳናል፤ “እኛም ለአባቶች የተሰጠውን ተስፋ የምሥራቹን ለእናንተ እንሰብካለን፤ ይህን ተስፋ እግዚአብሔር በሁለተኛው መዝሙር ደግሞ:- አንተ ልጄ ነህ፣ እኔ ዛሬ ወለድሁህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ ኢየሱስን አስነሥቶ ለእኛ ለልጆቻቸው

ፈጽሞአልና። እንደ ገናም፣ ወደ መበስበስ እንዳይመለስ ከሙታን እንደ አስነሣው፣ እንዲህ:- የታመነውን የዳዊትን ቅዱስ ተስፋ እሰጣችኋለሁ ብሎአል” (ሐ.ሥ. 13፥32-34)፤ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆኑ ታላቅ ማረጋገጫ፣ ከሙታን መነሣቱ እንደ ሆነ በሮም 1፥4 ላይ ያስረዳናል።

የመዝ. 21(22) ዋና ትኩረት በመሲሑ ሕማምና ሞት ላይ ቢሆንም፣ በመካከል ላይ፣ “ስምህን ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ፣ በጉባኤም መካከል አመሰግንሃለሁ” ተብሎ የተጻፈው ቃል በዕብራውያን ጸሓፊ ሞቶ ሕያው ስለ ሆነው ክርስቶስ እንደ ተነገረ ግልጽ ነው፤ መዝ. 21(22)፥22፤ ዕብ. 2፥12፤ ሞቶ የነበረ ክርስቶስ በጉባኤ መካከል ቆሞ እግዚአብሔርን እንዴት ሊያመሰግን ይችላል? ከሐዘን ወደ ደስታ ተመሳሳይ የሆነ የስሜት ለውጥን በትንቢተ ኢሳይያስ ም.53 እናያለን። ስለ መሲሑ ሕማምና መሥዋዕታዊ ሞት ከተናገረ በኋላ፣ ነቢዩ፣ “እግዚአብሔር በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፤ ነፍሱን ስለ ኃጢአት መሥዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል፣ ዕድሜውም ይረዝማል፣ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል። ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል ደስም ይለዋል” (ቁ.10-11) በማለት፣ ነቢዩ የመሲሑን ትንሣኤ ያመለክታል፤ ገና እንደ ሞተ ከሆነ የመሥዋዕቱን ፍሬ እንዴት ሊቀምስ ይችላል? ከሌላ የትንቢት ቃል ሁሉ ይልቅ፣ ከዚህ ምዕራፍ ወደ ክርስቶስ የሚያመለክት ቃል፣ ሐረግና አንቀጽ ተጽፎ ይገኛል፤ ለምሳሌ፣ ዮሐ. 19፥34፤ ሐ.ሥ. 8፥32-33፤ 1ጴጥ. 2፥21-25።

መጽሐፈ መዝሙርና ነቢያት ብቻ ሳይሆኑ ጌታችን ኢየሱስ ራሱ ስለ ትንሣኤ አስቀድሞ እንደ ተናገረ ብናስታውስ መልካም ነው። አብዛኛውን ጊዜ ስለ ሞቱና ስለ ትንሣኤው አንድ ላይ ለመናገር ይወድ ነበር፤ የአንድ ታላቅ ክሥተት ሁለት ገጾች ናቸውና። በመጀመሪያ ጊዜ ጌታችን ስለ ትንሣኤ በግልጽ የተናገረው፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ፣ “አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ” ብሎ ከእግዚአብሔር አብ የተገለጠለትን ታላቅ እውነት ካወጀ በኋላ ነው፤ ማቴ. 16፥16፥21። መልኩ በቅጽበት ከተለወጠ ጥቂት ጊዜ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ እንደ ገና ስለሚደርስበት ሕማምና ሞት ሲያመለክት

እንደ በፊቱ፣ “በሦስተኛውም ቀን ይነሣል” ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ሲያጽናናቸው በጣም ዐዘኑ፤ ማቴ. 17፥23። ወደ ኢየሩሳሌምም በመንገድ ላይ ሲሄዱ ጌታችን የሚደርሱበትን ሕማማት በዝርዝር አብራርቶ፣ ለሐዋርያት እንደ ገና በሦስተኛው ቀን ከሙታን እንደሚነሣ ነገራቸው፤ ማቴ. 20፥17-19። በሞቱ ዋዜማ ከእነርሱ ጋር ወደ ጌቴሴማኒ ከመሄዱ ጥቂት ጊዜ በፊት፣ “ከተነሣሁ በኋላ ግን ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ” በማለት ሐዋርያቱን ሊያጽናናቸው ፈለገ፤ ማቴ. 26፥32። ለሌሎች ሰዎች ስለሚቀበለው መከራ ሲናገር በምሳሌያዊ ዐይነት ተናገረ፤ በቤተ መቅደስ ግቢ ውስጥ ለሚገዳደሩት አይሁድ፣ “ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፣ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው።... እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር። ስለዚህ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ ዐሰቡና መጽሐፉንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ”፤ ዮሐ. 2፥19፥21-22። በሌላ ጊዜ የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌዎች ስለ ሥልጣኑ ሲጠይቁት፣ ጌታችን የወይን ዕርሻ ገበሬዎችን ምሳሌ ነገራቸው፤ ገበሬዎች የወይኑን ዕርሻ ባለቤት ልጅ እንደ ገደሉት ከተናገረ በኋላ፣ “ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣ እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ፤ ይህም ከጌታ ዘንድ ሆነ፣ ለዐይኖቻችንም ድንቅ ነው” ብሎ በመዝ. 117፥(118)፥22-23 የተጻፈው ቃል በእርሱ እንደሚፈጸም ሌላ ምሳሌ በመጠቀም አድማጮቹን አሳወቀ፤ ማቴ. 21፥42።

3. አስቀድሞ በመጠበቅ

በትንሣኤ ሙታን የማያምኑት ሰዱቃውያን ሊፈትኑት አንድ ቀን ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጡ፣ ጌታችን በሕገ ሙሴ ውስጥ ወደ ተጻፈው እውነት እንዲመራቸው ምቹ ሁኔታ ተፈጠረለት፤ “ስለ ትንሣኤ ሙታን ግን:- እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ የሚል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን? የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም”፤ ማቴ. 22፥31-32፤ ዘፀ. 3፥6። በዕብራውያን አመለካከት ሕያው ሰው ሁልጊዜ ሥጋም ነፍስም ነው እንጂ ነፍስ ብቻ አይደለም። እንግዲህ “ያለና የሚኖር” እግዚአብሔር

የአብርሃምን፣ የይስሐቅንና የያዕቆብን ሰውነት ከሙታን እንደሚያስነሣ ማሰብ አመክንዮታዊ ነው።


በነቢያቱ በኤልያስና በኤልሳዕ አገልግሎት ሁለት የሞቱ ሰዎችን ከሞት በማስነሣት እግዚአብሔር ለትንሣኤ ሙታን መንገዱን ሲያዘጋጅ እናያለን። ነቢዩ ኤልያስ በረኀብ ጊዜ በአንዲት መበለት ቤት ሲኖር፣ አንድ ልጇ ትንፋሹ ቀጥ እስከሚል ድረስ ታመመ። ኤልያስ ልጁን ከእናቱ ዕቅፍ ወስዶ እርሱ ወደሚኖርበት ሰገነት አወጣው። በዐልጋው ላይ ካስተኛው በኋላ፣ "በልጁም ላይ ሦስት ጊዜ ተዘርግቶ፣ አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ፣ የዚህ ልጅ ነፍስ ትመለስለት ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ።" እግዚአብሔር የኤልያስን ጸሎት ሰማና ልጁን አስነሣው፤ 1ነገ. 17፥17-24 አ.መ.ት.። ነቢዩ ኤልሳዕም በሱነም ትኖር የነበረችውን ሴት ወንድ ልጅ ከሞተ በኋላ በተመሳሳይ ሁኔታ ወደ እግዚአብሔር በመጸለይ አስነሥቶ እናቱ እንድትወስደው አደረገ፤ 2ነገ. 4፥32-37። "ሴቶች ሙታናቸውን በትንሣኤ ተቀበሉ" ተብሎ በዕብራውያን 11፥35 የተጻፈው ለእነዚህ ሴቶች በነቢያት እምነት ወደ ተደረጉላቸው ተአምራት ሊያመለክት ይችላል።

በአገልግሎቱ ወቅት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት ጊዜ የሞቱትን እንዳስነሣ እናውቃለን። በመጀመሪያ ያስነሣው አንዲት መበለት የሞተባትን አንድያ ልጅ በመሆኑ፣ በኤልያስና በኤልሳዕ ዘመን የተደረጉ ተአምራትን ያሳስባል፤ ሉቃ. 7፥11-16። ሁለተኛው፣ ዕድሜዋ ዐሥራ ሁለት ዓመት የነበረች የኢያኢሮስ ሴት ልጅ ስትሞት፣ ጌታችን ለሚያለቅሱ ሰዎች፣ "ተኝታለች እንጂ አልሞተችም" ብሎ ልጅቷ ወደ ተኛችበት ክፍል መግባቱን፣ እጁንም ይዞ፣ "አንቺ ብላቴና፣ ተነሺ" ብሎ በጮኸ ጊዜ፣ ነፍሷ መመለሷንና ወዲያውም ተነሥታ መቆሟን የሚያሳየው ነው፤ ሉቃ. 8፥49-56። ሦስተኛው፣ የማርያምንና የማርታን ወንድም አልዓዛርን ከሙታን ለማስነሣት ወደሚኖሩበት መንደር መሄዱን የሚገልጠው ነው። ይህ ክሥተት ከጌታችን ሞትና ትንሣኤ በፊት የተፈጸመ ስለ ነበረ፣ ሐዋርያው ዮሐንስ በተለይ ለማርታ ስለ ትንሣኤ ለሰጣት ትምህርት ሰፊ ስፍራ ሰጠ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ስለ ክርስቶስ አስቀድሞ የተመለከተው፣ የተነገረውና የተጠበቀው በቅርብ ጊዜ ወደ ፍጻሜው

ይደርሳልና። "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል" (ዮሐ. 11፥25) በማለት ሞትን የሚያሸንፈው፣ የዘለዓለምን ሕይወትም ለነፍስ ብቻ ሳይሆን ለሥጋም የሚሰጥ ኢየሱስ ራሱ መሆኑን እንድትረዳ ማርታን ያደፋፍራታል። የዚህ ታላቅ እውነት ምልክት እንዲሆን ጌታችን ከአራት ቀን በፊት የሞተውን ወንድሟን፣ "አልዓዛር ሆይ፣ ወደ ውጭ ና" በማለት በታላቅ ድምፅ ጮኾ ከሙታን አስነሣው፤ ቁ.43።

ይሁን እንጂ በብሉይ ኪዳንና በአራቱ ወንጌላት በተጻፉ ድንቅ ሥራዎችና በትንሣኤ ክርስቶስ መካከል አንድ ትልቅ ልዩነት አለ፤ ይኸውም፣ በነቢያቱ በኤልያስና በኤልሳዕ፣ በጌታችንም ምድራዊ አገልግሎት፣ ከሙታን የተነሡ ሁሉ አንድ ቀን እንደ ገና መሞታቸው ነው፤ ሲነሡ በፊት ወደ ነበራቸው ሁኔታ ተመልሰዋልና። ክርስቶስ ግን እንደ ገና አይሞትም፤ ሕያው ሆኖ ለዘለዓለም ይኖራል፤ የእርሱም ትንሣኤ ለሚያምኑበት ሁሉ የትንሣኤያቸው አርአያ ነው፤ "የሙታን ትንሣኤም እንደዚሁ ነው፤ የሚበሰብስ አካል ይዘራል፤ የማይበሰብስ አካል ሆኖ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል፤ በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፣ በኀይል ይነሣል፤ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፣ መንፈሳዊ አካል ይነሣል" ብሎአል ሐዋርያው ጳውሎስ፤ 1ቆሮ. 15፥42-44 አ.መ.ት.።

ክርስቶስ ከሙታን በመነሣት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ እርሱ የተጻፈውን ሁሉ ፈጸመ፣ ይህ የትንሣኤው እውነተኛነት አንድ ትልቅ ምልክት ነው። ቢሆንም የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በዚያ ጊዜ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈውን ገና ስላላስተዋሉ፣ እግዚአብሔር ሌላ ዐይነት ማረጋገጫ ሰጣቸው፤ ይህን እንድንመረምር በሚከተሉት ምዕራፎች በዚያ ወቅት የነበሩ የዐይን ምስክሮች የተናገሩትን እንመልከት!



የክርስቶስን መሞትና መቀበር በዐይን ያዩ ምስክሮች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዐይን ምስክርነት ላይ የተደረገው ትኵረት ከፍ ያለ ነው፤ እምነታችን በቅዠትና በፈጠራ ላይ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር የዓለምን ታሪክ በሚያስፈጽምበት አስተርእዮ (መገለጥ) ላይ ስለ ተመሠረተ ነው።

እንግዲህ በሕግና በነቢያት አስቀድሞ የተመለከተው መሲሕ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም ሲመጣ፣ የሕይወቱን፣ የሞቱንና የትንሣኤውን ርግጠኛነት የሚመሰክሩ ሰዎች መገኘታቸው አያስገርምም። ከሙታን የተነሣው ጌታችን ኢየሱስ ስለ እርሱ የተጻፈው ወደ ፍጻሜ መድረሱን ባመለከተ ጊዜ ሐዋርያቱን፣ "እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ" አላቸው (ሉቃ. 24፥48)፤ ወደ ሰማይም ከማረጉ ጥቂት ጊዜ በፊት፣ "መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ... ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" አላቸው፤ ሐ.ሥ. 1፥8። ሐዋርያው ጴጥሮስ በበዓለ ኀምሳ ቀን:- "ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው፤ ለዚህም ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን" ብሎ በኢየሩሳሌም ለተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ ሰበከ፤ ሐ.ሥ. 2፥32። በሸንጎው ፊት ጴጥሮስና ሌሎች ሐዋርያት፣ "እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፣ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው" ብለው በድፍረት ተናገሩ፤ ሐ.ሥ. 5፥32።

ለቆርኔሌዎስና ከእርሱ ጋር ለነበሩት አሕዛብ ሐዋርያው ጴጥሮስ ስለ ክርስቶስ፣ "እርሱን እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሣው ይገለጥም ዘንድ ሰጠው፤ ይኸውም ለሕዝብ ሁሉ አይደለም ነገር ግን በእግዚአብሔር አስቀድሞ የተመረጡ ምስክሮች ለሆንን ለእኛ ነው እንጂ፤ ከሙታንም ከተነሣ በኋላ ከእርሱ ጋር የበላን የጠጣንም እኛ ነን" (ሐ.ሥ. 10፥40-41) በማለት፣ እግዚአብሔር ሐዋርያትን የመረጠበት ዋና ዐላማ፣ ስለ ጌታችን ኢየሱስ እንዲመሰክሩ መሆኑን ገለጠ። ሐዋርያው ጴጥሮስ በሕይወቱ መጨረሻ፣ በሁለተኛው መልእክቱ በቅዱሱ ተራራ ላይ የክርስቶስን ክብር እንዳየ አንባብያኑን አሳሰባቸው፤ "ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኀይልና ስለ መምጣቱ


የነገርናችሁ እኮ የእርሱን ግርማ በዐይናችን አይተን እንጂ፣ በሰዎች ጥበብ የተፈጠረውን ተረት ተከትለን አይደለም... እንግዲያስ ትንቢታዊው ቃል ይበልጥ ተረጋግጦልናል”፤ 2ጴጥ. 1፥16፡19 አ.መ.ት.። ሐዋርያው ዮሐንስም፣ “ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን፣ በዐይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፤ ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን” ብሎ አንደኛውን መልእክት መጻፍ ጀመረ።

ስለዚህ ወደ ዋናው የጌታችን ተግባር ማለት ወደ ሞቱና ወደ ትንሣኤው ስንደርስ፣ የዐይን ምስክሮች የተናገሩትን በማስተዋል ልንመለከተው ይገባል።

ሀ. የክርስቶስን መሞት በዐይን ያዩ ምስክሮች

ኀሙስ ማታ ከመያዙ ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ ገና የፋሲካን ራት ለመብላት ከሐዋርያት ጋር በሰገነቱ በነበረው አዳራሽ ውስጥ ሳለ፣ ጌታችን ኢየሱስ፣ “እረኛውን እመታለሁ የመንጋውም በጎች ይበተናሉ” የሚለውን ነቢዩ ዘካርያስ የጻፈውን ቃል በመጥቀስ፣ ሐዋርያት ሁሉ በእርሱ ምክንያት ተሰናክለው እንደሚሄዱ አስጠነቀቃቸው፤ ዘካ. 13፥7፤ ማቴ. 26፥31። ቀጥሎም ጌቴሴማኒ በተባለው የአትክልት ሰፍራ ጌታችን በይሁዳ ተላልፎ ተሰጥቶ ከካህናት አለቆችና ከፈሪሳውያን በተላኩት ወታደሮችና ሎሌዎች ሲያዝ የተናገረው ቃል ተፈጸመ፤ “በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተውት ሸሹ”፤ ማቴ. 26፥56።

ሐዋርያት ወዴት ሸሽተው ይሆን? ይሁዳ በጥፋቱ ተጸጽቶ ራሱን ሰቅሎ እንደ ሞተ እናውቃለን (ማቴ. 27፥5)፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስን በሩቁ ይከተሉት ነበር፤ ሌሎቹ ዘጠኙ ሐዋርያት፣ ይሁዳና ከእርሱ ጋር የነበሩት ከመጡበት በተቃራኒ አቅጣጫ ማለት ማርታና ማርያም ከወንድማቸው ከአልዓዛር ጋር ወደ ኖሩበት መንደር ወደ ቢታንያ ሳይሄዱ አልቀሩም። በዚያ ሳምንት በቢታንያ እያደሩ በየቀኑ ከጌታችን ኢየሱስ ጋር የተመላለሱበት መንገድ ነበረና።



1. ኢየሱስ በማርቆስ ቤት ውስጥ ከዐሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ጋር ፋሲካን በላ። ይሁዳ ሊያስይዘው ወጣ።
2. ኢየሱስ፣ ዐሥራ አንዱና ማርቆስ ከቤት ወጡ፣ የቄድሮንን ሸለቆም አቋርጠው ሄዱ። እረኛው እንደሚመታና በጎቹ እንደሚበተኑ ኢየሱስ አስጠነቀቃቸው።
3. ኢየሱስ ወደ ጸለየበት ወደ ጌቴሴማኒ ገቡ።
4. ይሁዳ የቤተ መቅደሱ ጥበቃ አባላትና ከቤተ መቅደሱ በስተ ሰሜን በሚገኘው በአንቶንያ ግንብ ሰፍሮ ከነበረው የሮማውያን ወታደሮች ምድብ የተውጣጡ ወታደሮች ከሚገኙበት ኢየሱስን ከሚይዙት ጋር ዐብሮ መጣ።
5. ዐሥራ አንዱ በቢታንያ አቅጣጫ በደብረ ዘይት ተራራ ሸቅብ ወጥተው አመለጡ፤ ማርቆስ ያመለጠው ለጥቂት ነው።
6. ኢየሱስ ወደ ከተማ ተመልሶ ተወሰደ፤ ጴጥሮስና ዮሐንስ ከፍርሀታቸው የተላቀቁ መሰላቸውና ወደ ሊቀ ካህናቱ መኖሪያ ከሚሄደው ወደ ከተማ ከሚመለሰው ቡድን ጋር ዐብረው ተቀላቀሉ። ጴጥሮስ በቀያፋ ግቢ ኢየሱስን ካደው።
7. ዮሐንስ ጴጥሮስን ሰሎሜ፣ ቀለዮጳና ማርያም፣ የኢየሱስ እናት ማርያምም እየጠበቋቸው ወደሚገኙበት ወደ ቤቱ ወሰደው።

የመጀመሪያው የዐይን ምስክር:- ሐዋርያው ጴጥሮስ

ከብዙ ዓመታት በኋላ ሐዋርያው ጴጥሮስ በስደት ምክንያት ለተበተኑት ክርስቲያኖች በጻፈ ጊዜ፣ የክርስቶስ መከራ ምስክር መሆኑን ገለጸላቸው፤ 1ጴጥ. 5፥1። በጌቴሴማኒ ጌታችን ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስንም ይዞ ለመጸለይ ሲሄድ፣ ደቀ መዛሙርቱ በሐዘን ከመተኛታቸው በፊት ጌታችን በጸሎት ሲታገል፣ ሲሠቃይም ቢያንስ በከፊል እንዳዩና እንደ ሰሙ ልንገምት እንችላለን። ይሁዳ ከወታደሮች፣ ከካህናት አለቆችና ከፈሪሳውያን ከተላኩ ሎሌዎች ጋር ሲደርስ፣ የጌታችን ወዳጅ በመምሰል በሳመው ጊዜ፣ ጌታችን እንዴት ይሠቃይ እንደ ነበረ ጴጥሮስ የዐይን ምስክር ነበረ። እርሱ ራሱ የክርስቶስ መንግሥት እንዴት ያለ እንደ ሆነ ባለማስተዋል የሊቀ ካህናቱን አገልጋይ ቀኝ ጆሮ በሰይፍ ሲቈርጥ ሳያስበው የጌታችን ኢየሱስ መከራ እንዲበዛ አደረገ። ወታደሮቹ ኢየሱስን በጎይል ሲይዙ፣ ጌታችን፣ "ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፍና ጕመድ ይዛችሁ ወጣችሁን?" (ሉቃ. 22፥52) ሲል፣ የደረሰበትን ሕማም ጴጥሮስ ከጌታችን ድምፅ ሳይሰማ አልቀረም። ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ሁሉ ጌታቸዉን ጥለውት ሲሸሹ፣ ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር (ዮሐንስ ሳይሆን አልቀረም) ወደ ሊቀ ካህናቱ ቤት ኢየሱስን የሚወስዱትን ሰዎች ተከትለው ሄዱ። ዮሐንስ መጀመሪያ ስለ ደረሰና ሊቀ ካህናቱ ያውቀው ስለ ነበር ከጌታችን ኢየሱስ ጋር ወደ ግቢው ገባ (ዮሐ. 18፥15)፣ ጴጥሮስ ከሩቅ ተከትሎ፣ ከበሩ ውጭ ቀረ፤ ዮሐንስ ግን ጠባቂዋን በማነጋገር ጴጥሮስን አስገባው።

በሊቀ ካህናቱ ግቢ ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ የተቀበለውን መከራ ጴጥሮስ ምን ያህል እንደ መሰከረ በይበልጥ እንድናስተውል፣ በዚያ ዘመን የሀብታም ሰውን የቤት አሠራር ብናስታውስ መልካም ነው። የቤት ክፍሎች በውስጠኛ አደባባይ ዙሪያ ስለሚሠሩ፣ በአደባባዩ የሚገኝ ሰው ከሚፈጸሙ ጉዳዮች ብዙውን ሊያይና ሊሰማ ይችል ነበር። "ጴጥሮስ ግን እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ድረስ ሩቅ ሆኖ ተከተለው፤ የነገሩንም ፍጻሜ ያይ ዘንድ ወደ ውስጥ ገብቶ ከሎሌዎቹ ጋር ተቀመጠ"፤ ማቴ. 26፥58። ጴጥሮስ በውጩ በር ከገባ በኋላ፣ በመጀለኪያው ዐልፎ በግቢው ውስጥ በታችኛው በኩል እንደ

ተቀመጠ ስለ ተጻፈ (ማር. 14፥66)፤ በዘመኑ እንደ ተለመደው ወደ ክፍሎች የሚያመሩ አንዳንድ ደረጃዎች ሳይኖሩ አልቀሩም። በግቢው ውስጥ የነበሩት በዚያ ዓመት የነበረው ቀያፋ የተባለው ሊቀ ካህናትና በሮማውያን ከሊቀ ካህናትነቱ የተሻረው ሐና የተባለው የቀያፋ ዐማት ናቸው። ወታደሮቹ ኢየሱስን መጀመሪያ ወደ ሐና እንደ ወሰዱት ሐዋርያው ዮሐንስ ይነግረናል፤ በአይሁድ መካከል ብዙዎች እንደ እውነተኛ ሊቀ ካህናት ሳይቈጥሩት አልቀረምና። ጌታችን በሐና ፊት ቆሞ ሳለ፣ ጴጥሮስ ሲገባ ጠባቂዋ፣ "አንተ ደግሞ ከዚህ ሰው ደቀ መዛሙርት አንዱ አይደለህምን?" ብላ በጠየቀችው ጊዜ፣ "አይደለሁም" በማለት ጌታውን በመጀመሪያ ጊዜ ካደው። ቀጥሎም ብርድ ስለ ነበር ጴጥሮስ ከሊቀ ካህናቱ ሎሌዎች ጋር ቆሞ እሳት ይሞቅ ነበር።

ሐና ጌታችንን ስለ ደቀ መዛሙርቱና ስለ ትምህርቱ ሲጠይቀው፣ አጠገቡ ከቆሙት ሎሌዎች አንዱ ሰድቦ ኢየሱስን በጥፊ መታው፤ "ኢየሱስም መልሶ፣ ክፉ ተናግሬ እንደ ሆንሁ ስለ ክፉ መስክር፣ መልካም ተናግሬ እንደ ሆንሁ ግን ስለ ምን ትመታኛለህ? አለው"፤ ዮሐ. 18፥23። ቀጥሎም ሐና ጌታችንን ታስሮ እንዳለ ወደ ቀያፋ ላከው። ለእግዚአብሔር ልጅ በሰው ፊት ለፍርድ መቅረብ ምን ያህል ለውርደት እንደሚዳርግ መገመት ይቻላል፤ ይልቁንም ሐናንና ቀያፋን በመሳሰሉ ሰዎች ፊት መቆም እጅግ የባሰ ነገር ነው!

የሊቀ ካህናቱ ሎሌ የተናገረውን ስድብ ሰምቶ ኢየሱስን በጥፊ ሲመታው ጴጥሮስ አይቶ ይሆንን? ጌታችን ተይዞ እንዳለ ከሐና ወደ ቀያፋ ሲወሰድ ግን ሳያይ አልቀረም። ጌታችን ኢየሱስ በቀያፋ ፊት ሲቆም ጴጥሮስ ለሁለተኛ ጊዜ ጌታውን ካደው። ለሦስተኛ ጊዜ ስለ ኢየሱስ ሲጠየቅ፣ "አንተ ሰው፣ የምትለውን አላውቅም አለ። ያን ጊዜም ገና ሲናገር ዶሮ ጮኸ። ጌታም ዘወር ብሎ ጴጥሮስን ተመለከተው" (ሉቃ. 22፥60-61)፤ ወይም ጌታችን በቀያፋ ፊት በሚቆምበት ክፍል ዞር ብሎ በተከፈተ በር በኩል አሻግሮ ጴጥሮስን ሊያይ ይችል ነበር፣ ወይም አደባባዩን እንደ ገና በሚያቋርጥበት ጊዜ ጌታችን ዞር ሲል ከጴጥሮስ ጋር ዐይን ለዐይን ግጥም ሳይሉ አልቀሩም፤ ያም ሆነ ይህ ደቀ መዝሙሩ እንደዚህ ቅር ሲያሰኘው


በጌታ ዐይን የተሰማው ሐዘንና ሕማም ስለ ታየ፣ የጴጥሮስ ልብ በጥልቀት የተነካበት ወቅት ነበረ፤ “ጴጥሮስም:- ዛሬ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው የጌታ ቃል ትዝ አለው። ጴጥሮስም ወደ ውጭ ወጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ”፤ ሉቃ. 22፥61-62።

ከዚያ በኋላስ ጴጥሮስ ወዴት ሄደ? ምናልባት ሐዋርያው ዮሐንስ የጓደኛው የጴጥሮስ ሐዘን ተሰምቶት ከሊቀ ካህናቱ ግቢ ወጥቶ ጴጥሮስን ወደ ራሱ ቤት ወስዶታል። እዚያም ለጌታችን እናት ለቅድስት ድንግል ማርያም፣ ለወላጆቹ ለዘብዴዎስና ለሰሎሜ (የጌታችን እናት እኅት)፣ እንዲሁም ለቀለዮጳና ለሚስቱ ለማርያም ጌታችን እንደ ተያዘ አወራላቸው። ሁሉም የጎሙስን ሌሊት በጭንቀት አሳለፉ፤ ዐርብ ዕለት ሦስቱ ሴቶች ምናልባት በዘብዴዎስ፣ በቀለዮጳና በዮሐንስ ታግዘው ወደ ከተማዪቱ በመሄድ አሰቃቂ የሆኑትን ድርጊቶች ተከታተሉ። ጴጥሮስ እስከ መጨረሻ ጌታችን የደረሰበትን መከራ ሁሉ መሰከረ ወይስ አልመሰከረም? አንዳንድ ሊቃውንት ተበሳጭቶ፣ እንደ ገና የባሰ ነገር እንዳያደርግም ፈርቶ በዮሐንስ ቤት እንደ ቁየ ያስባሉ፤ ሌሎችም በ1ኛ ጴጥሮስ 5፥1 መሠረት ጴጥሮስ ከሐዋርያት መካከል አንዱና ዋናው በመሆኑ የጌታችንን ሕማምና ሞት ቢያንስ ከሩቅ አይቶአል ብለው ያምናሉ።

ሁለተኛው የዐይን ምስክር:- ከጌታችን ጋር ከተሰቀሉት ወንበዴዎች አንዱ

ከጌታችን ኢየሱስ ጋር የተሰቀሉት ሁለት ወንበዴዎች ነበሩ፤ የተሰቀሉትም አንዱ በቀኝ በኩል፣ ሌላውም በግራ በኩል ኢየሱስም ከሁለቱ የባሰ ወንጀለኛ እንደ ሆነ ተቈጥሮ በመካከላቸው በመሆን ነው። በመጀመሪያ ሁለቱም ወንበዴዎች ጌታችን ኢየሱስን እንደ ሰደቡት ቅዱስ ማቴዎስ ያስረዳናል፤ ማቴ. 27፥44። በኋላ ግን ከወንበዴዎች አንዱ ኢየሱስን በቅርብ መመልከት፣ የተናገረውንም መስማት ሲጀምር ሐሳቡ ተለወጠ። ጌታችን ገዦችና ወታደሮችም የሰነዘሩበትን ስድብ በትሕትና እንዴት እንደ ተቀበለ አይቶ፣ “አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው” ብሎ እንዴት እንደ ጸለየ ሰምቶ፣ ኢየሱስን መስደብ ላላቋረጠው ሌላ ወንበዴ፣ “ስላደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ

ነው፤ ይህ ግን ምንም ክፋት አላደረገም” በማለት ወቀሠው። ከጌታችን ራስ በላይ፣ “ይህ የአይሁድ ንጉሥ ነው” የሚለውን ጽሑፍ ባየ ጊዜ፣ የኢየሱስ መንግሥት ከዓለማዊ መንግሥት የተለየ መሆኑን፣ መሞቱም የመጨረሻ ሳይሆን ወደ መንግሥቱ መግባቱን እንደሚያመለክት በእምነት ተረድቶ፣ “ጌታ ሆይ፣ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ አለው። ኢየሱስም:- እውነት እልሃለሁ፣ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው”፤ ሉቃ. 23፥38-43። ይህን በመናገር ጌታችን የመሞቱ ሁለት ታላላቅ ውጤቶች ማለት የጎጢአት ስርየትን ማስገኘትና የገነትን በር ንስሓ ለሚገቡና በእርሱ ለሚያምኑ መክፈት መሆናቸውን አሳወቀ።



1. ማርያም መግደላዊት ከቢታንያ መጣች።
2. ማርያም መግደላዊት፣ ሰሎሜ (የጌታ እናት እኅት)፣ ዮሐንስ (የሰሎሜ ልጅ) እና የቀለዮጳዋ ማርያም ወደ መስቀሉ ቀረቡ! ሌሎች ዘመዶችና መልካምን የሚመኙ ሁሉ (ዮሐና እና ሶስና ጭምር) ራቅ ብለው ቆሙ።
3. ዮሐንስና ሰሎሜ የጌታን እናት በከተማው ውስጥ ወደሚገኘው ቤታቸው ይዘዋት ሄዱ።

ሦስተኛው የዐይን ምስክር:- በኢየሱስ ትይዩ ቆሞ የነበረው የመቶ አለቃ

ይህ ወታደር የሮም ሰራዊት የመቶ አለቃ ሲሆን፣ የስቅለቱ ጠቅላላ ርምጃ በሕጉ መሠረት እንዲፈጸም ኀላፊነት ነበረበት። የጌታችን እናት ቅድስት ድንግል ማርያምና እኅቷ ሰሎሜ፣ መግደላዊት ማርያምና የቀለዮጳ ሚስት ማርያም ሐዋርያው ዮሐንስም በኢየሱስ መስቀል እግርጌ እንዲቆሙ የፈቀደላቸው መቶ አለቃው ሳይሆን አልቀረም።

ጌታችን ነፍሱን በሰጠ ጊዜ መቶ አለቃው፣ "ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ" (ማር. 15÷39፤ ማቴ. 27÷54ን ይመ.)፤ "ይህ ሰው በእውነት (የእግዚአብሔር) ጻድቅ ነበረ" (ሉቃ. 23÷47) ብሎ መሰከረ። የመቶ አለቃው እንደዚህ ብሎ እንዲናገር ያነሣሣው ምን ይሆን? ከወንጌል ጸሓፊዎች ሦስቱ ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ የመቶ አለቃው ስለ ተናገረው የተለያየ ሐሳብ ሰንዝረዋል። ነገር ግን ሁሉም ጌታችን ኢየሱስ ነፍሱን በሰጠ ጊዜ በታላቅ ድምፅ መጮኹን ይናገራሉ፤ "ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱን ተወ" (ማቴ. 27÷50)፤ "ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ ነፍሱንም ሰጠ" (ማር. 15÷37)፤ "ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ:- አባት ሆይ፣ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ"፤ ሉቃ. 23÷46።

የተሰቀለ ሰው ሲሞት በታላቅ ድምፅ መጮኽ በጣም ያልተለመደ ነገር ነበረ። ቅዱስ ማርቆስ፣ "በዚያም በአንጻሩ የቆመ የመቶ አለቃ እንደዚህ ጮኾ ነፍሱን እንደ ሰጠ ባየ ጊዜ:- ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ" (ማር. 15÷39) በማለት እንዲመሰክር ያነሣሣው በተለይ የጌታችን አሟሟት መሆኑን ያሳያል። የመቶ አለቃው ብዙ ሰዎች ተሰቅለው ሲሞቱ አይቷል። የተሰቀሉ ሰዎች ነፍስ የምታልፈው ረጅም ሰዓት፣ ይልቁንም እስከ ሁለት ወይም እስከ ሦስት ቀን ድረስ ሲሠቃዩ ከመቈየታቸው የተነሣ ከዛሉና ኀሊናቸውን ከሳቱ በኋላ መሞታቸው የተለመደ መሆኑን የመቶ አለቃው ብዙ ጊዜ ሳያረጋግጥ አልቀረም። በተጨማሪም የመቶ አለቃው የመገረፍን አሰቃቂ ውጤት ያውቅ ነበር፤ ከገዢው ቤተ መንግሥት እስከ ቀራንዮ ድረስ ጌታችን መስቀሉን ተሸክሞ ሲሄድ፣ በኋላም በእርሱ ፈንታ ሌላ ሰው ተገድዶ እንደ ተሸከመለት ሳያይ አልቀረም። ታዲያ፣ ይህን

መከራ ሁሉ የተቀበለ ሰው ሲሞት በታላቅ ድምፅ እንዴት መጮኽ ቻለ? ጩኸቱም የድል አድራጊ እንጂ የተሸነፈ ሰው ጩኸት አልነበረም፤ የሰውየው ጎይል አምላካዊ ጎይል መሆን አለበት ብሎ ስላሰበ፣ "በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ" ብሎ ተናገረ። ይህን በተናገረ ጊዜ፣ በመንገድ የሚያልፉት፣ "ቤተ መቅደስን የምታፈርስ በሦስት ቀንም የምትሠራው፣ ራስህን አድን፤ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ" እያሉ የናዝሬቱ ኢየሱስን ሲሰድቡት ሰምቶ ነበር። የመቶ አለቃው ስለ አይሁድ መሲሕ ምን ያህል እንደ ተረዳ አናውቅም። በአረማዊ አነጋገር ከሮማውያን አማልክት ኢየሱስ የተወደደ መሆኑን ለመናገር ይፈልግ ይሆን? አይሁድ ቀደም ሲል ካፈዙበት አኳያ ሲታይ ቅዱስ ማቴዎስ የመቶ አለቃው ኢየሱስ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መመስከሩን እንድናስተውል የፈለገ ይመስላል። በቅዱስ ሉቃስ፣ "ይህ ሰው በእውነት ጻድቅ ነበረ" ተብሎ የተጻፈው የመቶ አለቃው የተናገረውን ምስክርነት ደግሞ "የእግዚአብሔር ጻድቅ ነው" ማለት ይቻላል። የእግዚአብሔር ልጅና የእግዚአብሔር ጻድቅ ሁለቱም መሲሑን የሚያመለክቱ ሐረጎች ናቸው። ጌታችን ከሐዋርያቱ ጋር ፊልጶስ ቂሣርያ በተባለው አገር በነበረ ጊዜ፣ እግዚአብሔር አብ ለጴጥሮስ ኢየሱስ፣ "ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ" መሆኑን (ማቴ. 16÷16) እንደ ገለጠለት ሁሉ፣ ለመቶ አለቃውም ሳይገልጥለት አልቀረም።

ይሁን እንጂ የመቶ አለቃውን ያስደነገጡት፣ ጌታችን በሞተበት ጊዜ የተከሠቱ አስደናቂ ነገሮች ነበሩ። ከቀኑ ሰድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ላይ ጨለማ እንደ ነበረ ተጽፎአል። ቅዱስ ማቴዎስ፣ ጌታችን ነፍሱን አሳልፎ በሰጠበት ወቅት የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች እንደ ተቀደደ ሲነግረን፣ "ምድር ተናወጠች፤ ዐለቶችም ተሰነጣጠቁ፤ መቃብሮች ተከፈቱ፤ እንቅላፍተው የነበሩትም ብዙዎች ቅዱሳን ተነሡ፤ ከመቃብርም በመውጣት ከኢየሱስ ትንሣኤ በኋላ ወደ ቅድስት ከተማ ገብተው ለብዙዎች ታዩ።" የመቶ አለቃውና ዐብረውት ኢየሱስን ይጠብቁት የነበሩት የመሬት መናወጡንና የሆነውን ነገር ሁሉ ባዩ ጊዜ እጅግ ፈሩ፤ ከዚያም፣ "በእውነት

የእግዚአብሔር ልጅ ነበር!” ብለው እንደ ተናገሩ አመልክቶአል፤ ማቴ. 27፥51-54 አ.መ.ት.።

ምንም እንኳ ድንጋጤና ፍርሀት ቢሰማውም የመቶ አለቃው ስለ አያቸው ክሥተቶች እግዚአብሔርን እንዳመሰገነ ቅዱስ ሉቃስ ይነግረናል፤ ሉቃ. 23፥47። ቅዱስ ማርቆስ በመቶ አለቃው አማካይነት ጌታችን ኢየሱስ በእውነት እንደ ሞተ ይፋ መግለጫ ይሰጠናል፤ “የአርማትያሱ ዮሴፍ በድፍረት ወደ ጲላጦስ ሄዶ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው። ጲላጦስም እንዲህ በቶሎ መሞቱን ሲሰማ ተደነቀ፤ የመቶ አለቃውንም ጠርቶ ከሞተ ምን ያህል ጊዜ እንደ ሆነ ጠየቀው፤ መሞቱንም ከመቶ አለቃው ካረጋገጠ በኋላ ሥጋውን ለዮሴፍ ሰጠው”፤ ማር. 15፥43-45 አ.መ.ት.።

በሕማማት ጊዜ እግዚአብሔር አብ የዓለምን ኀጢአት በሚሸከመው በልጁ በጌታችን ኢየሱስ ሥጋ ላይ ይህ ሁሉ መከራ እንዲደርስ ቢፈቅድም፣ ተግባሩን ከፈጸመ በኋላ ወዲያው ወደ ክብሩ ሲመልሰው እናያለን።

አራተኛው የወይን ምስክር:- ሐዋርያው ዮሐንስ

ጌታችን ኢየሱስ ይወደው የነበረው ዮሐንስ በመስቂሉ አጠገብ ቆሞ እንደ ተገኘ ሐዋርያው ዮሐንስ ራሱ ያስረዳናል፤ 19፥26። ልዩ ልዩ የወይን ምስክር ዝርዝሮች መኖራቸውን የሚያረጋግጡ ፍንጮች ይገኛሉ፤ ለምሳሌ፣ በመስቀሉ ላይ የተንጠለጠለው ጽሑፍ በአራማይክ፣ በላቲን በግሪክም እንደ ተጻፈ ከወንጌል ጸሓፊዎች ዮሐንስ ብቻ ይነግረናል፤ የጌታችንን ልብስ የሚመለከተውም ሌላው ማረጋገጫ ነው። አራቱ የወንጌል ጸሓፊዎች ኢየሱስን የሚጠብቁት ወታደሮች ዕጣ በመጣል ልብሱን እንደ ተከፋፈሉት ሲገልጹ፣ ሐዋርያው ዮሐንስ ለእያንዳንዱ አንድ ልብስ እንዲደርስ ለአራት እንደ ተከፋፈሉት ለማመልከት፣ “እጀ ጠባቡም ከላይ እስከ ታች አንድ ወጥ ሆኖ ያለ ስፌት የተሠራ” (ዮሐ. 19፥23 አ.መ.ት.) ስላለ እንዳይቀደድ ከአራቱ ወታደሮች ለየትኛው መድረስ እንደሚችል ዕጣ እንዲጣል ተወሰነ። እንደዚህ በማድረጋቸውም በመዝ. 21(22)፥18 የተጻፈው የትንቢት ቃል እንደ ተፈጸመ ዮሐንስ ብቻ ያሳስባል። ቀጥሎም፣ የወይን ምስክር

በመሆን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እነማን ቆመው እንደ ነበር ይዘረዝራል፤ ይኸውም፣ “እናቱ፣ የእናቱም እኅት፣ የቀለዮጳም ሚስት ማርያም፣ መግደላዊትም ማርያም” ነበሩ፤ ዮሐ. 19፥25። ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር በኢየሱስ አጠገብ እንደ ቆመ በመግለጽ በተለመደው አጻጻፍ እርሱ ራሱ መገኘቱን አመልክቷል። ሦስቱ የወንጌል ጸሓፊዎች ከሩቅ ቆመው ስለ ነበሩ ሰዎች ሲጽፉ፣ ሐዋርያው ዮሐንስ ብቻ ጌታችን ለእናቱና ለእርሱ ምን እንደ ተናገረ ሰማ፤ “ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን:- አንቺ ሴት፣ እነሆ ልጅሽ አላት። ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን:- እናትህ እነኋት አለው። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት”፤ ዮሐ. 19፥26-27።

ቀጥሎም ሐዋርያው ዮሐንስ ጌታችን ኢየሱስ እንደ ተናገረው አድርጎ፣ እናቱን ቅድስት ድንግል ማርያምን ወዲያውኑ ወደ ቤቱ ወሰዳት፤ እኅቷም ሰሎሜ (የዮሐንስ እናት) ዐብራ ሳትሄድ አልቀረችም። ስለዚህ ዮሐንስ ጌታችን በመስቀል ላይ ሳለ፣ “አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው” (ሉቃ. 23፥34) በማለት አሳልፈው ስለ ሰጡት ሲጸልይ የተናገረውን፣ “እውነት እልሃለሁ፣ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ” (ሉቃ. 23፥43) ብሎ ንስሓ ለገባው ወንበዴ የሰጠውን የተሰፋ ቃልና የሰውን ኀጢአት በተሸከመበት ጊዜ አብ ከእርሱ ዘወር በማለቱ፣ “ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ?... አምላኬ አምላኬ ስለ ምን ተውኸኝ?” (ማቴ. 27፥46) የሚለውን በሐዘን ጮኾ ያሰማውን ቃል ያልሰማ ይመስላል፤ በኋላም ጌታችን ሲቀበር በተመለከቱት ሴቶች መካከል የሰሎሜ ስም ያልተጠቀሰበት ምክንያት፣ ከጌታችን እናት ጋር በቤት ስለ ቈዩ ሊሆን ይችላል (ዮሐ. 19፥25 እና ማር. 15፥47 ይመ.)።

ሐዋርያው ዮሐንስ ወደ መስቀሉ የተመለሰበት ወቅት፣ ጌታችን በሐዘን ከጮኸ በኋላ ይመስላል። ማቴዎስና ማርቆስ አንድ ሰው በሰፍነግ የሞመጠጠ የወይን ጠጅ በዘንግ ሰክቶ እንዲጠጣው ለኢየሱስ እንዳቀረበለት ይነግሩናል። ዮሐንስ ግን ቅርብ ስለ ነበረ፣ የሞመጠጠ ወይን ጠጅ የተሞላበትን ዕቃ አየ፤ ሰፍነጉ የተሰካበት ዘንግ የሂሶጵ ዘንግ መሆኑን አየ፤ ዮሐ. 19፥29፤ ማቴ. 27፥48፤ ማር. 15፥36።

ሌሎቹ የወንጌል ጸሐፊዎች ጌታችን በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱን እንደ ሰጠ ሲያስረዱን፣ ዮሐንስ ግን፣ ጌታችን ሲጮኽ ምን እንዳለ ይገልጣል፤ "ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ:- ተፈጸመ አለ፣ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ"፤ ዮሐ. 19፥30። ይህ አሟሟት ድል ያደረገ እንጂ የተሸነፈ ሰው አሟሟት አልነበረም።

ስለ ጌታችን ሞት የተጻፈው የሚቀጥለው የዐይን ምስክር ቃል በዮሐንስ ወንጌል ላይ ብቻ ተጽፎ ይገኛል። ሐዋርያው ዮሐንስ የመሰከረውን አሁን እንመልከት፤ "ዕለቱ ለሰንበት መዘጋጃ ቀን ነበር። አይሁድ፣ የተሰቀሉት ሰዎች ሬሳ በሰንበት ቀን በመስቀል ላይ እንዳይውል ስለ ፈለጉና ያም የተለየ ሰንበት ስለ ነበር፣ የተሰቀሉት ሰዎች ጭናቸው ተሰብሮ በድናቸው እንዲወርድ ጲላጦስን ለመኑት። ስለዚህም ወታደሮቹ መጥተው ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሎ የነበረውን የመጀመሪያውን ሰው ጭን ሰበሩ፤ ደግሞም የሌላውን ሰው ጭን ሰበሩ። ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን ሞቶ ስላገኙት ጭኖቹን አልሰበሩም፤ ነገር ግን ከወታደሮቹ አንዱ የኢየሱስን ጐን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውሃ ፈሰሰ። ይህን ያየው ሰው ምስክርነቱን ሰጥቷል፤ ምስክርነቱም እውነት ነው፤ እውነትን እንደሚናገርም ያውቃል፤ እናንተም እንድታምኑ ይመሰክራል። ይህም የሆነው፣ መጽሐፍ፣ 'ከዐጥንቱ አንድም አይሰበርም' ያለው እንዲፈጸም፣ ሌላውም መጽሐፍ፣ 'የወጉትም ያዩታል' ስለሚል ነው"፤ ዮሐ. 19፥31-37 አ.መ.ት.።

በዚህ ምስክርነት ውስጥ እውነትም ምስጢርም አለበት። ዮሐንስ የመሰከረበትን የጌታችንን የመሞት እውነተኛነት በሦስት ዐይነት ያረጋግጣል:-

<u>አንደኛ</u>፤ በብሉይ ኪዳን በመዝ. 33(34)፥20 እና በዘካ. 12፥10 የተጻፉትን የትንቢት ቃሎች እንደ ተፈጸሙ በማሳየት።

<u>ሁለተኛ</u>፤ በዘፀ. 12፥1-11 ስለ ፋሲካ በግ የተሰጠው ምሳሌ በክርስቶስ መፈጸሙን በመግለጥ፤ ከፋሲካ በግ አንድም ዐጥንት መሰበር አልነበረበትምና፤ ዘኍ. 9፥12።

<u>ሦስተኛ</u>፤ የኢየሱስን የጐን መወጋት በመንገርና ጌታችን በእውነት እንደ ሞተ በሕክምና ደረጃ የታወቀ ምልክትን በመስጠት። ጌታ ኢየሱስ ከሙታን እንደ ተነሣ ይረጋገጥ ዘንድ ስለ መሞቱ የማያጠራጥር ማስረጃ ያስፈልጋል።

ከዓመታት በኋላ ሐዋርያው ዮሐንስ በጌታችን ላይ ስለ ደረሰው መከራ ሲያሰላስል፣ የጐኑ መወጋት የተለየ ትርጉም እንዳለው ያስረዳናል፤ ከተወጋው የጌታችን ጐን የፈሰሰው ውሃና ደም፣ ጌታችን በምድር ላይ የነበረውን አገልግሎት በጥምቀቱ እንደ ጀመረ ፍጻሜ ላይ የደረሰውም በሞቱ እንደ ሆነ ልንረዳ እንችላለን፤ 1ዮሐ. 5፥6። ከጌታችን ጐን የፈሰሰው ውሃና ደም በሞቱ ያስገኘልንን ንጽሕናና ዕርቅ ያሳስበናል፤ 1ዮሐ. 1፥7፤ ሮም 3፥25።

ለ. የክርስቶስን መቀበር ያዩ የዐይን ምስክሮች

አንባቢው በቀላሉ እንዲያነጻጽራቸው በአራቱ ወንጌላት ክርስቶስ ስለ መቀበሩ የተጻፉ ዐጫጭር ዘገባዎችን በአንድነት እናቀርባለን:-

ማቴዎስ 27፥57-61

በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለ ጠጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ፣ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበረ ይኸውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው። ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ። ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንጹሕ በፍታ ከፈነው፣ ከዐለት በወቀረው በዐዲሱ መቃብርም አኖረው፣ በመቃብሩም ደጃፍ ታላቅ ድንጋይ አንከባሎ ሄደ። መግደላዊት ማርያምም ሁለተኛዪቱም ማርያም በመቃብሩ አንጻር ተቀምጠው በዚያ ነበሩ።

ማርቆስ 15፥42-47

አሁንም በመሸ ጊዜ የሰንበት ዋዜማ የሆነ የማዘጋጀት ቀን ስለ ነበረ፣ የከበረ አማካሪ የሆነ የአርማትያስ ዮሴፍ መጣ፣ እርሱም ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠባበቅ ነበር፤ ደፍሮም ወደ ጲላጦስ ገባና የኢየሱስን ሥጋ ለመነው። ጲላጦስም አሁኑን እንዴት ሞተ ብሎ ተደነቀ፤ የመቶ አለቃውንም ጠርቶ ከሞተ ቈይቶአልን? ብሎ ጠየቀው፤ ከመቶ አለቃውም ተረድቶ በድኑን ለዮሴፍ ሰጠው። በፍታም ገዝቶ አውርዶም በበፍታ ከፈነው ከዐለትም በተወቀረ መቃብር አኖረው፣ በመቃብሩ ደጃፍም ድንጋይ አንከባለለ። መግደላዊትም ማርያም የዮሳም እናት ማርያም ወዴት እንዳኖሩት ይመለከቱ ነበር።

ሉቃስ 23፥50-56	ዮሐንስ 19፥38-42
እነሆም፤ በጎና ጻድቅ ሰው የሸንጎ አማካሪም የሆነ ዮሴፍ የሚባል ሰው ነበረ ይህም በምክራቸውና በሥራቸው አልተባበረም ነበር፤ አርማትያስም ከምትባል ከአይሁድ ከተማ ሆኖ እርሱ ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠባበቅ ነበር። ይኸውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው፤ አውርዶም በተልባ እግር ልብስ ከፈነው፥ ማንም ገና ባልተቀበረበት ከዐለትም በተወቀረ መቃብር አኖረው። የመዘጋጀት ቀንም ነበረ፤ ሰንበትም ሊጀምር ነበረ።	ከዚህም በኋላ አይሁድን ስለ ፈራ በስውር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የነበረ የአርማትያስ ዮሴፍ የኢየሱስን ሥጋ ሊወስድ ጲላጦስን ለመነ፤ ጲላጦስም ፈቀደለት። ስለዚህም መጥቶ የኢየሱስን ሥጋ ወሰደ። ደግሞም አስቀድሞ በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ የነበረ ኒቆዲሞስ መቶ ንጥር የሚያህል የከርቤና የእሬት ቅልቅል ይዞ መጣ። የኢየሱስንም ሥጋ ወሰደው እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ ከሽቱ ጋር በተልባ እግር ልብስ ከፈኑት። በተሰቀለበትም ስፍራ አትክልት ነበረ፥ በአትክልቱም ማንም ገና ያልተቀበረበት ዐዲስ መቃብር ነበረ። ስለዚህ መቃብሩ ቅርብ ነበረና ስለ አይሁድ ማዘጋጀት ቀን ኢየሱስን በዚያ አኖሩት።

በስም የተጠቀሱ አራት ሰዎች ብቻ ጌታችን ሲቀበር እንደ ተገኙ እናውቃለን። ሁሉም የወንጌል ጸሓፊዎች ከአርማትያስ የመጣውን ዮሴፍን ይጠቅሳሉ፤ ቅዱስ ማቴዎስና ቅዱስ ማርቆስ፤ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛዪቱ (የታናሹ ያዕቆብና የዮሳም እናት) ከመቃብሩ ትይዩ ተቀምጠው ጌታችን የት እንደ ተቀበረ ይመለከቱ እንደ ነበር ያስረዳሉ። በተጨማሪም ሐዋርያው ዮሐንስ በሌሊት ወደ ኢየሱስ የመጣው ኒቆዲሞስ በቀብሩ ዝግጅት እንደ ተሳተፈ ይነግረናል። ከሌሎች ሐዋርያት ይልቅ ኒቆዲሞስን የማወቅ ዕድል የነበረው ሐዋርያው ዮሐንስ ነበረ፤ ኒቆዲሞስ ከአይሁድ አለቆች አንዱ ሲሆን (ዮሐ. 3፥1፤ 7፥50)፣ ዮሐንስ በሊቀ ካህናቱ ቤተ ሰብ ዘንድ የታወቀ እንደ ነበረ አስቀድመን ተገንዝበናል። እንግዲህ ሐዋርያው ዮሐንስ ራሱ በቀብሩ ላይ ይገኝ ይሆን? ጌታችን ኢየሱስ ነፍሱን እስከሚሰጥ ድረስ በመስቀል አጠገብ የቈየው የተወደደው ደቀ መዝሙር ዮሐንስ ለእናቱ ለቅድስት ድንግል ማርያም፤ ልጇ ስለ ተቀበረበት ሁኔታና ቦታ የዐይን ምስክርነት ለመስጠት እንደ ጓጓ መገመት እንችላለን። እንደዚህ እንድንል የሚያደርገንም፤ ከሌሎች የወንጌል ጸሓፊዎች

ይልቅ አንዳንድ የዐይን ምስክር ዝርዝሮች በዮሐንስ ወንጌል ተጽፈው መገኘታቸው ነው፤ ለምሳሌ፤ ኒቆዲሞስ ሽቱ ለመግዛት ወደ ገበያ እንደ ሄደ ብቻ ሳይሆን፤ ምን ዐይነት (የከርቤና የእሬት ቅልቅል)፤ ምን ያህልም ሽቱ (33-34 ኪሎ ግራም) እንደ ገዛ ሐዋርያው ዮሐንስ ይነግረናል፤ ታዲያ፤ ሽቱውን ለመሸከም ሐዋርያው ኒቆዲሞስን ረድቶት ይሆን? ይህን ያህል ከፍተኛ መጠን ያለው ሽቱ በዘመኑ ለንጉሥ ቀብር የሚሆን ተገቢ መጠን ነበረ።

ጌታችን የተቀበረበትን ቦታ በሚመለከት፤ በተሰቀለበት ስፍራ አቅራቢያ የአትክልት ቦታ እንደ ነበረ የሚነግረን ሐዋርያው ዮሐንስ ብቻ ነው፤ "በዔድን አትክልት ስፍራ ጎይላቸውን መጀመሪያ የተቀበሉት ሞትና መቃብር አሁንም በአትክልት ስፍራ ተሸንፈው ይገኛሉ"[8] ተብሎ የተጻፈው የአንድ ሊቅ ሐተታ ሐዋርያው ዮሐንስ ካለው ሐሳብ ጋር ሊስማማ ይችላል። ከማቴዎስ፤ ከማርቆስና ከሉቃስ የምንማረው፤ መቃብሩ ከዐለት ተፈልፍሎ የተሠራ መሆኑን ነው። ማቴዎስ ብቻ ዮሴፍ መቃብሩን ለራሱ አዘጋጅቶት እንደ ነበር ያስረዳናል። ሉቃስና ዮሐንስ፤ በመቃብሩ ውስጥ ማንም ያልተቀበረበት መሆኑን በሚጠቁመው ሐሳብ ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፤ ዮሐንስ መቃብሩ ዐዲስ መሆኑን ጨምሮ ጽፎአል፤ "ሰው ካልተፀነሰበት ድንግል ማሕፀን የተወለደ፤ ሰው ካልተቀበረበት ድንግል መቃብር መውጣት ይገባዋል!"[9] ዮሴፍ ትልቅ ድንጋይ አንከባሎ የመቃብሩን በር እንደ ዘጋው ከማቴዎስና ከማርቆስ እናስተውላለን፤ ሉቃስና ዮሐንስ ስለ ትንሣኤው ዕለት እስከሚናገሩ ድረስ ድንጋዩን አይጠቅሱም።

የአርማትያሱ ዮሴፍ ከማቴዎስ ወንጌል ሀብታም ሰው፤ ከማርቆስ ወንጌል የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠባበቅ የነበረ ክቡር አማካሪ (የተከበረ የሸንጎ አባል)፣ ከሉቃስ ወንጌል በጎና ጻድቅ ሰው፤ ከዮሐንስ ወንጌል አይሁድን ስለ ፈራ ስዉር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር መሆኑን

[8] Matthew Henry's Commentary on the Whole Bible, Marshall Pickering 1967, page 421 New Testament section.
[9] Ibid.

እንማራለን። ስለዚህ የጌታችን ኢየሱስን ሥጋ ለመለመን ወደ ጲላጦስ መሄድ መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ ርምጃ ነበረ።

ሦስቱ የወንጌል ጸሓፊዎች ማቴዎስ፣ ማርቆስና ሉቃስ ዮሴፍ የጌታችንን ሥጋ በበፍታ ወይም በተልባ እግር ልብስ እንደ ከፈነ ሲናገሩ፣ ዮሐንስ ብቻ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ዐብረው፣ "እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ ሽቱ ቀብተው ከተልባ እግር በተሠራ ጨርቅ ከፈኑት" በማለት አቀባበሩን አብራርቶአል። "በኢየሱስ ራስ ላይ ተጠምጥሞ የነበረውን ጨርቅ" ጨምረው እንደ ገለጡም ከም.20፥7 እናውቃለን። አንባቢው፣ በፍጥነት ለጌታችን የተደረገለትን አገናነዝ በአይሁድ ሥርዐት መሠረት ለአልዓዛር ከተደረገለት አገናነዝ ጋር ማነጻጸር ቢፈልግ ዮሐ. 11፥43-44ን ይመልከት። አልዓዛር ማለፊያ ልብሱን እንደ ለበሰ ሳይቀበር አልቀረም፤ በተጨማሪም ፊቱ ብቻ በሻሽ እንደ ተጠመጠመ፣ እግሩ ደግሞ በቀጭን ስስ ጨርቅ እንደ ተጠቀለለ ዮሐንስ ይነግረናል።

ቀጥሎ የወንጌል ጸሓፊዎች ስለ ሴቶች ምን እንደ ጻፉ እንመልከት። ማቴዎስ፣ ጌታችን በተቀበረበት ጊዜ፣ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛዪቱ ማርያም በመቃብሩ አንጻር ተቀምጠው እንደ ነበር ሲገልጽ፣ ማርቆስ ሁለቱም ሴቶች ከመቃብሩ ውጭ ሆነው "ወዴት እንዳኖሩት" ይመለከቱ እንደ ነበር ያስረዳናል። ሉቃስ ከጌታችን ጋር ከገሊላ የመጡት ሴቶች ዮሴፍን ተከትለውት እንደ ሄዱ ይነግረናል፣ ምናልባት ከሁለቱም ጋር ሌሎች እንደ ነበሩ ሉቃስ ሊያውቅ ይችላል ማለት ነው፤ ለምሳሌ፣ እሑድ በሴቶች መካከል የሄሮድስ አዛዥ የኩዛ ሚስት ዮሐና እንደ ተገኘች እናውቃለን (ሉቃ. 24፥10)፤ ከዮሐና ጋር በስም የተጠቀሰችዋ ሶስናም ጌታችንን እንዳገለገለችው ከሉቃ. 8፥3 እንረዳለን። ሰሎሜ እሑድ ከሌሎች ሴቶች ጋር እንደ ነበረች ብናውቅም፣ ከእኅቷ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር የነበረች ይመስላል፤ ስለዚህ እርሷ በቀብሩ ጊዜ በስም አለመጠቀሷ አያስገርምም። ሉቃስ፣ ሴቶቹ የጌታችንን ሥጋ "እንዴት እንዳኖሩት አዩ" ይላል፤ ማለት፣ አንዳንዶች (ዮሐና? ሶስና?) ወደ መቃብሩ ገብተው ጌታችን የተኛበትን ስፍራ ሳያዩ አልቀሩም። ከዚያም በኋላ ተመልሰው በትእዛዙ መሠረት በሰንበት ቀን ዐረፉ፤ ሽቱና ቅባትም አዘጋጁ። ዮሐንስ ለዐላማው

አስፈላጊ ስላልነበረ ጌታችን በተቀበረበት ጊዜ ስለ ነበሩት ሴቶች አይናገርም።

ስለ ጌታችን ቀብርና ትንሣኤ ቅዱስ ማቴዎስ ሲጽፍ አንዱ ዐላማው፣ የጌታችን አስከሬን ስላለመገኘቱ በኢየሩሳሌም የተስፋፋውን ሐሰተኛ ታሪክ ማስወገድ ነው፤ ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው የኢየሱስን አስከሬን ሰርቀው ወስደውታል ይባል ነበርና። ስለዚህ ከወንጌል ጸሓፊዎች ሁሉ ማቴዎስ ብቻ ጲላጦስ ለሊቀ ካህናቱ ስለ ሰጠው ጠባቂዎች፣ ስለ ምድር መናወጥ፣ መልኩ ስለሚያጥበረብረው መልአክ፣ ለሊቀ ካህናቱ ስለ ቀረበው የጠባቂዎች ዘገባ፣ ተኝተው ሳሉ ደቀ መዛሙርት መጥተው አስከሬኑን ሰርቀውታል የሚለውን ወሬ እንዲያሠራጩ ለጠባቂዎች ከሊቀ ካህናቱ ስለ ተሰጠው ጉቦ ይናገራል።

እያንዳንዱ የወንጌል ጸሓፊ ስለ ጌታችን መቀበር መጻፉ እንዴት አስፈላጊ ሆኖ ታየው? ለዚህ ቢያንስ ሦስት ምክንያቶችን ልናቀርብ እንችላለን፤ የመጀመሪያው ምክንያት፣ ጌታችን ስለ ተቀበረ በእውነት እንደ ሞተ የሚያረጋግጥ ማስረጃ መሆኑ ነው። ሁለተኛው ምክንያት፣ መቃብሩ ስለ ጌታችን ትንሣኤ ከሚቀርቡት ማስረጃዎች አንዱ ስለ ሆነ ነው። ሦስተኛው ምክንያት፣ በብሉይ ኪዳን በነቢያት የተጻፈው የትንቢት ቃል መፈጸሙ ነው፤ "ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ" (ኢሳ. 53፥9)፤ "ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራለች" (መዝ. 15(16)፥9)፤ "ዮናስም ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት በዓሣው ሆድ ውስጥ ነበረ"፤ ዮና. 2፥1። ጌታችን ኢየሱስ በነቢዩ ዮናስ የተጻፈው በራሱ እንደሚፈጸም አረጋገጠ፤ "ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፣ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል" ብሎአል፤ ማቴ. 12፥40። ሐዋርያው ጳውሎስም፣ "መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረም" በማለት በነቢያትና በጌታችን የተነገረውን እውነት አስተጋባ፤ 1ቆሮ. 15፥3።

በሚቀጥለው ምዕራፍ፣ በሦስተኛው ቀን በመቃብሩ ቦታ ምን እንደ ተከሠተ በዐይን ምስክሮች የተነገረውን እንመረምራለን።

ምዕራፍ 4

የትንሣኤ ክርስቶስን እውነተኛነት የሚያረጋግጡ ሕያዋን ማስረጃዎች

ከሌላው ነገር ሁሉ ይልቅ ሐዋርያት ስለ ጌታቸው ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ርግጠኛ ማስረጃ የማቅረብ ጽኑ ፍላጎት ነበራቸው፤ ይህንም ማድረግ የፈለጉት በሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ነበር፤ አንደኛው ምክንያት፣ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ለሕዝቡ ሁሉ ሳይሆን ለሐዋርያትና ከእነርሱ ጋር ጎብረት ለነበራቸው ሌሎች ደቀ መዛሙርት ሕያው ሆኖ ራሱን በመግለጥ፣ በእነርሱ ምስክርነት ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ይሆኑ ዘንድ ጌታችን ዐደራ ስለ ሰጣቸው፤ ሁለተኛው፣ እርሱ መሲሕ መሆኑን ከሰጣቸው ማስረጃዎች ሁሉ ይበልጥ የሚያረጋግጠውና የመጨረሻው የእርሱ ትንሣኤ ስለ ነበረ፤ ሦስተኛውም፣ ለቤዛነታችንና ለደኅንነታችን የከፈለው መሥዋዕት ፍሬና ውጤት ሁሉ በትንሣኤው ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው፤ "ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኀጢአታችሁ አላችሁ"፤ 1ቆሮ. 15፥17።

ይሁን እንጂ ወደዚህ ምዕራፍ ዋና ፍሬ ነገር ከመድረሳችን በፊት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ክርስቶስ ስለ ተነሣበት ቀን የተጻፈው በይበልጥ ግልጽ እንዲሆንልን፣ የሚያዘጋጁንን ጥቂት ነጥቦች ማንሣት ያስፈልጋል:-

1. ስለ አንድ የተወሰነ ታሪክ ወይም ከሥተት የተጻፈ መግለጫ ከአንድ በላይ ከሆነ፣ አንዱን ከሌላው ጋር ስናነጻጽርም አንዳንድ ዝርዝር ሐሳቦች የማይስማሙ ቢመስሉን፣ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት መመልከት ይገባናል? በእነዚህ ዝርዝር ነጥቦች ላይ በማተኮር፣ የተወሰኑ ሐያስያን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ጸሓፊዎች፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣንና እውነተኛነት እስከማያምኑ ድረስ እነዚህ ነገሮች ዕንቅፋት ሊሆኑባቸው እንደሚችሉ ያስባሉ። ትሑት የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ግን የጌታውን ትምህርት በሌላ ዐይን መመልከት ነበረበት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ታሪክ ወይም አንቀጽ

ተደጋግሞ የሚገኘው በእግዚአብሔር ፊት ዋና ነገር መሆኑን ዐውቀን የሚያስተምረንን ትምህርት ልብ አድርገን እንድናዳምጥ ነው። በዚህ ዐይነት ተደጋግመው የምናገኛቸው ታሪኮች የተሰጡን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል የሐሳብ መለያየት እንዲፈጠር ሳይሆን፣ እውነቱን በጥልቀት እንድናውቅና ከቀድሞው ይልቅ እንድናስተውል ነው። ስለ ጌታችን ኢየሱስ ትንሣኤ በተጻፈው በእያንዳንዱ መግለጫ እግዚአብሔር በቂ ብርሃንን በመስጠት፣ አእምሯችንን በይበልጥ መክፈት እንደሚፈልግ መረዳት አለብን።

2. የክርስቶስን ትንሣኤ በሚመለከት መገንዘብ የሚያስፈልገን፣ የተሰጡን መረጃዎች ስለ አንድ ውስብስብ ክሥተት የተሰጡ መግለጫዎች እንጂ በፍርድ ቤት የቀረቡ ምስክርነቶች አለመሆናቸውን ነው። እንዲሁም ደግሞ በአርታዒ የተዘጋጁ ሰነዶች አይደሉም፤ ተራ ሰዎች ፈጽሞ ባልተለመደ ሁኔታ ውስጥ ተገኝተው ያደረጓቸውና የተናገሯቸውና ያዩአቸው ስለ ሆኑ፣ በአንድ በኩል ከልብ የሚፈልቁ ስሜታውያን ሐሳቦች የነበሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቍጥጥር ሥር የነበሩ ዘገባዎች ናቸው። የተጻፉት መግለጫዎች ተንኰል አልባ መልክ በእውነት ማመንን የሚያነሣሣ በመሆኑ እውነተኛነታቸውን የሚያረጋግጥ ነገር ነው። ከልዩ ልዩ አቅጣጫ፣ በልዩ ልዩ ወቅትና በልዩ ልዩ ዐይነት ሁኔታ ወደ መቃብሩ የደረሱትን ሰዎች ስሜትና አመለካከት የምናውቅ ቢሆንም፣ በእነርሱ መካከል አንድም ሰው ባዶ የሆነ መቃብርን ይልቁንም ከሙታን የተነሣውን ክርስቶስን ለማየት ከቶ ያሰበ አልነበረም።

እንግዲህ በታሪኩ ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች የተለያዩ በመሆናቸው፣ የወንጌል ጸሓፊዎች የጻፉት ዋናው መልእክት አንድ ዐይነት ቢሆንም፣ በዝርዝር ሲታይ የተለያየ ሊሆን ይችላል፤ በመቃብሩ ስፍራ የተፈጸመውን የሚያዩት በልዩ ልዩ ሰዎች ዐይን ነውና። በተጨማሪም ታሪኩን ሲተርክ እያንዳንዱ የወንጌል ጸሓፊ የራሱ ዐላማ የነበረው ይመስላል፤

<u>ቅዱስ ማቴዎስ</u>፤ 'የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በድኑን ሰረቁት' የሚለውን በኢየሩሳሌም የተሠራጨውን ሐሰተኛ ወሬ መቃወም እንደ ፈለገ

ቀደም ሲል ዐስበናል። ማቴዎስ ወደ ቢታንያ በሸሹት ደቀ መዛሙርት መካከል ሆኖ፣ ከእነርሱ አመለካከት አንጻር ታሪኩን ሳይጽፍ አልቀረም።

<u>ቅዱስ ማርቆስ</u>፤ በሐዋርያው ዮሐንስ ቤት አንድ ላይ ከቅድስት ድንግል ማርያም፣ ከዘብዴዎስና ከቀለዮጳ፣ ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ጋር ሌሊቱን በዚያ ካሳለፉት ሦስት ሴቶች (ሰሎሜ፣ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛዪቱ ማርያም) አመለካከት አንጻር እንደ ጻፈ ይታሰባል። ማርቆስ ታሪኩን በመጀመሪያ የሰማው ከሐዋርያው ጴጥሮስ መሆኑን ልንገምት እንችላለን፤ ሁለቱም በደንብ ይተዋወቁ ነበርና።


<u>ቅዱስ ሉቃስ</u>፤ ሉቃስ በጉልሕ የጻፈው ታሪክ ብልኅ የነበረችዋ ዮሐና በነገረችው መልእክት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል።

<u>ቅዱስ ዮሐንስ</u>፤ ሐዋርያው ዮሐንስ ትኵረት የሚያደርገው በትንሣኤው ታሪክ ላይ ሳይሆን፣ ስለ ትንሣኤው በተሰጡ ማስረጃዎች ላይ ነው፤ ለእርሱ ዐላማ ዋና ዋና ድርሻ የነበራቸው መግደላዊት ማርያም፣ ሐዋርያው ጴጥሮስና ዮሐንስ ራሱ ነበሩ።

<u>ቅዱስ ጳውሎስ</u>፤ በወንጌል ጸሓፊዎች በተጻፉት አራት ዘገባዎች ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የጻፈውን ምስክርነት መጨመር አለብን፤ "እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ:- መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረም፣ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ"፤ 1ቆሮ. 15፥3-4። ሐዋርያው ጳውሎስ በተለይ የክርስቶስ መሞት፣ መቀበርና ከሙታን መነሣት በክርስቲያናዊ እምነት ያላቸውን መሠረታዊ ሰፍራና ይህም ሁሉ በብሉይ ኪዳን የተጻፈው ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን ያሳስበናል።

3. በመግቢያችን መጨረሻ "ትንሣኤ" በዐዲስ ኪዳን ውስጥ ምን ትርጉም እንዳለው በዐጭሩ መመልከት አለብን። በክርስቶስ ዘመን የነበሩ ግሪኮች የሥጋ ትንሣኤን ነቅፈው ከሥጋ ነጻ የወጣው ነፍስ የዘለዓለም ሕያውነት እንደ ነበረው ያምኑ ነበር። ፈሪሳውያንና በአቡቀለምሲስ (ብዙ ምስሎችና ምስክርነቶች ያሉበት) የሚያምኑ አይሁድ የሰው ሥጋ በምድራዊ መልኩ እንደሚነሣ ይጠባበቁ ነበር፤ ለምሳሌ፣ በናይን ከተማ የመበለቲቷ ልጅ ከሞት መነሣት (ሉቃ. 7፥11-15)፤

የኢያኢሮስ ሴት ልጅ መነሣት (ሉቃ. 8፥41-42፥49-56) እና የአልዓዛር መነሣት፤ ዮሐ. 11፥1-44። እነዚህ ሰዎች ቢፈወሱም ሳይለወጡ ስለ ተነሡ ጊዜአቸው ሲደርስ እንደ ገና ሞቱ። ጌታችን ኢየሱስ በትምህርቱ እስከሚገልጠውና በሥጋው በሞትና በትንሣኤ እስከሚያልፍ ድረስ፣ ማንም ስለ ሥጋ መለወጥ አላሰበም ነበር፤ ሉቃ. 20፥34-36፤ 24፥31፥36-43፤ ሐ.ሥ. 1፥9-11ን ይመ.። እንግዲህ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምንፈልገው፣ እስትንፋስ የተመለሰለትን ሰው ሳይሆን፣ ከሙታን የተነሣውን ለዘለዓለም ሕያው የሆነውን ጌታችን ኢየሱስን ነው። በሚከተሉት ምዕራፎች ውስጥ እንደምናየው፣ የጌታችንን፣ የራሳችንንም ትንሣኤ በትክክል ለማስተዋል በሁለቱም ሁኔታዎች መካከል ያለውን ልዩነት እንድንረዳ ያስፈልጋል።



1. መቃብሩ በድንጋይ ተዘጋ፤ የቤተ መቅደስ ጠባቂዎችም በሮማውያን ወታደሮች በመታገዝ መቃብሩን መጠበቅ ጀመሩ።
2. የዕለተ ሰንበት ጊዜ ወደ መገባደጃው ሲቃረብ፣ ቀለዮጳና ሚስቱ ከዮሐንስ ቤት ወጥተው ቢታንያ ከሚገኙት ከዘጠኙ ደቀ መዛሙርት ጋር ለመገናኘት ከግርያም መግደላዊት ጋር ሄዱ።
3. ሰንበት ካለፈ በኋላ ሰሎሜ ከኢየሩሳሌም ገበያ የሚቀባ ሽቱ ገዛች።

በሐሳባችን በሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን በማለዳ ጌታችን ኢየሱስ ወደ ተቀበረበት መቃብር ከመሄዳችን በፊት፣ ቅዳሜ ማታ የነበረውን ሁኔታ ለመመርመር ብንሞክር መልካም ነው፤ ለምሳሌ፣ ወደ መቃብሩ የሄዱ የተለያዩ ምስክሮች ከየት ተነሥተው የት እንደ ደረሱ ብናውቅ፣ በአራቱ ታሪኮች መካከል ላይ ላዩን የሚታዩ የማይስማሙ ዝርዝር ሐሳቦች ይጠፉ ይሆን? ስለ ቅዳሜ ማታ እንዲሁ ደግሞ በሚከተለው ምዕራፍ ስለ ዕለተ ትንሣኤ ከቀረቡት አስተሳሰቦች አብዛኞቻቸው በJohn Wenham "Easter Enigma" በሚል ርእስ በተጻፈው መጽሐፍ ሐሳብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው።

ዐርብ ምሽት ላይ በኢየሱስ ቀብር የተገኙት ሴቶች፣ "በሰንበትም እንደ ትእዛዙ ዐረፉ"፤ ሉቃ. 23፥56። በእነርሱ መካከል የሄሮድስ አዛዥ የኩዛ ሚስት ዮሐናና ምናልባት ጓደኛዋ ሶስና ነበሩ፤ ሉቃ. 8፥3፤ 23፥55፤ 24፥10። እነዚህ ሴቶች ሁለቱም ሀብታሞች በመሆናቸው ከንብረታቸው ለእሑድ ማለዳ የሚያስፈልጋቸውን ሽቱና ቅባት ማዘጋጀት ሳይችሉ አልቀሩም። ሁለቱም በሄሮድስ ቤተ መንግሥት ሌሊቱን ለማሳለፍ ስላሰቡ፣ እሑድ ማለዳ ወደ መቃብሩ ሄደው እዚያ ከሌሎች ሦስት ሴቶች ጋር ለመገናኘት ቢወስኑ አያስገርምም።

ቅዳሜ ዕለት ምንም እንኳ የሰንበት ቀን ቢሆንም፣ የአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች የኢየሱስን ጎይልና ከሦስት ቀን በኋላ ከሙታን እንደሚነሣ የተናገረውን ቃል ስለ ፈሩ ወደ ጲላጦስ ሄደው መቃብሩ እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ ይጠበቅ ዘንድ ትእዛዝ እንዲሰጥ ጠየቁት። ከራሳቸው የቤተ መቅደስ ጠባቂዎች በተጨማሪ ጲላጦስ የተወሰኑ የሮም ጠባቂዎችን ያዘዘ ይመስላል። የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ሄደው መቃብሩን በማኅተም አሽገው አስጠበቁት።

በሰንበት ቀን መጨረሻ ላይ (12 ሰዓት ምሽት ሲሆን)፣ በዮሐንስ ቤት የነበሩ ሁሉ በተለይ ስለ ሁለት ጕዳዮች ሳይጨነቁ አልቀሩም፤ አንደኛው ነገር፣ ገና የቀራቸውን ሽቱና ቅባት ማታ ከሚከፈተው ገበያ መግዛቱ ነው። ሀብታም የነበረችዋ መግደላዊት ማርያም በቢታንያ ከምትኖረዋ ከአልዓዛርና ከማርታ እኅት ጋር አንድ ከሆነች፣ የነበራትን

ሽቱ በኢየሱስ ራስ ላይ አፍስሳ ከሌሎቹ ጋር የራሷን ድርሻ ለመክፈል ሳትፈልግ አልቀረችም። ከቢታንያዋ ማርያም የተለየች ሌላ ማርያም ከሆነች፣ በሚገዛ ዕቃ መሳተፍ የምትፈልግ መሆኗ ግልጽ ነው። ገና ወደ መቃብሩ ያልሄደችው፣ ከሌሎች ይልቅ የኢየሩሳሌምን ገበያ የምታውቀው ሰሎሜ በመሆኗ እርሷ ለሦስቱ ሴቶች የሚያስፈልገውን እንድትገዛ ተስማምታ ሊሆን ይችላል።

ሁለተኛው ነገር፣ በቢታንያ ከቄዩት ዘጠኝ ሐዋርያት ጋር መገናኘት ነው፤ ሁለት ቀን ሙሉ ስለ እነርሱ ምንም አልተሰማምና። መግደላዊት ማርያም የቢታንያዋ ማርያም ከሆነች ወደ ቤት መሄድ እንደምትፈልግ ግልጽ ነው፤ የቀለዮጳና የሚስቱ የማርያም ልጅ ታናሹ ያዕቆብ በቢታንያ ይገኝ ስለ ነበር፣ ለመሄድ ብትናፍቅ አያስገርምም። ሰሎሜም ምንም እንኳ እዚያ ልጅ (ያዕቆብ) ቢኖራትም፣ በዚያን ጊዜ ለጌታችን እናት ለእኅቷ ለቅድስት ድንግል ማርያም ቅድሚያ መስጠት ሳትፈልግ አልቀረችም። የሆነው ሆኖ ሁለቱም ማርያሞች ለመሄድ እንደ ወሰኑ ልናስብ እንችላለን፤ ሴቶች በመሆናቸው በምሽት ጊዜ ብቻቸውን እንዳይሄዱ የሁለተኛዪቱ ማርያም ባለቤት ቀለዮጳ ቢሸኛቸው አያስገርምም።

እነዚህ ዝርዝር ሐሳቦች አመክንዮታውያን የሆኑ ግምቶች ብቻ መሆናቸውን ማስታወስ አለብን፤ በታሪኩ ውስጥ የሚሳተፉ ሰዎች ሌላ ሐሳብ ቢኖራቸውም፣ ዋናውን ታሪክ የሚለውጥ አይሆንም። በዚህ ግምት መሠረት ብንቀጥል የቅዳሜ ማታ ሁኔታ የሚከተለው መልክ ሊኖረው ይችላል:-

<u>በቢታንያ የቄዩ ሰዎች</u>፤ ዘጠኙ ሐዋርያት፣ በኋላም ቀለዮጳና ሚስቱ ማርያም፣ መግደላዊት ማርያምም፤

<u>በዮሐንስ ቤት የቄዩ ሰዎች</u>፤ የጌታችን እናት ቅድስት ድንግል ማርያም፣ ዘብዴዎስና ሰሎሜ፣ ሐዋርያው ጴጥሮስና ሐዋርያው ዮሐንስ፣ እነርሱም ሁለቱ ማርያሞችና ቀለዮጳ እሑድ ማለዳ እንዲመለሱ ይጠባበቁ ነበር፤

<u>ሄሮድስ አንቲጳስ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ በኖረበት በመቃብያን ግቢ ውስጥ የቄዩ ሰዎች</u>፤ ዮሐናና "ሶስና"፣ ብቻቸውን ወደ መቃብሩ ለመሄድ ተስማምተው ነበር፤

በአርማትያሱ በዮሴፍ የአትክልት ስፍራ የተገኙ ሰዎች፤ ሁለት የዘብ ቡድኖች ጥበቃውን የጀመሩ ሲሆን፣ አንዱ ከአይሁድ የቤተ መቅደስ ጠባቂዎች፣ ሌላው ደግሞ ከሮም ወታደሮች የተመደበ የጥበቃ ቡድን ነው።

በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ለሚፈጸመው ታላቅ ክሥተት መድረኩ አሁን ተዘጋጅቷል። ማለዳ ወደ መቃብሩ የሚሄዱትን ልዩ ልዩ ሰዎች እንድንሸኛቸው፣ ያዩትን እንድናይ፣ የሰሙትን እንድንሰማ፣ የተሰማቸው እንዲሰማን፣ በኋላም ከሙታን ከተነሣው ከጌታችን ኢየሱስ ጋር እስከምንገናኝ ድረስ ስለ ሆነው ነገር ሁሉ እንድናሰላስል እግዚአብሔር ይጋብዘናል። በአራቱ የወንጌል ጸሓፊዎች የተጻፉትን ታሪኮች ማዋሐድ ይቻል ዘንድ አንባቢው በይበልጥ እንዲመረምር፣ ስለ ትንሣኤ ክርስቶስ በአራቱ ወንጌላት ተጽፈው የሚገኙ ታሪኮችን ከተሰማሚ ሐተታ ጋር ጐን ለጐን አስቀምጠናቸዋል።

በአራቱ ወንጌላት ጸሓፊዎች ስለ ትንሣኤ ክርስቶስ የተጻፉትን በተከታታይነት ለመመርመር ስንሞክር፣ ስድስት ነገሮችን በጥንቃቄ መመልከት አለብን፤ እነርሱም የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የሴቶች ወደ መቃብሩ መድረስ፣ በመቃብር ውስጥ የተሰጠው መልአካዊ መገለጥ፣ ሴቶቹ መልእክቱን ሰምተው ከመቃብሩ መሸሻቸው፣ የጠባቂዎች መመስከርና በጉቦ መደለል እንደዚሁም ጴጥሮስና ዮሐንስ የበፍታ ልብሱን አቀማመጥ መመልከታቸው ናቸው።

1. የመሬት መንቀጥቀጥ

ማቴ. 28፥1-4

"በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛዪቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ። እነሆም የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤	ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ። መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ። ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ።"

በቅዱስ ማቴዎስ የተጻፈውን ታሪክ መጀመሪያ ስናነብ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ የተነሣው ሴቶች ከደረሱ በኋላ ይመስላል፤ መልአኩም ለሴቶች መልእክቱን ሲናገር፣ ጠባቂዎቹ በመሬት ላይ ተጋድመው

እንደ ነበር ልናስብ እንችላለን። ማቴዎስ ግን ሁኔታውን እንደዚህ የምናስተውለው ስለ መሆናችን ይጠራጠራል። እግዚአብሔር ትንሣኤ ክርስቶስን ለሕዝቡ ሁሉ ሳይሆን ለተመረጡ ሰዎች ብቻ እንደ ገለጠ ሐዋርያው ጴጥሮስ ያሳስበናል፤ ሐ.ሥ. 10፥41። ታዲያ ከሁሉ ቀድመው የሰሙት በክርስቶስ የማያምኑ አይሁዳውያን ጠባቂዎችና አረማዊ የነበረ ሮማዊ ወታደር እንዲሆኑ እግዚአብሔር እንዴት ፈቀደ? ቅዱስ ማቴዎስ፣ ሴቶቹ ከመድረሳቸው ጥቂት ጊዜ በፊት ወታደሮቹ ወደ አእምሯቸው ተመልሰው ከአትክልት ስፍራ እንደ ወጡ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ሴቶቹ የሰሙትን ለኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ለመናገር ሲሄዱ፣ ወታደሮቹ ከካህናት አለቆች ጋር መገናኘታቸውን እንድንረዳ ሳይፈልግ አይቀርም። የመሬት መንቀጥቀጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በልዩ ልዩ ጊዜ የእግዚአብሔርን መኖርና መሥራት ያመለክታል፤ ዘፀ. 19፥18-19፤ መሳ. 5፥4። ጌታችን ኢየሱስ ነፍሱን በሰጠበት ወቅት የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከላይ ወደ ታች ሲቀደድ፣ "ምድርም ተናወጠች፣ ዐለቶችም ተሰነጠቁ መቃብሮችም ተከፈቱ፤ ተኝተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ" ብሎ የጻፈው ቅዱስ ማቴዎስ ነው፤ 27፥51-52። ትንሣኤ ክርስቶስ መለኮታዊ ተአምር የተፈጸመ መሆኑን ያረጋግጣል፤ መልአኩ ድንጋዩን ያንከባለለው፣ ትንሣኤውን እንዲያረጋግጡ ምስክሮች ወደ ውስጥ ገብተው ይመለከቱ ዘንድ እንጂ ሕያው የሆነ ክርስቶስ እንዲወጣ አልነበረም። "መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ" ሆኖ (28፥3)፣ በድንጋዩ ላይ የተቀመጠበት ምክንያት ጠባቂዎቹን ለማስፈራት ቢሆንም፣ በኋላ ወደ መቃብሩ የገባው፣ ቦታውን ለማየት እስከማይደፍሩ ድረስ ሴቶቹን እንዳያስደነግጣቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ቅዱስ ማቴዎስ የታሪኩን ተከታታይነት በግልጽ ለምን አልጻፈም ብለው ለሚጠይቁ ሰዎች የሚከተሉትን አስተሳሰቦች ማቅረብ ይቻላል:-

- ግሪኮች ስለ ነገሮች ተከታታይነት፣ ስለ ጊዜያትም ብዙ አልተቸገሩም። እኛ ቅደም ተከተሉን በትክክል መጻፍ ብንፈልግ፣ "እነሆም፣ የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ


ሆኖ ነበር፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀምጦ ነበር” ማለት ብንችልም፣ የግሪክ ግሶች ብዙ ጊዜ ልዩነቱን አያመለክቱም።

- በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩ የታሪክ ጸሓፊዎች እንዲሁም ደግሞ በብሉይ ኪዳን ዘመን የኖሩ የዕብራውያን የታሪክ ጸሓፊዎች ብዙ ጊዜ ባለፈውና ባሁኑ ጊዜ ክሥተቶች መካከል ወዲያና ወዲህ ይሉ ነበር፤ የዘመናዊ የታሪክ ጽሑፍ ልዩ ልዩ ሕጎችና ሐቆች ለእነርሱ አይታወቁም ነበርና። ስለዚህ የመጀመሪያዎቹ አንባብያን የነበራቸውን አመለካከት በጥንቃቄ እስከምንመረምረው ድረስ የታሪኩ አጻጻፍ ለእኛ እንግዳ ሊሆን ይችላል። ጸሓፊዎቹ ተሳስተዋል ማለት ግን ተገቢ አይደለም፤ በእግዚአብሔር የተሰጠን ማስረጃ ነውና።

- እሑድ ማለዳ የሆነው የመሬት መንቀጥቀጥ፣ የጌታ መልአክ መውረድ አንድ ታላቅ የሆነ ክሥተትን ምን ያህል እንዳሳወቀ መረዳት ያስፈልጋል። በዚያ ቀን የተፈጸሙ ድርጊቶች ስሜትን የሚቀሰቅሱ ነገሮች ነበሩ፤ ስለ እነርሱ መጀመሪያ የተናገሩት፣ በድንጋጤና በደስታ ስሜት ተውጠው እንደ ተናገሩ ልንገምት እንችላለን። ሰው በዚህ ዐይነት መንፈስ ሲገኝ ሁሉን በተከታታይነት ላይናገር ይችላል፤ ቃሎቹ እንደ ፏፏቴ ሳይፈልቁ አይቀሩምና ሐሳቡ በቅደም ተከተል ረገድ አንድ ጊዜ ወደ ኋላ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ፊት ቢሄድ አያስገርምም።

2. የሴቶች ወደ መቃብሩ መድረስ

ማቴ. 28፥1	ማር. 16፥2
በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛዪቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ።	ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን እጅግ በማለዳ ፀሓይ ከወጣ በኋላ ወደ መቃብር መጡ።
ሉቃ. 24፥1	**ዮሐ. 20፥1**
ነገር ግን ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ።	ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች።



1. ገና ጨለማ ሳለ ማርያም መግደላዊትና ሌላዋ ማርያም (ከባሏ ጋር) ወደ ዮሐንስ ቤት ለመመለስ ከቢታንያ ተነሡ።
   (የመሬት መናወጥ ሆነ፤ መልአኩ የመቃብሩን ድንጋይ አነሣ መቃብሩን የሚጠብቁትም ሸሹ።)
2. ቀለዮጳ በዮሐንስ ቤት ሲቈይ፣ ሰሎሜ ከሁለቱ ማርያሞች ጋር ሆና በጌናጥ በር በኩል ወደ መቃብሩ ጕዞ ጀመሩ።
3. መቃብሩን ክፍት ሆኖ አዩት። ማርያም መግደላዊት ለዮሐንስና ለጴጥሮስ ለመናገር በፍጥነት ተመልሳ ሄደች።



ኢሉድ 2: ማለዳ

1. ዮሐና እና 'ሶስና' ከሀስሞናዊው ቤተ መንግሥት ተነሥተው በኤፍሬም በር በኩል መቃብሩ ደረሱ። ስለሜንና ሌላዋን ማርያም ይዘው ነው ወደ መቃብሩ የሄዱት፤ በዚያም መላእክቱ ታዩአቸው፤ መልእክቶቻቸውንም ነገሯቸው።
2. በዮሐና መሪነት ወደ ከተማው በፍጥነት ተመለሱ። በመጨረሻም ወደ ዮሐንስ ቤት የሚወስደውን መንገድ አገኙ።

ሴቶቹ በስንት ሰዓት ወደ መቃብሩ ደረሱ? አስቀድሞ እንደ ተጠቈመው አስተሳሰብ የቅዳሜን ሌሊት የት እንዳሳለፉት ሰናስታውስ፣ ከልዩ ልዩ አቅጣጫ የመጡ ይመስላል። እንግዲህ የወንጌል ጸሓፊዎች የተነሡበትንና የደረሱበትን ሰዓት ለመግለጽ በተለያዩ ሐረጎች ይጠቀማሉ፤ ለምሳሌ፣ ቅዱስ ማቴዎስ፣ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛዪቱ ማርያም ከቢታንያ መቃብሩን ለማየት የመጡት በመጀመሪያው ቀን ንጋት ላይ ነው ይላል። ቅዱስ ዮሐንስ በተለይ በመግደላዊት ማርያም ታሪክ ላይ በማትኰር፣ "ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን... ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ" እንደ መጣች ጽፎአል። ከቢታንያ ወደ ኢየሩሳሌም የዐምስት ኪሎ ሜትር ጕዞ ስለ ነበረ፣ ሲነሡ ገና ጨለማ ቢሆንም፣ እስከሚደርሱ ድረስ "ሊነጋ" ይችላል። ሁለቱን ሴቶች ቀለዮጳ መሸኘቱ አስፈላጊ ነበር፤ መንገድ ላይ ከስሎሜ ጋር እንዲገናኙ ወደ ዮሐንስ ቤት ብቅ ማለት የነበረባቸው መሆኑን አንረሳም። የሞተ ሰውን ሥጋ መቅባት የሴት ድርሻ ስለ ነበረ፣ ቀለዮጳ

በዮሐንስ ቤት ለመቈየት ወሰነ። ዮሐናና "ሶስና" ከሄሮድስ ቤተ መንግሥት "እጅግ ማልደው" ወደ መቃብሩ እንደ መጡ ቅዱስ ሉቃስ ይነግረናል። ቅዱስ ማርቆስ ግን ሁለቱም ማርያሞችና ሰሎሜ ወደ መቃብሩ በመሄድ ላይ ሳሉ፣ "እጅግ በማለዳ ፀሓይ ከወጣ በኋላ" በማለት የሚፃረር ሐሳብ ያለው ሐረግ ይመስላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፀሓይ ሲወጣ ማለት ጎሕ ሲቀድ ማለት ስለ ሆነ ምንም ግጭት አይፈጠርም። የማያጠራጥረው፣ ሴቶች ሲነሡ ገና ጨለማ፣ ወደ መቃብሩ ስፍራ ሲደርሱ ግን የቀኑ ብርሃን የነበረ መሆኑ ነው።

እንግዲህ የእሑድ ማለዳ ድርጊቶች ተከታታይነት ምን መልክ ይኖረው ይሆን? አስቀድሞ በተጠቈመው አስተሳሰብ መሠረት እንደሚከተለው ሊሆን ይችል ነበር:- ገና ጨለማ ሳለ መግደላዊት ማርያም፣ ሁለተኛዪቱ ማርያምና ባለቤቷ ቀለዮጳ ከቢታንያ ተነሡ፤ ወደ ዮሐንስ ቤት የደረሱት፣ ጎሕ ሲቀድ ነው። ቀለዮጳ እዚያ ሲቈይ፣ ሁለቱ ማርያሞች ከሰሎሜ ጋር እርሷ የገዛቸውን ሽቱና ቅባት ተሸክመው ወደ መቃብሩ የሚያደርጉትን ጕዞ ቀጠሉ። በጌናጥ በር በኩል ዐልፈው ወደ ዮሴፍ የአትክልት ስፍራ ገቡ። በታላቁ የመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት የተቸገሩ ስለ መሆናቸው ምንም ነገር አልተጻፈም። በጨለማው ጊዜ ታላቅና የሚያንጸባርቅ መልአክ የተገለጠበት የምድር መናወጥ፣ ለዐጭር ጊዜ የሚቈይና በውጤት የተወሰነ ሊሆን ይችል ነበር። በእውነት ሴቶቹ ይጨነቁ የነበረው ስለ ሌላ ጕዳይ ነው፤ ይኸውም፣ "እርስ በርሳቸውም:- ድንጋዩን ከመቃብር ደጃፍ ማን ያንከባልልልናል? ይባባሉ ነበር"፤ ማር. 16፥3። ምናልባት ዮሴፍ፣ ወይም አትክልተኛ ወይም የሌሊት ዘበኛ ሳይኖር እንደማይቀር በማሰብ ተጽናንተው ጕዟቸውን ቀጥለው ሊሆን ይችላል። ወደ አትክልቱ ስፍራ እስከሚደርሱ ድረስ ሙሉ የቀን ብርሃን ነበረ። ወደ መቃብሩ ሲቀርቡም እየተደነቁ ትልቁ ድንጋይ ከመቃብሩ ደጃፍ ላይ እንደ ተንከባለለ ተመለከቱ።

መግደላዊት ማርያም ደንግጣ የጌታ ኢየሱስ ሥጋ እንደ ተሰረቀ ዐሰበች፤ ሌሎቹ ሴቶች ግራ እየተጋቡ ሲቆሙ እነርሱን ትታ፣ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ለማስረዳት ወደ ዮሐንስ ቤት ሮጠች። ሰሎሜና ሁለተኛዪቱ ማርያም እርስ በርሳቸው ሲመካከሩ፣ ዮሐናና "ሶስና"

ወደ እነርሱ ሲጠጉ አዩ፤ ሴቶቹ የቀብሩን ሥርዐት በአንድነት ለመፈጸም ተስማምተው ነበርና። ዮሐናና "ሶስና" ከሄሮድስ ቤተ መንግሥት በኤፍሬም በር በኩል ወደ አትክልቱ ስፍራ ደርሰው ነበር፤ የኢየሱስ ሥጋ እንዴት እንደ ተቀመጠ ዐርብ ምሽት ላይ ያዩት ሴቶች እነርሱ ስለ ነበሩ፤ አስከሬኑ በመቃብሩ ውስጥ መገኘት አለመገኘቱን ማረጋገጥ እንደሚገባቸው ወሰኑ። እንግዲህ ዮሐናና "ሶስና" ሰሎሜንና ሁለተኛዪቱን ማርያም አስከትለው ወደ ውስጥ ገቡ። ጐንበስ ብለው በጠባቡ መግቢያ በኩል ተሻግረው ክፍት ወደ ሆነው ሰፊ ቦታ ዐለፉ። ዐይኖቻቸው የደበዘዘውን ብርሃን እስከሚለምዱት ድረስ፤ አራቱ ሴቶች በስተ ግራ የነበረውን ግድግዳ ተደግፈው ቆሙ። ሦስቱ የወንጌል ጸሓፊዎች ማቴዎስ፤ ማርቆስና ሉቃስ ምን እንደ ተከሠተ ይነግሩናል:-

3. በመቃብር ውስጥ የታየው መልአካዊ መገለጥ

ማቴዎስ 28፥5-7

መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው:- እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ ዐውቃለሁና እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ። ፈጥናችሁም ሂዱና:- ከሙታን ተነሣ፤ እነሆም ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሯቸው። እነሆም ነገርኋችሁ።

ማርቆስ 16፥5-8

ወደ መቃብሩም ገብተው ነጭ ልብስ የተጐናጸፈ ጕልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ አዩና ደነገጡ። እርሱ ግን:- አትደንግጡ፤ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ፤ ተነሥቶአል፤ በዚህ የለም፤ እነሆ እርሱን ያኖሩበት ስፍራ። ነገር ግን ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ለጴጥሮስም:- ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፤ እንደ ነገራችሁ በዚያ ታዩታላችሁ ብላችሁ ንገሯቸው አላቸው።

ሉቃስ 24፥3-8

ገብተውም የጌታን የኢየሱስን ሥጋ አላገኙም። እነርሱም በዚህ ሲያመነቱ፤ እነሆ፤ ሁለት ሰዎች የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው ወደ እነርሱ ቀረቡ፤ ፈርተውም ፊታቸውን ወደ ምድር አቀርቅረው ሳሉ፤ እንዲህ አሏቸው:- ሕያውን ከሙታን መካከል ስለ ምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም። የሰው ልጅ በኀጢአተኞች እጅ ዐልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ግድ ነው እያለ ገና በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደ ተናገረ ዐስቡ።

ሦስቱን አንቀጾች ስናነጻጽር፤ በተለይ የመልአኩን (መላእክቱን) መልእክት በሚመለከት የሉቃስ አጻጻፍ ከማቴዎስና ከማርቆስ አጻጻፍ እንደሚለይ ግልጽ ነው። "አትፍሩ" ወይም "አትደንግጡ" የተባለው ቃል ቀርቶአል፤ የጌታችን ሥጋ ዐርፎበት የነበረውን ቦታ እንዲያዩ ሴቶች አልተጋበዙም፤ ወደ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሄደው ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲነግሯቸው የተሰጠው ትእዛዝ፤ ወደ ገሊላም ሄደው እዚያ እንደሚያዩት ተገብቶ የነበረው የተሰፋ ቃልም አልተጻፈም። በዚህ ፈንታ መላእክቱ፤ "ሕያውን ከሙታን መካከል ስለ ምን ትፈልጋላችሁ?" ብለው ሴቶቹን ይጠይቃሉ፤ "እንደ ነገራችሁ በዚያ (በገሊላ) ታዩታላችሁ።" በማርቆስ እንደ ተጻፈው ሐረግ፤ ሉቃስ፤ "የሰው ልጅ በኀጢአተኞች እጅ ዐልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ግድ ነው እያለ ገና በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደ ተናገረ ዐስቡ" በማለት ጽፎአል። የተነገረው መልእክት ሁሉ በመልአኩ አማካይነት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ሲሆን፤ እያንዳንዱ የወንጌል ጸሓፊ ከራሱ ዐላማ ጋር የሚስማማውን እንደ መረጠ ግልጽ ነው። በሚከተለው ምዕራፍ ሕያው የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ወደ ኤማሁስ ይጓዙ ከነበሩ ሁለት ደቀ መዛሙርት ጋር ሲነጋገር፤ በኋላም ለሐዋርያትና ለሌሎች ደቀ መዛሙርት ራሱን በገለጠ ጊዜ፤ ትንሣኤውን አስቀድሞ በሕግና በነቢያት፤ ራሱም ከተናገራቸው ቃላት ጋር በጥብቅ በማዛመድ ያስገነዘበውን አንባብያኑ ያስተውሉ ዘንድ ሉቃስ መፈለጉ ጕልቶ ይታያል። ማቴዎስ በበኩሉ የራሱ የሆነ ዐላማ እንደ ነበረው አይተናል፤ ማርቆስ ታሪኩን በመጀመሪያ ከሐዋርያው ጴጥሮስ ከሰማ፤ "ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ለጴጥሮስም... ንገሯቸው" የተባለውን ለጴጥሮስ የማይረሳ ቃል ጨምሮ መታየቱ የሚያስገርም አይሆንም። የሦስቱ ወንጌላውያን መልእክቶች ተደጋጋፊዎች እንጂ እርስ በርስ የሚቃረኑ አይደሉም። የተነገረው ሁሉ ከሁለት ደቂቃ በላይ የሚፈጅ ላይሆን ይችላል።

መልእክቱንና የሚያስከትለውን ውጤት ከመመርመራችን በፊት መልእክተኞቹን መመልከት አለብን። ቅዱስ ማርቆስ ለሴቶቹ የተናገረው መልእክተኛ፤ "ነጭ ልብስ የተጐናጸፈ ጕልማሳ" መሆኑን ይገልጣል። ሴቶቹ እንደ "ደነገጡ" በኋላም እየተንቀጠቀጡ በፍርሀት

ከመቃብሩ እንደ ሸሹ ይነግረናል። በተፈጥሮ ከሚታወቀው በላይ የሆነ ገጽታ ያለው ጒልማሳ ነበረና ምናልባት ሴቶቹ የፈሩት በነጭ ልብሱ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም፤ መልአኩ ከሱራፌልና ከኪሩቤል በቀር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጡ መላእክት ሁሉ እንደ ሆኑት፤ በሰው መልክ ታየ። ቅዱስ ሉቃስ በግልጽ "ሁለት ሰዎች የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው ወደ እነርሱ ቀረቡ፤ ፈርተውም ፊታቸውን ወደ ምድር አቀርቅረው" (24፥5) መላእክቱ የተናገሯቸውን እንደ ሰሙ ጽፎአል። በኋላ ሴቶቹ የመላእክትን ራእይ እንዳዩ ለደቀ መዛሙርት ነገሯቸው፤ 24፥23። ማርቆስ፣ መልአኩ ተቀምጦ ሴቶቹን ተናገራቸው ሲል፣ ሉቃስ "ወደ እነርሱ ቀረቡ" ("አጠገባቸው ቆሙ" አ.መ.ት.) ይላል፤ "ታያቸው" ተብሎ የተተረጐመው የግሪኩ ቃል አንዳንድ ጊዜ "በድንገት ታያቸው" ሊባል ይችላል። መላእክቱ ሳይታዩ ሴቶቹ ወደ መቃብሩ እንደ ገቡ ሉቃስ ብቻ በግልጽ ይናገራል፤ ማርቆስ፣ "ወደ መቃብሩም ገብተው" በሚለውና "ወደ መቃብሩ እንደ ገቡም" (አ.መ.ት.) በሚለው አባባል መካከል የትርጒም ልዩነት የለም። በማቴዎስ ወንጌል የተገለጠው መልአክ ጠባቂዎቹን ለማስፈራራት በመጀመሪያ ውጭ በትልቁ ድንጋይ ላይ እንደ ተቀመጠ፣ በኋላም ሴቶቹን እንዳያስፈራቸው ወደ ውስጥ እንደ ገባ ዐስበናል፤ ስለዚህ እርሱ፣ "የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ" ("ኑና ተኝቶበት የነበረውን ቦታ እዩ" አ.መ.ት.) በማለት፣ መልአኩ የተናገረው ወደ መቃብሩ እንዲገቡ ሳይሆን፣ በውስጥ ተገኝተው ሳይፈሩ ኢየሱስ ተኝቶበት የነበረውን ቦታ በቅርብ ሆነው እንዲመለከቱ የሚያስገነዝብ ነው፤ ከተልባ እግር ልብሱ በቀር ቦታው ባዶ ነበረና!

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ታሪክ ዋና ዋና ወቅቶች ላይ መላእክት ትልቅ ድርሻ እንደ ነበራቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል። ቅድስት ድንግል ማርያምን ያበሠረው መልአኩ ገብርኤል ነበረ፤ ጌታችን በተወለደበት ሌሊት መወለዱን ለእረኞች ያሳወቁት፣ እግዚአብሔርንም ያመሰገኑት መላእክት ነበሩ፤ ጌታችን በምድረ በዳ በተፈተነ ጊዜ ያገለገሉት መላእክት ናቸው፤ በጌቴሴማኒ ጌታችንን ሲጸልይ ያበረታታው መልአክ ነበረ፤ አሁን ከሙታን ሲነሣ በኋላም

ወደ ሰማይ ሲያርግ መላእክት መላካቸውን እናውቃለን። መላእክት በእነዚህ ወቅቶች እግዚአብሔር ስለሚያደርገው ታላቅ የማዳን ሥራ መግለጫ ይሰጣሉ።

አንድ የወንጌል ጸሓፊ ስለ አንድ መልአክ፣ ሌላው ስለ ሁለት መላእክት ቢናገር በእውነት ግጭት የሚያስነሣ አይደለም፤ መላእክቱ ሁለት ከሆኑ ቢያንስ አንድ መልአክ እንደ ነበረ ግልጽ ነው። አንድም የወንጌል ጸሓፊ አንድ መልአክ ብቻ እንደ ተገኘ አይናገርም። አንዳንድ ጊዜ ዋናው ተናጋሪ ብቻ ሊጠቀስ ይችላል። በዚህ አመለካከት በጌርጌሴኖን አገር ማርቆስና ሉቃስ ከርኩሳን መናፍስት የተፈወሰው አንድ ሰው እንደ ነበረ ሲጽፉ፣ ማቴዎስ ሁለት እንደ ነበሩ ገልጾአል (8፥28)፤ በኢያሪኮ የተፈወሱ ዐይነ ስውሮችም ሁለት መሆናቸውን ያስረዳናል፤ 20፥30፤ ማር. 10፥46-52፤ ሉቃ. 18፥35-43 ይመ.።[10] ስለ ትንሣኤ ክርስቶስ የጻፉ ምስክሮች በፍርድ ቤት "ስንት መላእክት ነበሩ?" የሚል ጥያቄ ቢቀርብላቸው በዳኛው ፊት መልስ አይሰጡም፤ ከራሳቸው አመለካከት እያንዳንዳቸው እውነቱን በማሰብ ስለ አንድ ታላቅና በወቅቱ ግራ አጋብቶ ስለ ነበረ ክሥተት ለመናገር ሙከራ ያደርጋሉ።

ስለዚህ አራቱ የወንጌል ጸሓፊዎች የጻፉትን አያይዘን ከተመለከትነው፣ ሁለት መላእክት የነበሩ ይመስላል፣ ከእነርሱ አንዱ ዋናው ተናጋሪ ነበረ። እርሱ "መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ" ሆኖ ታላቁን ድንጋይ አንሥቶ ከመቃብሩ መግቢያ አንከባልሎ ጠባቂዎቹ ከአትክልቱ ስፍራ እስከሚወጡ ድረስ በላዩ ላይ ተቀመጠበት። በኋላም ወደ መቃብሩ ውስጥ ገብቶ ከሁለተኛው መልአክ ጋር የመጀመሪያዎቹ ሴቶች እስከሚደርሱ ድረስ ሳይታዩ ቈዩ። ለሴቶቹ በታዩአቸው ጊዜ መልእክታቸውን አቀረቡላቸው። ጴጥሮስና ዮሐንስ በደረሱ ጊዜ ባይታዩም፣ መግደላዊት ማርያም ወደ

[10] በሁለቱ ታሪኮች ከተፈወሱት መካከል አንዱ ኢየሱስን መከተል እንደ ፈለገ በማርቆስና በሉቃስ ስለ ተጻፈ፣ በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ የሚታወቅ ሳይሆን አልቀረም።

አትክልቱ ስፍራ ተመልሳ መቃብሩን ለማየት ጐንበስ ስትል መላእክቱ እንደ ገና ታዩ።

እንግዲህ አራቱ ሴቶች ሰሎሜና ሁለተኛዪቱ ማርያም፣ ዮሐናና "ሶስና" በዋሻው ጠርዝ ተደግፈው ሲገኙ ድንገት በክፍሉም ውስጥ ብሩህ ብርሃን በርቶ ጨለማውን አባረረ። የኢየሱስ ሥጋ ተኝቶበት በነበረው ቦታ እጅግ የሚያንጸባርቅ ነጭ ልብስ የለበሱትን ሁለት ጉልማሶች አዩ። ከፍርሀትና ከድንጋጤ የተነሣ ሴቶቹ በግንባራቸው ተደፍተው ምድር ላይ ወደቁ። የሦስቱን የወንጌል ጸሓፊዎች አባባል ለማጣመር ስንሞክር፣ ከመላእክቱ አንዱ ሴቶቹን እንዲህ ብሎ ተናገራቸው:-

"እናንተስ አትፍሩ አትደንግጡም፤ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን እንድትሹ ዐውቃለሁና። ሕያውን ከሙታን መካከል ስለ ምን ትፈልጋላችሁ? እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤ እነሆ እርሱን ያኖሩበትን ስፍራ ኑና እዩ። የሰው ልጅ በኀጢአተኞች እጅ ዐልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ግድ ነው እያለ ገና በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደ ተናገረ ዐስቡ። ፈጥናችሁም ሂዱና:- ከሙታን ተነሣ እነሆም ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፤ በዚያ ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ለጴጥሮስም ንገሯቸው። እነሆም ነገርኋችሁ።"

እውነት ነው፣ እያንዳንዱ የወንጌል ጸሓፊ የጻፈውን ሰናነብ ሐሳቡ በይበልጥ የተለመደ ነው። እንዲሁ እንደሚታየው ግን ሦስቱ የወንጌል ጸሓፊዎች የጻፉትን በአንድነት አጣምረን ስንመለከት መልእክቱ ሙሉ በሙሉ ራሱን የማይፃረር መሆኑ ግልጽ ሆኖአል። ሴቶቹ መልእክቱን ሰምተው ምን እንዳደረጉ አሁን እንድንመለከት ያስፈልጋል።

4. ሴቶቹ መልእክቱን ከሰሙ በኋላ ከመቃብሩ መሸሻቸው

ማቴዎስ 28፥8	ማርቆስ 16፥8
በፍርሀትና በታላቅ ደስታም ፈጥነው ከመቃብር ሄዱ፤ ለደቀ መዛሙርቱም ሊያወሩ ሮጡ።	መንቀጥቀጥና መደንገጥ ይዞአቸው ነበርና ወጥተው ከመቃብር ሸሹ፤ ይፈሩ ነበርና ለማንም አንዳች አልነገሩም።

ከመቃብሩም ተመልሰው ይህን ሁሉ ለዐሥራ አንዱና ለሌሎች ሁሉ ነገሩአቸው። ይህንም ለሐዋርያት የነገሩአቸው መግደላዊት ማርያምና ዮሐና	የያዕቆብም እናት ማርያም ከእነርሱም ጋር የነበሩት ሌሎች ሴቶች ነበሩ። ይህም ቃል ቅዠት መስሎ ታያቸውና አላመኑአቸውም።

ሴቶቹ በመልአክ ለተነገራቸው መልእክት ምን ዐይነት የአፀፋ ምላሽ እንደ ሰጡ በማቴዎስ፣ በማርቆስና በሉቃስ ተጽፎአል። በሦስቱ አጻጻፍ ላይ በተለይ ሁለት ጥያቄዎች ሊነሡ ይችላሉ፤ ይኸውም፣ አንደኛው፣ ባዩትና በሰሙት ምክንያት ሴቶቹ ፈሩ ወይስ ተደሰቱ? የሚለው ነው። ማቴዎስ በፍርሀትና በታላቅ ደስታ ተሞልተው ከመቃብሩ ፈጥነው ሄዱ ሲል፣ ማርቆስ፣ በመንቀጥቀጥና በድንጋጤ ተይዘው ከመቃብር ሸሹ ብሎ ጽፎአል። ሁለቱም የወንጌል ጸሓፊዎች በተጠቀሙባቸው አባባሎች መካከል ብዙ ልዩነት ላይኖር ይችላል። በታላቅና ባልታሰበ አንድ ዜና ምክንያት ሰው በተመሳሳይ ጊዜ ሊፈራም ሊደሰትም ይችላል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰው መልአክን ባየ ጊዜ የፍርሀት ስሜት የሚሰማው መሆኑ የተለመደ ነበር፤ ሉቃ. 1፥12፡29፤ 2፥9። ስለ መሲሑ ከሙታን መነሣት በብሉይ ኪዳን የተጻፈውና በጌታችን የተነገረው ለእነርሱ ገና ግልጽ ባይሆንላቸውም፣ በመልአኩ መልእክት ተጽናንተው ከሚያስቡት በላይ ታላቅ የነበረ የተስፋ ስሜት ልባቸውን ሳይሞላው እንዳልቀረ መገመት እንችላለን። የሚያስደስት ነገር በቅርብ እንደሚፈጸም የሚያመለክት ስሜት ሊያሳድርብን ይችላል፤ የሴቶቹ ሁኔታ ከዚህ የተለየ ላይሆን ይችላል።

ሁለተኛው ጥያቄ፣ ሴቶቹ የኢየሱስን ደቀ መዛሙርት ስለ ትንሣኤ ለማሳወቅ የተሰጣቸውን ትእዛዝ እንዴት እንደ ፈጸሙት የሚያመለክት ነው። ማቴዎስ፣ "ለደቀ መዛሙርቱም ሊያወሩ ሮጡ" በማለት፣ ወዴትና ወደ እነማን እንደ ሄዱ አልገለጠም፤ ወደ ዮሐንስ ቤት? ወደ ቢታንያ? ወደ ሁለቱም? በሚከተለው ምዕራፍ ወደዚህ ነጥብ እንመለሳለን። የማርቆስ ወንጌል፣ በብዙ ሊቃውንት ዘንድ በመጀመሪያ እንደ ተጻፈ የሚታመን ሲሆን፣ የሚጨርሰው፣ የሴቶቹን ዝምታ በመግለጽ ነው፤ በሌላ ወንጌል ጸሓፊ የተነገረው ሐሳብ ቄይቶ እንደ ተጨመረ ይታመናል። ይህ ግን መሆን አይችልም። በመንገድ ላይ ወደ

ዮሐንስ ቤት ሲሄዱ ሳሉ ለማንም አንዳች አልተናገሩም፤ እርሰ በርሳቸውም እንኳ የተነጋገሩ አይመስልም። በኋላ ግን እነርሱ ባይናገሩ ኖሮ ሌሎች ሰዎች እንዴት ግንዛቤ ላይ ደረሱ? ሉቃስ የመግደላዊት ማርያምን ወደ ጴጥሮስና ወደ ዮሐንስ መሄድ ከዮሐናና ከሌሎች ሴቶች ወደ ዐሥራ አንዱና ሌሎች ደቀ መዛሙርት መሄድ ጋር አያይዞ ያሳያል። እርሱ (ለምሳሌ፤ 24፥11፡25፡38፡41) እና ማርቆስ (16፥11፡13፡14) ትኵረት ያደረጉት በደቀ መዛሙርት አለማመን ላይ ነው።

እንግዲህ ዮሐና በመጣችበት መንገድ ማለት በኤፍሬም በር በኩል "ሶስና"ን፣ ሰሎሜንና ሁለተኛዪቱን ማርያም ከአትክልቱ ስፍራ ወደ ከተማዪቱ ስትመራቸው በሐሳባችን ማየት እንችላለን። በመጀመሪያ አንደበታቸው በፍርሀት ስለ ተያዘ ዝም ብለው፣ ወዴትም እንደሚሄዱ በደንብ ሳያውቁ፣ ድንጋጤአቸው ከታላቅ ደስታ ጋር እየተደባለቀ፣ ያዩትንና የሰሙትን ለማውራት በመጓጓት ወደ ዮሐንስ ቤት ደረሱ። ሴቶቹ በመቃብሩ ስፍራ ከደረሱበት ጊዜ ጀምሮ በአትክልቱ ስፍራ የሆነው ሁሉ የፈጀው ጊዜ ከዐሥር ደቂቃ ላይበልጥ ይችላል!

5. የጠባቂዎች መመስከርና በጉቦ መደለል

አሁን ወደ ጠባቂዎች መመለስ አለብን። አስደናቂው ነገር፣ በመቃብሩ ቦታ ስለ ትንሣኤ ክርስቶስ ከተሰጡት ማስረጃዎች መካከል አንዱ ከጠላት መገኘቱ ነው።

ሴቶቹ ወደ አትክልቱ ስፍራ ከመድረሳቸው ጥቂት ጊዜ በፊት፣ ጠባቂዎቹ ሾሽተው የወጡበት ወቅት ሳይሆን እንዳልቀረ ዐስበናል። ከዐሥር ደቂቃ ያህል በኋላ፣ ሴቶቹ ወደ ዮሐንስ ቤት በመጓዝ ላይ ሳሉ፣ ከጠባቂዎቹ አንዳንዶች ምን እንዳደረጉ ቅዱስ ማቴዎስ ይነግረናል።

ማቴዎስ 28፥11-15

ሲሄዱም ሳሉ እነሆ፣ ከጠባቆቹ አንዳንድ ወደ ከተማ መጥተው የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች አወሩ። ከሽማግሌች ጋርም ተሰብስበው ተማከሩና ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጥተዋቸው:- እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ። ይህም በገዢው ዘንድ የተሰማ እንደ ሆነ፣ እኛ እናስረዳዋለን እናንተም ያለ

ሥጋት እንድትሆኑ እናደርጋለን አሉአቸው። እነርሱም ገንዘቡን ተቀብለው እንደ አስተማሩአቸው አደረጉ። ይህም ነገር በአይሁድ ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ ሲወራ ይኖራል።

ጠባቂዎቹ፣ "የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች አወሩ" ተብሎ በተጻፈው ቃል መሠረት፣ ከሦስት ቀን በኋላ እንደሚነሣ ኢየሱስ የተናገረውን ያስታወሱት የአይሁድ መሪዎች፣ እርሱ በርግጥ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በመጨረሻ ያምኑ ኖሮአል? በጭራሽ! እነርሱ ራሳቸው እውነትን ለመቀበል እንምቢተኞች የነበሩ ሲሆን፣ ሌሎችም እንዳይቀበሉት ምን ዐይነት ርምጃ እንደ ወሰዱ አሁን ይታያል። እርሰ በርሳቸው ተመካክረው እውነቱ እንዳይገለጥ ብቻ ሳይሆን፣ ይልቁን ዐውቀው ውሸት እንዲሰፋፋ፣ የካህናት አለቆች ለጠባቂዎቹ ትልቅ ጉቦ ሰጡአቸው። "እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰረቁት በሉ" አሉአቸው። ታሪኩ ራሱን የሚፃረር በመሆኑ የሚያሥቅ ነው፤ ጠባቂዎቹ ተኝተው ከሆነ፣ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በሌሊት መጥተው በድኑን እንደ ሰረቁት እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ? በተረኛነቱ ጊዜ ተኝቶ የተገኘ ሮማዊ ወታደር ከፍ ያለ ቅጣት ስለሚደርስበት፣ ችግር ቢነሣ ከሮማዊው ገዥ ከጲላጦስ ጋር ተነጋግረው ክፉ ነገር እንዳይደርስባቸው የካህናት አለቆች የሚያስፈልገውን እንደሚያደርጉላቸው ከጠባቂዎቹ ጋር ተስማሙ። ጠባቂዎቹ በእውነት ተኝተው ቢገኙ ኖሮ፣ በሮማ ባለሥልጣናት ፊት በመጀመሪያ የሚከሰሱአቸው የአይሁድ መሪዎች ይሆኑ ነበር፤ ድርጊታቸው ውሸት መሆኑ ግልጽ ነውና!

እውነቱን ለመቀበል በእልከኛነት እንምቢ ማለት በእግዚአብሔር ፊት ከባድ ኀጢአት ቢሆንም፣ ይልቁንም ሌሎች ሰዎች እንዳያምኑ በተንኰልና በጉቦ መጠቀም የባሰ አስከፊ ኀጢአት ነው። በኢየሩሳሌም ውስጥ ለመንዛት ከተጀመረው ወሬ በስተ ኋላ የነበረውን ተንኰልና ውሸት ቅዱስ ማቴዎስ ስለ ትንሣኤ ክርስቶስ በሚጽፈው ታሪክ መግለጥ መፈለጉ አያስገርምም። ቢሆንም በሐሰተኛ ወሬ ውስጥ ያለው መርዝ ቶሎ እየተሰፋፋ ይሄዳል። "ይህም ነገር በአይሁድ ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ ሲወራ ይኖራል" ብሎአል። ማቴዎስ ስለ ራሱ ዘመን ሁኔታ

ሲጽፍ፣ ይልቁንም እስከዚህ ዘመን ድረስ፣ ሰዎች በትንሣኤ ክርስቶስ እንዳያምኑ፣ ደቀ መዛሙርቱ በድኑን ሰርቀዋል የሚል የሐሰት ምክንያትን የሚያቀርቡ አሉ።

6. ጴጥሮስና ዮሐንስ የተልባ እግር ልብሱን አቀማመጥ መመልከታቸው


ሉቃስ 24÷12

ጴጥሮስ ግን ተነሥቶ ወደ መቃብር ሮጠ፤ በዚያም ዝቅ ብሎ ሲመለከት የተልባ እግር ልብስን ብቻ አየ፤ በሆነውም ነገር እየተደነቀ ወደ ቤቱ ሄደ።

ዮሐንስ 20÷2-10

እየሮጠችም ወደ ስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ይወደው ወደ ነበረው ወደ ሌላው ደቀ መዝሙር መጥታ:- ጌታን ከመቃብር ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አናውቅም አለቻቸው። ስለዚህ ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር ወጥተው ወደ መቃብሩ ሄዱ። ሁለቱም ዐብረው ሮጡ፤ ሌላው ደቀ መዝሙርም ከጴጥሮስ ይልቅ ፈጥኖ ወደ ፊት ሮጠና አስቀድሞ ከመቃብሩ ደረሰ፤ ዝቅም ብሎ ቢመለከት የተልባ እግሩን ልብስ ተቀምጦ አየ፣ ነገር ግን አልገባም። ስምዖን ጴጥሮስም ተከትሎት መጣ ወደ መቃብሩም ገባ፤ የተልባ እግሩን ልብስ ተቀምጦ አየ፣ ደግሞም በራሱ የነበረውን ጨርቅ ለብቻው በአንድ ስፍራ ተጠምጥሞ እንደ ነበረ እንጂ ከተልባ እግሩ ልብስ ጋር ተቀምጦ እንዳልነበረ አየ። በዚያን ጊዜ አስቀድሞ ወደ መቃብር የመጣውም ሌላው ደቀ መዝሙር ደግሞ ገባ፣ አየም፣ አመነም፤ ከሙታን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው የሚለውን የመጽሐፉን ቃል ገና አላወቁም ነበርና። ደቀ መዛሙርቱም ወደ ቤታቸው ደግሞ ሄዱ።

ሌሎቹ ሴቶች ወደ መቃብሩ ሲገቡና እዚያም ተገኝተው የመልአኩን መልእክት ሲሰሙ ወደ ቀረችው መግደላዊት ማርያም መመለስ አለብን። ቅዱስ ዮሐንስ ወደ መቃብሩ ከሄዱ ሴቶች መግደላዊት ማርያምን ቢጠቅስም፣ ማርያም "ወዴትም እንዳኖሩት አናውቅም" ብላ ከተናገረችው፣ ሌሎች ሴቶች ከእርሷ ጋር እንደ ሄዱ መገንዘቡን ያሳያል። "ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች" የሚለው ሐረግ፣ ሴት በመሆኗ በዚያ ሰዓት ብቻዋን እንድትሄድ ማንም አይጠብቅም። የማርያምን ታሪክ በመምረጥ ግን፣ በታሪኩ ምን ያህል የሐዋርያው ልብ እንደ ተነካ፣ ደግሞም ስለ ትንሣኤ ክርስቶስ ልዩ ልዩ ማስረጃ ማቅረብ ካለው ዐላማ ጋር እንደሚስማማ ያሳያል።



1. በዚያን ጊዜ ዮሐንስና ጴጥሮስ (ማርያም መግደላዊት ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሸኘታቸው) በጌናጥ በር በኩል ወደ መቃብሩ አመሩ።
2. እነርሱ ወደ ቤት ሲመለሱ ማርያም መግደላዊት ወደ ኋላ ቀረች። በመቃብሩ ቦታ መላእክቱን አየች፣ ቀጥሎም ኢየሱስ ተገለጠላት።
3. ማርያም መግደላዊት ወደ ዮሐንስ ቤት ተመልሳ ሄደች።

ማርያም ጌታችን ኢየሱስ ከሙታን እንደሚነሣ ምንም ሐሳብ ያልነበራት ይመስላል። እርሷ እንደ ተረዳችው፣ ሰው ታላቁን ድንጋይ ያንከባለለበት ምክንያት፣ የኢየሱስን ሥጋ ለመስረቅ ብቻ መሆን ነበረበት። የዮሐንስ አገላለጽ፣ አስቀድመን እንዳየነው፣ ማንኛውም ሰው ወደ መቃብሩ ከመግባቱ በፊት፣ እርሷ ስለ መሄዷ ጉዳይ ያለው አስተሳሰብ ጽኑ ነው። አንድ ጊዜ ወደ ተከፈተው መቃብር መመልከቷ ግን፣ ወደ ጴጥሮስና ዮሐንስ ፈጥና እንድትሄድ በቂ ነበረና። ማርያም የተናገረችውን ከሰሙ በኋላ፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ እየሮጡ ወደ መቃብሩ ሄዱ።

በጥንታዊቷ ኢየሩሳሌም ብዙ መንገዶች ስለ ነበሩ፣ ከመቃብሩ በመመለስ ላይ የነበሩ ሴቶች ወደ መቃብሩ በፍጥነት ከሚሄዱት ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ጋር አልተገናኙም። ዮሐንስ የኢየሩሳሌም ነዋሪ ስለ ነበረ ከቤቱ ወደ አትክልቱ ስፍራ ቀጥታ የሚመራው መንገድ

በጌናጥ በር መሆኑን ዐወቀ። ዮሐና ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ ብቻ ወደ ከተማዪቱ ስለ መጣች፣ ከእርሷ ጋር የነበሩትን ለሄሮድስ ቤተ መንግሥት በሚቀርበው በኤፍሬም በር በኩል ሳትመራቸው አልቀረችም።

በሉቃስ በተጻፈው ዐጭር ዘገባ (24፥12) ጴጥሮስ ብቻ ቢጠቀስ፣ ዮሐንስ ከገለጸው ታሪክ ጋር አይጋጭም። ሉቃስ፣ ጴጥሮስ "ዝቅ ብሎ ሲመለከት" ሲል፣ ዮሐንስ፣ ጴጥሮስ "ወደ መቃብሩም እንደ ገባ" ይላል፤ የተለመደው የመቃብር መግቢያ ጠባብና ዝቅ ያለ ስለ ነበረ፣ የሰው በድን የሚያርፍበትን ከድንጋይ የተቀረጸ መደርደሪያ ከቅርብ እንዲያይ ጐንበስ ብሎ በመግቢያው በኩል ማለፍ ነበረበት። እንግዲህ ጴጥሮስ ያየው ምንድን ነበረ? ሉቃስ፣ "የተልባ እግር ልብስን ብቻ" እንዳየ ይነግረናል፤ የኢየሱስን ሥጋ አላየም ማለት ነው? ወይስ "በፍታው እንዳለ ለብቻው ተቀምጦ" (አ.መ.ት.) አይቶአል? ዮሐንስ የጻፈውን ብንመለከት ምን እንዳየ ግልጽ ይሆናል፤ "የተልባ እግሩን ልብስ ተቀምጦ አየ፣ ደግሞም በራሱ የነበረውን ጨርቅ ለብቻው በአንድ ስፍራ ተጠምጥሞ እንደ ነበረ እንጂ ከተልባ እግሩ ልብስ ጋር ተቀምጦ እንዳልነበረ አየ"፤ 20፥6-7። "በሆነውም ነገር እየተደነቀ ወደ ቤቱ" እንደ ሄደ ሉቃስ ይነግረናል። ዮሐንስ ከጴጥሮስ በፊት ወደ መቃብሩ ደርሶ ዝቅ ብሎ ከሩቅ ሲመለከት፣ የተልባ እግሩን ልብስ አየ፣ ኢየሱስ ተኝቶበት የነበረውን ስፍራ ግን ከዚያ ሙሉ በሙሉ ማየት አልቻለም። ጴጥሮስ ወደ ዋናው የመቃብር ክፍል እንደ ገባ ባየ ጊዜ ዮሐንስም ተከተለው፤ "ገባ፣ አየም፣ አመነም" ተብሎ ተጽፎአል (ቊ.8-9)፤ ዮሐንስ ያመነው ምንድን ነበረ? ያመነው ጌታ እንደ ተነሣ እኮ ነው! እንዲያምን ያደረገውስ ምን ይሆን? በዚያን ጊዜ እንዲያምን ያደረገው በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ ክርስቶስ ከሙታን መነሣት የተጻፈው አልነበረም፤ "ከሙታን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው የሚለውን የመጽሐፉን ቃል ገና አላወቁም ነበርና" (ቊ.9)፤ በዚያ ወቅት ክርስቶስ መነሣቱን እንዲያምን ያደረገው፣ የልብሱ አቀማመጥ ነበረ። እንዴትስ አሳመነው? አንድ ሊቅ የሚከተለውን ብሎአል፣ "እንደ መግነዝ ያገለገለው የበፍታ ጨርቅ ባዶውን እንደ ቀረ የቢራቢሮ ቀፎ መስሎ ታየ፤ ምንም ያልተገኘበት

ባዶ ነበረ። በራሱ ላይ ተጠምጥሞ የነበረውም ጨርቅ ከከፈኑ ተለይቶ ባዶ ነበረ። ነገር ግን እንደ ከፈኑ በኢየሱስ ራስ ተጠምጥሞ በነበረበት ጊዜ የነበረውን ቅርጽ ጠብቋል። ይህ ነበረ የጴጥሮስን ልብ የነካው። የኢየሱስ ሥጋ ተንኖ የወጣ መሰለ። ሥጋው የተሸፈነበት ከፈን በድኑ ስላልተገኘ በሽቱውና በቅመሙ ከብደት ከመጨማደድ በቀር ምንም ጉድለት አልነበረውም፤ በራሱ ላይም ተጠምጥሞ የነበረው ጨርቅ ከመጀመሪያ የነበረው ጐድጓዳ ቅርጽ ገና አልተለወጠም ነበር። ለዚህ አስደናቂ ነገር ምን ምክንያት ይኖራል? መቃብርን የሚዘርፍ ማንኛውም ሌባ እንደዚህ ዐይነት አስደናቂ ነገር ማድረግ አይችልም፣ እርሱ በድኑን ከነሙሉ ልብሱ ይሰርቀው ነበርና። ኢየሱስ እንዲሁ ወደ ሕይወት ብቻ ቢመለስ ኖሮ፣ ሲንቀሳቀስ ልብሱን ይጠቀምበት ወይም በሌላ ዐይነት ልብሱን ዐጣጥፎ በጐን ያስቀምጠው ነበር። ይሁን እንጂ የተሰጡ ፍንጮች ሁሉ፣ ጌታችን ኢየሱስ ወደ ዐዲስ ዐይነት ሕይወት፣ ወደ ዐዲስ ዐይነት ህልውና እንደ ተሸጋገረ አመለከቱ። ወደ ዐዲስ የሕይወት ደረጃ የሚገባ ቢራቢሮ እንጭጭ ሳለ የተሸፈነበትን ቀፎ እንደሚተው ሁሉ፣ ኢየሱስ በተለወጠ ሕይወት በተነሣ ጊዜ ከፈኑን፣ ጨርቁንም ሁሉ ትቶ ወጣ።"[11]

ጴጥሮስ ብቻውን ወደ መቃብሩ አልሄደም። ሉቃስ እሑድ ከሰዓት በኋላ ወደ ኤማሁስ ስለሚሄዱ መንገደኞች ሲጽፍ፣ ከሴቶች በተጨማሪ ወደ መቃብሩ ከሚሄዱ ወንዶች፣ ከጴጥሮስም ጋር ቢያንስ አንድ ሌላ ሰው መኖሩን እንደ ተገነዘበ ያልታሰበበት አንድ ፍንጭ አለ፤ ከመንገደኞች መካከል ቀለዮጳ አንዱ ነው፤ ሳያውቀው እርሱንና ሌሎችን ደቀ መዛሙርት ግራ ስላጋቢቸው ስለ እሑድ ማለዳ ድርጊቶች ኢየሱስን ለማስረዳት ሲሞክር፣ "ከእኛም ጋር ከነበሩት ወደ መቃብር ሄደው፣ ሴቶች እንደ ተናገሩት ሆኖ አገኙት፣ እርሱን ግን አላዩትም"፤ ሉቃ. 24፥24። በመቃብር ውስጥ ያዩት ማስረጃ ጴጥሮስን አስደነቀው ዮሐንስንም አሳመነው፤ ነገር ግን ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ኢየሱስን ሳያዩ ወደ ቤታቸው ሄዱ።

---

[11] Michael Green, *Man Alive*, IVP 1967፣ በተጨማሪ ጆን ስቶት፣ "ክርስቲያንነት" ም.3 ገጽ 41ን ይመ.።

በዚህ ታሪክ ውስጥ ከቅዱሳት መጻሕፍት ጭምር ለግንዛቤ የሚረዳቸው ሌላ ዐይነት ሥዕላዊ ማስረጃ ግራ ለተጋቡት ደቀ መዛሙርት በመሰጠቱ የእግዚአብሔርን ጸጋ እናያለን። በብሉይ ኪዳን ስለ ክርስቶስ የተጻፈውን ሳይሰሙ ወይም ሳያነብቡ አልቀሩም። ሰው የተጻፈውን አንብቦ ከማስተዋሉ በፊት ግን በእውነት የተጻፈውን ያውቀዋል ማለት አይቻልም።

በዚህ ምዕራፍ እግዚአብሔር የምድርን መናወጥ፣ ጌታ ኢየሱስን ከሚቃወሙት የተሰጠውን የግዴታ ምስክርነት፣ የመልአካዊ መገለጥና መልእክት፣ ከዚህም በተጨማሪ ባዶው መቃብር ውስጥ የነበረውን የተልባ እግር ልብስ በፊታችን በማስቀመጥ፣ ክርስቶስ ከሙታን እንደ ተነሣ ዐወጀልን። ይህ ሁሉ እናምን ዘንድ አይበቃምን? ሆነም አልሆነም፣ ሌላውን የትንሣኤ ክርስቶስ ማስረጃ በሚከተለው ምዕራፍ እንመረምራለን።

ምዕራፍ 5

ከሙታን ከተነሣው ከጌታችን ኢየሱስ ጋር የተገናኙ የዐይን ምስክሮች

ባዶ መቃብርን መመልከትና ክርስቶስ መነሣቱን በዐይን ከሚታዩ መላእክት መስማት አስደናቂ ነገር ቢሆንም፣ ከሙታን ከተነሣው ከራሱ ከክርስቶስ ጋር መገናኘት እጅግ በጣም ይበልጣል! ጌታችን ኢየሱስ ለሐዋርያት በአካል ስለ ታየባቸው ስለ እነዚህ ማስረጃዎች ቅዱስ ሉቃስ፣ "ከሕማማቱም በኋላ ራሱ ቀርቦ ሕያው መሆኑን፣ ለእነዚሁ በብዙ ማስረጃ እያረጋገጠላቸው አርባ ቀንም ዐልፎ ዐልፎ እየታያቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ነገራቸው" ብሎአል፤ ሐ.ሥ. 1፥3 አ.መ.ት.። ከመላእክት የተሰጠው መልእክትና ከበፍታ ልብሱ አቀማመጥ በተጨማሪ፣ የመታየቱን ማስረጃዎች እንድን መረምራቸው ከእግዚአብሔር የተሰጡ ሦስተኛ የማስረጃ ዐይነቶች ናቸው።

በዚህ ምዕራፍ ጌታችን ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣበት እስከ ዐረገበት ቀን ድረስ ዐሥራ አንድ ጊዜ ስለ መታየቱ በዐዲስ ኪዳን ውስጥ የተጻፈውን በዐጭሩ እንመለከታለን። የጌታችንን በአካል መታየት እውን መታየት እንዳልሆነ የሚያምኑትን ለመደገፍ ምክንያት እንደሚያሳጣ እናያለን። በመጀመሪያ ጌታን ያዩት ሰዎች ጌታቸው ከሙታን ይነሣል ብለው በጭራሽ አልጠበቁም ነበር። በተጨማሪ ጌታችን ኢየሱስ በተለያዩ ሁኔታዎች እንደ ታየ ግልጽ ነው:- አንዳንድ ጊዜ በግል ለአንድ ደቀ መዝሙር፣ በሌላ ጊዜ በቡድን ተሰብስበው ለነበሩ ደቀ መዛሙርት፣ ቁጥሩም ከዐምስት መቶ በላይ ለሚሆኑ ደቀ መዛሙርት በአንድ ጊዜ፣ በቤት ውስጥ፣ ከቤት ውጭ፣ በከተማና በገጠር፣ በባሕር ዳር ወይም በተራራ ላይ።

እያንዳንዱን የጌታችንን መታየት ስንመረምር፣ ምን እንደ ሆነ፣ ጌታችን ኢየሱስ ከሙታን መነሣቱን እንዴት እንዳረጋገጠ እርሱን በአካል ያዩት የሰጡትን የአፀፋ ምላሽ፣ ጸሓፊዎች በአካል መታየቱን

ለማስረጃነት እንዴት እንደ ተጠቀሙበትና በዚህ ዘመን ለምንኖር ምእመናን የሚያስተምረውን እንመለከታለን።

ሀ. በኢየሩሳሌምና በአካባቢው ስድስት ጊዜ የታየ ስለ መሆኑ

1. ለመግደላዊት ማርያም

የመግደላዊት ማርያምን ታሪክ መከታተል እንችል ዘንድ ወደ መቃብሩ መለስ ብለን ጥናታችንን እንጀምራለን። መግደላዊት ማርያም ከአትክልቱ ስፍራ ከወጡት ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ጋር ከመገናኘቷ በፊት፣ ምናልባት ከጌታችን እናት ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ቈይታ፣ ወደ መቃብሩ ተመልሳ በመሄድ ብቻዋን ከመቃብሩ ውጭ ቆማ እያለቀሰች ነበር።

ቅዱስ ማርቆስ እንደሚያሳስበን፣ ሕያው የሆነው ጌታችን ኢየሱስ መጀመሪያ የታየው፣ ሰባት አጋንንትን ላወጣላት ለመግደላዊት ማርያም ነበር፤ ማር. 16፥9። መግደላዊት ማርያም ብዙው ጎጢአቷ ስለ ተሰረየላት እጅግ የወደደችዋ ጎጢአተኛ ሴት (ሉቃ. 7፥36-50)፣ በተጨማሪም ከፍ ያለ ዋጋ የነበረውን የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ሽቶ በኢየሱስ ላይ ያርከፈከፈችው እርሷ ሳትሆን አልቀረችም፤ ዮሐ. 12፥1-8፤ እርሷ ከሆነች፣ ያደረገችው የጌታችንን መሞትና መቀበር እንደሚያመለክት፣ ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ይልቅ ዋናውን የኢየሱስን ተግባር ተረድታ ነበር ማለት ነው፤ ነገር ግን እምነቷ ክርስቶስ ከሙታን እስከሚነሣበት ድረስ ገና አላደገም። በምድራዊ አገልግሎት ላወቀችው ጌታችን ኢየሱስ በነበራት ፍቅር ጠንካራ ብትሆንም፣ ከአገልግሎቱ የሚገኘውን አስደናቂ ፍሬ በማስተዋል ረገድ ገና ደካማ ነበረች፤ ሞቶ የነበረውን የጌታዋን ሥጋ መጠበቅ እንዴት እንደምትችል ብቻ ስትጨነቅ ታይታለች። ከራሷ አንደበት እንደ ሰማው የማርያምን ታሪክ ጽፎ ያቀረበልን ሐዋርያው ዮሐንስ ነው፤ ዮሐ. 20፥11-18።

በመቃብሩ ፊት እያለቀሰች ማርያም ጐንበስ ብላ በጠባቡ መግቢያ በኩል ስትመለከት ኢየሱስ ተኝቶበት የነበረውን ስፍራ ከሩቅ አየች። በድንጋጤ ነጫጭ ልብስ የለበሱትን ሁለት መላእክት አየች፤ አንዱ

በኢየሱስ እግር በኩል፣ ሌላው ምናልባት በከፈኑና ማርያም ከነበረችበት ቦታ በማይታየው በኢየሱስ ራስ ላይ ተጠምጥሞ በነበረው ጨርቅ መካከል በራስጌ ተቀምጦ ነበር። በእንባዋ ታውራ ስለ ነበር ከፈኑ ባዶና ያልተገነዘበት መሰላት። ሌሎቹ ሴቶች ሁኔታውን በቅርብ ለመረዳት ወደ መቃብር ገብተው ነበር፤ ማርያም ግን ምናልባት በመጀመሪያም ስላልገባችና በዚህ ጊዜ ብቻዋን ስለ ነበረች ወደ ውስጥ ለመግባት አልደፈረችም። መላእክቱ ስለ ተነሣው ክርስቶስ ለእርሷ ምንም አልተናገሩም፤ በዚህ ፈንታ "አንቺ ሴት፣ ስለ ምን ታለቅሻለሽ?" ብለው ጠየቋት። ማርያም የሰጠችው መልስ ለጴጥሮስና ለዮሐንስ ከነገረቻቸው ጋር ተመሳሳይ ነው፤ ከዚህ በፊት ከሌሎች ሴቶች ጋር ዐብራ ስለ ነበረች ከእንድ በላይ ነበሩ፤ አሁን ግን ብቻዋን በመሆኗ እርሷ መልስ ትሰጣለች፤ "ጌታዬን ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አላውቅም አለቻቸው።" መልሷ የነበራትን ችግር ገለጠው፤ ይኸውም የሞተውን የክርስቶስን ሥጋ የምትፈልግ መሆኗ ነው።

ገና ከመቃብሩ ውጭ ሳለች በስተ ኋላዋ ሰው እንደ ነበረ ሳታውቅ ዘወር ስትል ድንገት ጌታ ኢየሱስን አየችው፤ እርሱም መላእክት ለማርያም ያቀረቡላትን ጥያቄ ደግሞ አቀረበላት፤ "...ማንንስ ትፈልጊያለሽ? አላት።" ማርያም የነበራት እምነት ስለ ኢየሱስ በነበራት አለማስተዋል ተዳክሞ፣ ምናልባትም ወደ አትክልቱ ስፍራ ከሌሎች ሴቶች ጋር ስትመጣ ስለ ትልቁ ድንጋይ መንከባለል የነበራቸውን ንግግር አስታውሳ፣ ኢየሱስ የአትክልቱ ስፍራ ጠባቂ መስሎአት፣ "ጌታ ሆይ፣ አንተ ወስደኸው እንደ ሆንህ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ እኔም እወስደዋለሁ አለችው"፤ በሌላ አነጋገር፣ "እኔ የሞተውን ጌታዬን ወስጄ በዚህ ሁኔታ ለራሴ መጠበቅ እፈልጋለሁ" ማለቷ ነው። የሚቀጥለው ደግሞ፣ በሕይወቷ የተከሠተ አንድ አስደናቂ አጋጣሚ ሳይሆን አልቀረም፤ ከሙታን የተነሣው ኢየሱስ "ማርያም" በማለት ስሟን የጠራበት አስደናቂ ሁኔታ፤ መልኩን ባታውቅም ስሟን ሲጠራ ብዙ ጊዜ ከዚያ በፊት ሰምታ ነበር፤ የጠራት በትክክል እርሱ ራሱ ነዋ! ማርያም ወዲያው ድምፁ በአክብሮትና በደስታ ተሞልቶ፣ "'ረቡኒ' አለችው፤ ትርጓሜውም:- መምህር ሆይ ማለት ነው።" እንደ ገና እንዳይጠፋባት ጌታ ኢየሱስን

ለመንካት እጇን ስትዘረጋ ኢየሱስ፣ እንዳትነካው ከልክሎአት፣ ወደ አብ የሚመለስበት ወቅት ገና እንደ ሆነ በመናገር አጽናናት። ይሁን እንጂ በሞቱና በትንሣኤው መሠረት "ወንድሞቼ" በማለቱ፣ በእርሱና በደቀ መዛሙርቱ መካከል የነበረው ግንኙነት እንደ ተለወጠ፣ "አባቴ" እና "አባታችሁ"፣ "አምላኬ" እና "አምላካችሁ" ሲል፣ ከአብ ጋር የነበረው ግንኙነት እነርሱ ከአብ ጋር ከነበራቸው ግንኙነት እንደሚለይ ደቀ መዛሙርቱን አስረዳቸው።

ማርያም የሞተውን ክርስቶስ እየፈለገች ወደ መቃብር መጥታ ሳለ፣ ሕያው ከሆነው ጌታ ጋር ተገናኝታ ከመቃብር ተመለሰች! የእርሷ ታሪክ በዚህ ዘመን ለምንኖር ምን ዐይነት ትምህርት መስጠት ይችላል? ለሞተው ክርስቶስ ለብዙ ዓመታት ፍቅርን ሲያሳዩ ከኖሩት ሰዎች መካከል አንባቢው እንደ አንዱ ይቈጠር ይሆን? እነዚህ ሰዎች ስለ ክርስቶስ የተሣሉ ሥዕሎችንና ምስሎችን እያከበሩ ኖረዋል፣ የተሰቀለውን ክርስቶስን በሚያሳዩት መስቀሎች ፊት ተንበርክከዋል፣ ምናልባት ከሞት እንደ ተነሣ ሰምተው ይሆናል፤ ሕያው የሆነው ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር ተገናኝቶ በስማቸው መጥራት እንደሚፈልግ ግን አላሰቡም። እምነቷን የቀሰቀሰው፣ ሐዘኗን ወደ ደስታ የለወጠው፣ ከሙታን የተነሣው የማርያም ጌታ ስሟን ሲጠራው ነው። እውነት ነው፣ "መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞተ፣ ተቀበረም" (1ቆሮ. 15፥3)፤ ጌታችን አስቀድሞ ባይሞት ኖሮ፣ ከሙታን መነሣት አይችልም ነበር። በመጀመሪያው አስደናቂ የፋሲካ እሑድ ጧት ማርያምን በስም የጠራው ክርስቶስ አሁንም በዘመናችን ሕያው የሆነ፣ ሞትንና ኀጢአትን ያሸነፈ ጌታና አምላክ ነው። ገና ሰዎችን በስም እየጠራ ሥራውን ይቀጥላል፤ ይህን ሐተታ የምታሰላስል አንባቢ ሆይ፣ ጌታ ስምህን ሲጠራ ድምፁን በመስማት ላይ ነህ? የዐጸፋ ምላሽህስ ምን ይሆን?

2. ለሌሎቹ ሴቶች

መግደላዊት ማርያም ገና በአትክልቱ ስፍራ ውስጥ ሳለች፣ አራቱ ሴቶች:- ሰሎሜና ሁለተኛዪቱ ማርያም፣ ዮሐናና "ሶስና" ወደ ዮሐንስ ቤት ሄዱ። እዚያም ዐብረው ከጌታችን እናት ከድንግል ማርያም፣

ከጴጥሮስና ከዮሐንስ፣ ከዘብዴዎስና ከቀለዮጳ ጋር ሌሎችን የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሲያዝኑና ሲያለቅሱ አገኟቸው። ስለ ባዶው መቃብርና ስለ መላእክት መታየት፣ ከመልአኩ ስለ ተሰጠውም መልእክት ሲሰሙ ደቀ መዛሙርቱ ተደናገጡ። ቀለዮጳ ከሰዓት በኋላ ከአንድ ጓደኛው ጋር ወደ ኤማሁስ ሲሄድ፣ ለማያውቀው አንድ መንገደኛ ማለት ለኢየሱስ፣ "ከእኛ ውስጥ ማልደው ከመቃብሩ ዘንድ የነበሩት አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን፤ ሥጋውንም ባጡ ጊዜ:- ሕያው ነው የሚሉ የመላእክትን ራእይ ደግሞ አየን ሲሉ መጥተው ነበር" በማለት የተናገረው (ሉቃ. 24፥22-23)፣ አራቱ ሴቶች ወደ ሰጡት ምስክርነት የሚያመለክት ይመስላል። ታሪኩን የሰሙት ተገረሙ፣ ነገር ግን ከዮሐንስ በቀር ገና አላመኑም፤ ዮሐንስ በመጀመሪያ ያገኘውን ዐይነ እምነት ለሌሎች አለመናገሩ የሚያስገርም አይደለም፤ ሕያው ከተባለው ከጌታችን ኢየሱስ ጋር እስካሁን ድረስ ማንም አልተገናኘም ነበርና።

ምንም እንኳ ጓደኞቻቸው ቃላቸውን ባያምኑም፣ አራቱ ሴቶች በዐደራ የተሰጣቸውን መልእክት በቢታንያ ለቈዩት ዘጠኝ ሐዋርያት እንዲነግሩ ፈጥነው ተነሡ። ከጌታቸው ጋር ብዙ ጊዜ በተራመዱበት መንገድ እየሄዱ ሳሉ፣ "እነሆ ኢየሱስ አገኛቸውና፣ ደስ ይበላችሁ (ሰላም ለእናንተ ይሁን! አ.መ.ት.) አላቸው"፤ ማቴ. 28፥9። ሴቶቹ ወዲያው የሰሙትን የዐጸፋ ምላሽ እንመልከት፤ "እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት"፤ ይህ ዐጸፋ እምነትና አክብሮት ይታዩበታል።

"አትንኪኝ" ብሎ ለመግደላዊት ማርያም የተናገረው ጌታችን ኢየሱስ እንዳይነኩት ሌሎቹን ሴቶች ለምን አልከለከለም? የእነርሱ ሁኔታ ከማርያም ሁኔታ የተለየ ነበረ። ማርያም ስለ ሞተው የኢየሱስ ሥጋ ከመጨነቅ ገና አልተላቀቀችም ነበር፤ እንግዲህ ኢየሱስ ከእርሷ ጋር በተገናኘ ጊዜ፣ ከሙታን ተነሥቶ በቅርብ ጊዜ ወደ አብ እንደሚያርግ፣ ከዚያም ጀምሮ በአካላዊ ደረጃ ሳይሆን በመንፈሳዊ ደረጃ ከ"ወንድሞቹ" እና ከ"እኅቶቹ" ጋር እንደሚገናኝ ማርያምን ለማስተማር ጀመረ። ከዚያም በኋላ የነገራትን ለሌሎች ደቀ መዛሙርት እንድትነግራቸው ላካት። አራቱ ሴቶች የተሰጣቸውን መልእክት ከመልአኩ ተቀብለው ነበር። ግራ እየተጋቡ በድንጋጤና በደስታ

ተሞልተው መልአኩን ታዝዘው በዮሐንስ ቤት ወደሚገኙት ደቀ መዛሙርት ሄዱ፤ አለማመናቸው ዝም አላሰኛቸውም ነበር፤ በዚህ ጊዜ ሌሎቹን ሐዋርያት ለመፈለግ በመንገድ ላይ ነበሩ። ባገኙት ከፊል ማስተዋል መታዘዝ ጀምረዋል፤ ጌታችን ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር በተገናኘ ጊዜ ለነበራቸው እምነት ዋጋ ሰጠ። ከሙታን የተነሣው ጌታ ራሱ በመልአክ የተነገራቸውን፣ ለሌሎቹም የሚያሳውቁትን የመልእክት እውነተኛነት አረጋገጠላቸው፤ "እትፍሩ ሄዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ፣ በዚያም ያዩኛል አላቸው"፤ ማቴ. 28÷10። ሴቶቹም በደስታ ተሞልተው ወደ ቢታንያ ሮጠው በመሄድ እንደ ደረሱ ለዘጠኝ ሐዋርያትና ከእነርሱ ጋር ለነበሩት፣ ትንፋሽ እያጠራቸው ታሪኩን እንደ ነገሯቸው ልንገምት እንችላለን።

እዚህ ላይ አንድ ነገር ብናስታውስ ጥሩ ነው፤ ሕያው የሆነውን ኢየሱስን በመጀመሪያ ያዩት ሴቶች መሆናቸው ከእግዚአብሔር የተሰጠ እንዴት ታላቅ ዕድል ነበረ! መልአኩ፣ በኋላም የተነሣው ጌታ ኢየሱስ ራሱ ስለ ትንሣኤው የመጀመሪያ ምስክሮች እንዲሆኑ ዐደራ ለእነርሱ መስጠታቸው ታይቶ የማይታወቅ ክብር ነበረ። በዚያ ዘመን በአይሁድ ሕግ መሠረት የሴቶች ምስክርነት ተቀባይነት አልነበረውና በፍርድ ቤት ምስክርነት ለመስጠት መብት አልነበራቸውም፤ እግዚአብሔር ግን በዚህ ዓለም ዝቅ ያለውንና የተናቀውን ነገር እንደሚመርጥ ተናግሮአል፤ 1ቆሮ. 1÷28።

በመካከሉ መግደላዊት ማርያም ከሕያው ኢየሱስ ጋር ከተገናኘች በኋላ ቀጥታ ወደ ዮሐንስ ቤት ሳትሄድ አልቀረችም። እዚያም ከሙታን የተነሣውን ጌታ እንዳየችና የተናገራትንም ስትገልጽላቸው ገና በሐዘን ያሉና ያላመኑ ይመስላል። ቅዱስ ማርቆስ፣ "ከሳምንቱም በመጀመሪያው ቀን ማልዶ በተነሣ ጊዜ፣ አስቀድሞ ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለመግደላዊት ማርያም ታየ። እርሷ ሄዳ ከእርሱ ጋር ሆነው ለነበሩት ሲያዝኑና ሲያለቅሱ ሳሉ አወራችላቸው፤ እነርሱም ሕያው እንደ ሆነ ለእርሷም እንደ ታያት ሲሰሙ አላመኑም" ብሎአል፤ ማር. 16÷9-11። ዮሐንስ ግን የማርያምን ምስክርነት ከቶ አልረሳውም። ቄይቶ ከሙታን የተነሣው ኢየሱስ መታየት በሐዋርያትና በሌሎች ደቀ መዛሙርት ከተረጋገጠ በኋላ፣ ዮሐንስ በጻፈው ወንጌል በኢየሱስ

ከተደረጉ ድንቅ ምልክቶች ሁሉ ይልቅ ታላቅ ለሆነው፣ ማለት ከሙታን ለመነሣቱ፣ የተሰጠ አንዱ ማስረጃ እንዲሆን በማርያም ታሪክ ተጠቀመበት። ለሌሎቹ ሴቶች ምን እንደ ተደረገ ሰምታ፣ ጌታችን ኢየሱስ የሰጣትን ተልእኮ ገና እንዳልጨረሰች ስላወቀች፣ ወደ ቢታንያ ተከትላቸው ለመሄድ ወሰነች? ሄዳለች ብለን እናስብ! ሙሉ ቀን ስለ ነበረ በደንብ በምታውቀው መንገድ ብቻዋን ለመሄድ በዚህ ጊዜ እንድትፈራ የሚያደርጋት ምንም ምክንያት ሊኖራት አይችልም። በመንገድ ላይ እንደ ገና ከኢየሱስ ጋር ሳትገናኝ፣ አራቱ ሴቶች ታሪኩን ተናግረው እንደ ጨረሱ ደረሰች። መግደላዊት ማርያም ከሌሎቹ ሴቶች በፊት ገና በአትክልቱ ስፍራ በነበረች ጊዜ፣ ከሙታን ከተነሣው ኢየሱስ ጋር እንደ ተገናኘች በደስታ አወራችላቸው፤ ኢየሱስ ያቀረበላቸውንም መልእክት አስታወቀቻቸው። በቢታንያ የነበሩት ሐዋርያት ግን እንደ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት፣ "ሴቶቹ የተናገሩት ቃል መቀባዠር ስለ መሰላቸው አላመኗቸውም"፤ ሉቃ. 24÷11 አ.መ.ት.።

ይሁን እንጂ ሐዋርያት፣ ከሰዓት በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው በመሄድ፣ እራት በአንድነት እንዲበሉ ጴጥሮስን፣ ዮሐንስንና በአጠቃላይ ከሐዋርያት ጋር ቅርብ ግንኙነት የነበራቸውን ደቀ መዛሙርት ለመሰብሰብ ወሰኑ። ባለፈው ሁለት ወይም ሦስት ቀን ውስጥ በዮሐንስ ቤት ብዙ መግባትና መውጣት ስለ ታየ፣ መገናኛ እንዲሆንላቸው የማርቆስን ቤት ሳይመርጡ አልቀሩም። እዚያም ጌታችን ከመሞቱ በፊት የፋሲካን እራት ዐብረው በልተው ነበር። በዚያ ሰፍራ በሮቹን ቆልፈው ከአይሁድ የሃይማኖት መሪዎች ተደብቀው በዕለቱ ስለ ተፈጸመው ሁሉ በሰላም ሐሳብ ለሐሳብ መለዋወጥ ይችላሉ። ምናልባት በቢታንያ ጥቂት ካረፉና ምሳ ከበሉ በኋላ፣ እራት እንዲያዘጋጁ ሴቶቹ ከወንዶች ጥቂት ጊዜ ቀድመው ከቢታንያ ተነሡ።

ቅዱስ ማቴዎስ በኋላ የአራቱን ሴቶች ምስክርነት አስታውሶ፣ ክርስቶስ ከሙታን በተነሣበት ጊዜ ከመረጣቸው ጥቂት ክሥተቶች አንዱ የሆነውን ታላቁ ተልእኮን የሚያቀርበው ለወንጌሉ መደምደሚያ እንደ መግቢያ እንዲያገለግል ማድረጉ፣ በሴቶቹ ምስክርነት ልቡ እንደ ተነካ ያሳያል። የኢየሱስ ለሴቶች መታየት ከሙታን የተነሣው

ኢየሱስ፣ ከሌሎች ስለ ትንሣኤው ታዝዘው ከሚናገሩት ጋር ዐብሮ እንደሚገኝ ከሚገልጸው ወንጌል መደምደሚያ ዋና መሪ ሐሳብ ጋር በደንብ ይስማማል። ታላቁን ተልእኮ ስንመረምር ወደዚህ ነገር እንመለሳለን። ዛሬም ሕያው የሆነው ጌታችን፣ ወንጌሉን ገና በግልጽ ባያስተውሉም፣ ለሰሙት ወደሚታዘዙና እስከዚህ ጊዜ ድረስ ስለ እርሱ የተረዱትን ለሌሎች ወደሚያስተላልፉት ሰዎች ይመጣል። በመንገድ ላይ ሳሉ፣ "እነሆ ኢየሱስ አገኛቸው" የሚለው በእውነት፣ "እነሆ ኢየሱስ አንባቢውን አገኘው" ወደሚለው ተግባራዊ ቃል ሊለወጥ ይችላል።

ለእሑድ ማታ ስለ ታሰበው ማዕድና ስብሰባ ከማተታችን በፊት፣ የሐዋርያው ጴጥሮስንና የቀለዮጳን ታሪክ ለመከታተል ለትንሽ ጊዜ ወደ ዮሐንስ ቤት እንመለሳለን።

3. ለሐዋርያው ጴጥሮስ

ጴጥሮስ በመቃብሩ ውስጥ የበፍታ ልብሱን አቀማመጥ በማየት እየተገረመ ወደ ቤት እንደ ተመለሰ አይተናል። በአራቱ ሴቶች አማካይነት ከመልአኩ የተነገረው "ለጴጥሮስም" የሚለው የተጨመረው ቃል ጌታውን በመካድ የተሰማውን ኀዘን በመጠኑ ሳያቃልልለት አልቀረም። ቀጥሎም ከመግደላዊት ማርያም የሰማው ምናልባት ዐዲስ ተስፋ ጨምሮለት ነበር። ጌታ ኢየሱስ በርግጥ ሕያው ከሆነ፣ ከጴጥሮስ ጋር ለመገናኘት ፈቃደኛ ይሆናልን? ከሆነም ጴጥሮስን ቢወቅሠው አያስገርምም። ምናልባት ከቢታንያ ከተመለሱት ሴቶች ኢየሱስ ስለ መታየቱ ካወቀ በኋላ፣ ከማታው ቀጠሮ በፊት ያየውንና የሰማውን ለማሰላሰል በብዙ ሕዝብ ወደ ተሞላው ወደ ዮሐንስ ቤት ከመሄድ ቀርቶ፣ ጌታ ኢየሱስ ዘወትር ወደሚሄድበት የአትክልት ስፍራ ወደ ጌቴሴማኒ ለመግባት ወይም ወደ ደብረ ዘይት ለመውጣትና በእዚያ ጊዜ ለማሳለፍ እንደ ወሰነ ልንገምት እንችላለን። ያም ሆነ ይህ ከሙታን የተነሣው ኢየሱስ ለጴጥሮስ ታየ። በሚያስደስተውና በሚያሳዝነው በዚያ ግንኙነትም ምን እንደ ተከሠተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተመዘገበም፤ የምናውቀው፣ ንስሓ በገባው፣ ራሱን ዝቅ ባረገው ደቀ መዝሙር በጴጥሮስና በርኅራኄና በፍቅር በተሞላው

በተወደደው ጌታ መካከል የነበረው ለጊዜው የተበላሸ ግንኙነት መፈወሱን ብቻ ነው። ከብዙ ዓመታት በኋላ ጴጥሮስ ለሚጽፍላቸው ክርስቲያኖች በዚህ ወቅት ለራሱ ለጴጥሮስ የሚስማማ ተገቢ ቃል ነው፤ "እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና፣ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል"፤ 1ጴጥ. 2፥25። ከሰው ሁሉ ባይሆንም ከሌላ ሐዋርያ ሁሉ በፊት ኢየሱስ በልቅሶና በብስጭት ላይ ይገኝ ለነበረው ለጴጥሮስ በመታየት፣ ያደረገለት ምሕረት ምን ያህል ታላቅ መሆኑን ያሳያል። እውነት ነው፤ መሪ እንዲሆን በኢየሱስ የተመረጠው ጴጥሮስ ከጌታው ጋር የነበረው የተበላሸ ግንኙነት እንዲስተካከል አስፈላጊ መሆኑን ልናስተውል እንችላለን። ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ የታያቸውን ሰዎች በዘረዘረ ጊዜ፣ ከሁሉ አስቀድሞ "ለኬፋ" እንደ ታየ ጻፈ፤ 1ቆሮ. 15፥5። "ኬፋ" የሚለው የአራማይክ ቃልና "ጴጥሮስ" የሚለው የግሪኩ ትርጉም "ዐለት" ማለት ሲሆን፣ ጌታ ኢየሱስ ለዐዲሱ ሕይወትና አገልግሎት የሰጠው ስም ነበረ። እሑድ ማታ፣ ሌሎች ሐዋርያት ጌታችን ኢየሱስ ለጴጥሮስ እንደ ታየ በተናገሩ ጊዜ፣ "ጌታ በእውነት ተነሥቷል ለስምዖንም ታይቷል" አሉ፤ ሉቃ. 24፥34። ስምዖን ከመጀመሪያ ጀምሮ የጴጥሮስ የቤተ ሰብ ስም ነበረ።

ሕያው የሆነው ጌታችን ኢየሱስ በዘመናችን በጎጢአት ወድቀው ተስፋ ወደ ቈረጡትና ወደ ዐዘኑት አገልጋዮቹ ለመምጣት ይወዳል። ንስሓ ሲገቡ፣ በጸጋ የተሞላው ጌታችን ኢየሱስ ፍቅሩንና ርኅራኄውን አፍስሶ ኀጢአታቸውን ሊሰርይላቸውና ሊፈውሳቸው ይችላል፤ የሞተው ከኀጢአታቸው ሁሉ እንዲያነጻቸው ነውና። ከእነዚህ ከወደቁት ደቀ መዛሙርት መካከል አንባቢው አንዱ እርሱ እንደ ሆነ ቢሰማው፣ በርጢሜዎስ ለተባለው ዐይነ ስውር "አይዞህ፤ ተነሥ፤ ይጠራሃል!" (ማር. 10፥49 አ.መ.ት.) ተብሎ የተጻፈው የፍቅርና የርኅራኄ ቃል ለልቡ ይናገር።

4. ለቀለዮጳና ለጓደኛው

ከዮሐንስ ቤት የምንመለከተው ሌላ ሰው ቀለዮጳ ነው። የሁለተኛዪቱ ማርያም ባል፤ የታናሹ የሐዋርያው ያዕቆብና የዮሳ አባት

እንደ ሆነ ይታሰባል። በተጨማሪ ቀለዮጳ የቅድስት ድንግል ማርያም ዕርኛ የዮሴፍ ወንድም መሆኑ ይታወቃል[12]፤ በጥንታ ቤተ ክርስቲያን በታሪክ ጸሓፊው አውሳብዮስ የተጠቀሰውና በ2ኛው ክፍለ ዘመን ይኖር በነበረው የታሪክ ጸሓፊ ሄጂሲጶስ ይህ ሐሳብ ተጽፎ ነበር። እንደዚያም ከሆነ፣ ቀለዮጳ የጌታችን ቅርብ የቤተ ሰብ አባል በመሆን የአባወራነት ኀላፊነት ነበረው ማለት ይቻላል። የሁለተኛዪቱ ማርያም ባል ቀለዮጳ (ቀልዮጳ አ.መ.ት.) እና ወደ ኤማሁስ የሄደው ቀለዮጳ አንድ መሆናቸውን እንድናምን ጥሩ ምክንያት ነው። በዚህ መሠረት ላይ ጌታችን ከተነሣ ጥቂት ጊዜ በኋላ ለእርሱ መታየቱን በደንብ ልናስተውል እንችላለን። በጌታችን እናት ቤተ ሰብና በዮሴፍ ቤተ ሰብ መካከል ይህ ቅርብ የሆነ ዝምድና ከመኖሩ የተነሣ፣ በታላቁ ሐዘናቸው ጊዜ ዐብረው በዮሐንስ ማለት በወላጆቹ በዘብዴዎስና በሰሎሜ ቤት በአንድነት መገኘታቸው ግልጽ ነው።

የሁለተኛዪቱ ማርያም ባል ቀለዮጳ የቤተ ሰብ አባል እንደ መሆኑ የልዩ ልዩ ሰዎችን ማለት የመግደላዊት ማርያምን፣ የጴጥሮስን፣ የዮሐንስንና የሌሎቹን ሴቶች (የራሱን ሚስት ማርያም ጭምር) መግባትና መውጣት በዐይን አይቶ እንደ መሰከረ ተገንዝበናል። በሉቃስ ወንጌል የተጻፉት ዝርዝር ሐሳቦች ከዚህ ሐሳብ ጋር ይስማማሉ። "ከእኛ ውስጥ... የነበሩት አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን... ሕያው ነው የሚሉት የመላእክትን ራእይ ደግሞ አየን ሲሉ..." ተብሎ ተጽፎአል፤ "ከእኛም ጋር ከነበሩት" በማለት ጴጥሮስ ብቻውን ወደ መቃብር አለመሄዱን ቀለዮጳ ያሳስባል፤ "እርሱን ግን አላዩትም" ብሎ የተናገረውም፣ ኢየሱስን ያየችው ስለ መሆኗ አስደናቂውን የመግደላዊት ማርያምን ታሪክ እንደ ሰሙ ፍንጭ ይሰጠናል።

ስም ሳይጠቀስ የቀለዮጳ ጓደኛው የተባለው ማን ይሆን? ጌታችንን በፊት ያየችው የቀለዮጳ ሚስት አትመስልም፤ እርሷ ኢየሱስን አይታ አላወቀችውም ነበርን? የቀለዮጳና የማርያም ልጅ ዮሳም ይሆን? በኤማሁስ የነበረው ቤት፣ በኢየሩሳሌም ከዘመዶቻቸው ጋር ይገናኙ ዘንድ ለተወሰነ ቀን ለቅቀውት የነበረ የነቀለዮጳ ቤት ሳይሆን ይቀርን?

[12] J. Wenham "Easter Enigma" ገጽ 37-38።

ሌሎቹ እንደሚያስቡት፣ ከቀለዮጳ ጋር የሄደው፣ በትሕትና ስሙን ያልጠቀሰው የወንጌል ጸሓፊው ሉቃስ ነበረ። ታሪኩ በጣም ጉልሕ በመሆኑና በዐይን ምስክር የተጻፈ ስለሚመስል ይህ አስተሳሰብ አንባቢን የሚስብ ነው፤ ይህም፣ በኤማሁስ የነበረው ቤት የቅዱስ ሉቃስ እንደ ሆነ የሚጠቁም ነው። ይሁን እንጂ ማረጋገጫ ስለሌለን በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምናነበው የሁለተኛው መንገደኛ ስም አለመጠቀሱ የተሻለ አቀራረብ ነው።

ኤማሁስ ከኢየሩሳሌም ዐሥራ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል የሚርቅ መንደር እንደ ነበረ ከታሪኩ መጀመሪያ እናውቃለን፤ ሉቃ. 24፥13 አ.መ.ት.፤ መንደሩ በረጅም የዓለም ታሪክ ሂደት ስለ ጠፋ፣ ቦታውን ግን በትክክል የት እንደሚገኝ ማወቅ አንችልም። የ"ኤማሁስ" ትርጉም "ፍል ውሃ የሚገኝበት ቦታ" ስለ ሆነ፣ ድሮ በፈውስ ምክንያት የታወቀ መንደር ሳይሆን አልቀረም። በዐጭሩ በሉቃ. 24፥13-35 የተጻፈው አስደናቂ ታሪክ አከፋፈል (እንደ አ.መ.ት.) እንደሚከተለው ነው:-

ቁ. 13-15 ሁለቱ ደቀ መዛሙርት በኢየሩሳሌም ስለ ተፈጸመው ሁሉ ሲነጋገሩ፣ ኢየሱስ ከበስተ ኋላቸው መጥቶ ሳያውቁት ከእነርሱ ጋር ይራመድ ጀመር።

ቁ.17 <u>የኢየሱስ የመጀመሪያ ጥያቄ</u>፣ "እየሄዳችሁ፣ መንገድ ላይ እርስ በርስ እንዲህ የምትወያዩት ምንድን ነው?"

ቁ.18 <u>የዋናው ተናጋሪ የቀለዮጳ መልስ</u>፣ "በእነዚህ ቀናት እዚህ በኢየሩሳሌም የሆነውን ነገር የማታውቅ፣ አንተ ብቻ ለአገሩ እንግዳ ነህን?"

ቁ.19 <u>የኢየሱስ ሁለተኛ ጥያቄ</u>፣ "የሆነው ነገር ምንድን ነው?"

ቁ.19-24 <u>የቀለዮጳ መልስ</u>፣ ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ አገልግሎትና ስለ ደረሰበት መከራና ሞት፣ ደቀ መዛሙርቱ በእርሱ ስለ ነበራቸው ተስፋ፣ በሦስተኛው ቀን ወደ መቃብር የሄዱት ሴቶችና ሌሎች ሰዎች የተናገሩትን የሚያውቅ መሆኑን ያብራራል። "ሥጋውንም ባጡ ጊዜ..."፣ "እርሱ

በሕይወት እንዳለ የነገሯቸውን መላእክት በራእይ እንዳዩ አወሩልን”፣ “እርሱን ግን አላዩትም” በማለት የተናገረው፣ ምንም እንኳ እርሱና ጓደኞቹ የተከሠተውን በቅርብ ቢከታተሉም፣ ምን ያህል ግራ እንደ ገባቸው ያሳያል።

ቊ.25-27 <u>የኢየሱስ ወቀሣና ትምህርት</u>፣ “እናንተ የማታስተውሉ ሰዎች፣ ልባችሁም ነቢያት የተናገሩትን ሁሉ ከማመን የዘገየ፣ ክርስቶስ ይህን መከራ መቀበልና ወደ ክብሩም መግባት አይገባውምን?” በማለት ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እርሱ የተጻፈውን አስረዳቸው።

ቊ.28-31 <u>የኢየሱስ መገለጥና መሰወር</u>፣ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ከእነርሱ ጋር እራት እንዲበላ አጥብቀው ሲጋብዙት፣ ከእነርሱ ጋር በማእድ ተቀምጦ ዳቦ በቈረሰ ጊዜ ወዲያው ዐይናቸው ተከፈተ ዐወቁትም። ያወቁትም፣ ኢየሱስ መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው መከራ እንደ ተቀበለው፣ ከሙታን በመነሣቱ ወደ ክብሩ መግባት እንደሚጀምረው ክርስቶስ ነው። እርሱም ወዲያው ከእነርሱ ተሰወረ።

ቊ.32-35 <u>የእነርሱ ዐጸፋ ምላሽ</u>፣ “በመንገድ ሳለን፣ እያነጋገረን ቅዱሳት መጻሕፍትንም ገልጦ ሲያስረዳን፣ ልባችን እንደ እሳት ይቃጠልብን አልነበረምን?” እየተባባሉ፣ ምንም እንኳ ምሽት ቢሆንም ሌሎቹን ደቀ መዛሙርት ለማግኘት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።

ቅዱስ ሉቃስ ይህን ታሪክ በዝርዝር የገለጸው፣ ለእርሱ ዐላማ ቊልፍ ስለ ነበረ ነው። በታሪኩ ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ነገሮችን እንረዳለን፤ የመጀመሪያው፣ በተነሣው ክርስቶስና በቅዱሳት መጻሕፍት መካከል ባለው ቅርብ ግንኙነት ላይ ያተኵራል። ሕያው የሆነውን ኢየሱስን እንዲያውቅ ሰውን የሚያዘጋጀው፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እርሱ የተጻፈውን ሰው ማስተዋል ሲጀምር ነው። ሴቶቹ ወደ መቃብሩ በሄዱበት ጊዜ፣ በመልአኩ ከተሰጠው መልእክት፣ “እዚህ የለም፤

ደግሞም በገሊላ በነበረ ጊዜ ምን እንዳላችሁ አስታውሱ” ብሎ በተለይ የጠቀሰው ሉቃስ ነው። በሉቃስ አመለካከት ሕያው የሆነው ክርስቶስና የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት (ነቢያት ወይም ክርስቶስ ራሱ የነቢያትን ቃል ለማረጋገጥ የተናገረው ቃል) ለወንጌል መስፋፋት መሠረታዊ መንፈሳዊ ሐቅ ነው። ይህ ታሪክ በሉቃስ ትርጉም መሠረት ለሐዋርያት ለተሰጠው ታላቁ ተልእኮና በሐዋርያት ሥራ በሉቃስ ስለ ወንጌል መስፋፋት ለተመዘገበው ታሪክ ሁሉ መንገዱን ያዘጋጃል።

ታሪኩ ሁለተኛውን ነገር የሚያስረዳን፣ በመጻሕፍት ጭምር ከሙታን የተነሣው ጌታ በፊቱ ለሚገኝ ሰው በአንድ የታወቀ ምልክት ራሱን ገለጠ፤ ለምሳሌ፣ ለመግደላዊት ማርያም፣ ስሟን በመጥራት ነበረ የተገለጠው፤ በኤማሁስ ደግሞ እንጀራን በመቊረስ። ሁለቱ ጓደኞች በደቀ መዛሙርት ፊት እንጀራን ሲቈርስ ስንት ጊዜ አይተውት ነበር? ሰዎቹ የተነሣውን ኢየሱስን ለምን ወዲያው አላወቁትም ብለን እንጠይቅ ይሆናል፤ ከትንሣኤው በኋላ የተወሰነ ለውጥ በመኖሩ? ወይስ በመጻሕፍት የተጻፈውን ሰዎቹ ባለማስተዋላቸው? ወይስ ደግሞ የእምነት ጕድለት ስለ ነበረ ነው? ሊያውቁት ያልቻሉት በሦስቱ ምክንያቶች ሳይሆን አይቀርም። አንድ ነገር ግልጽ ነው፤ ዐይናቸው ሲከፈት በተሰጣቸው ጸጋ እንጂ በራሳቸው ችሎታ ወይም መንፈሳዊነት አላወቁትም። የተሰጣቸው ጸጋ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን ቅዱስ ሉቃስና ቅዱስ ዮሐንስ በማብራራት ለበዓለ ኀምሳ ያዘጋጁናል።

ዛሬ ሕያው ስለ ሆነው ክርስቶስ ግራ የምንጋባ ሰዎች ምን ማድረግ እንደሚያስፈልገን ይህ ታሪክ ያስተምረናል። ስለ ክርስቶስ በተጻፉ በብሉይና በዐዲስ ኪዳናት ብንጀምር መልካም ነው፤ ይህን ስናደርግ ልባችን እንደ እሳት ሊቃጠልብን ይችላል። ወደ ኤማሁስ የተጓዙ ሁለቱ ጓደኞች ወደ ቤታቸው እንዲገባ ገና ያላወቁትን ኢየሱስን እንደ ጋበዙት ሁሉ፣ እኛም ወደ ሕይወታችን እንዲገባ የሕይወታችንን በር እንክፈትለት፤ ራእ. 3፥20። የቤተ ክርስቲያን አባሎች ከሆንን፣ ክርስቶስ እንዳዘዘን ወደ መሥዋዕታዊ ሞቱ የሚያመለክቱትን ጎብስቱንና ወይኑን በመቀበል እርሱን ማስታወስ እንችላለን። መንፈስ

ቅዱስ ዐይናችንን እንዲከፍትልን እግዚአብሔርን እንጠይቅ፤ “እናንተ ትሹኛላችሁ፣ በፍጹም ልባችሁ ከሻችሁኝ ታገኙኛላችሁ” ተብሎ የተጻፈው እግዚአብሔር የሰጠው የተስፋ ቃል ጸንቶ የሚኖር ነውና፤ ኤር. 29፥13!

5. በመጀመሪያ በማርቆስ ቤት - ለ“ዐሥራ አንዱ” መታየቱ

ቀለዮጳና ጓደኛው የከተማዪቱ በሮች ሌሊት ሳይዘጉ ገብተው ወደ ማርቆስ ቤት ደረሱ፤ “ዐሥራ አንዱና ከእነርሱ ጋር የነበሩትም:- ጌታ በእውነት ተነሥቶአል ለስምዖንም ታይቶአል እያሉ በአንድነት ተሰብስበው አገኙአቸው”፤ ሉቃ. 24፥34። ምናልባት ደቀ መዛሙርቱ ሴቶች ከተናገሯቸው ቃላት ይልቅ እንደ መሪ የሚቆጠረው ሐዋርያው ጴጥሮስ በተናገራቸው ቃላት ለማመን ቀለላቸው! ቢሆንም በመካከላቸው የተሰጡ የወጸፋ ምላሾች ድብልቅ ሐሳብ እንደ ነበሩባቸው፣ በኤማሁስ የሆነውን ቅዱስ ማርቆስ የጻፈው ሐተታ ያሳያል፤ “ከዚህም በኋላ ከእነርሱ ለሁለቱ ወደ ባላገር ሲሄዱ በመንገድ በሌላ መልክ ተገለጠ፤ እነርሱም ሄደው ለሌሎቹ አወሩ፤ እነዚያንም ደግሞ አላመኑአቸውም”፤ ማር. 16፥12-13። ቅዱስ ሉቃስ ግን፣ “እነርሱም በመንገድ የሆነውን እንጀራውንም በቈረሰ ጊዜ እንዴት እንደ ታወቀላቸው ተረኩላቸው” በማለት፣ ቀለዮጳና ጓደኛው የተናገሩት፣ የጴጥሮስን ምስክርነት በመደገፍ ተቀባይነት ያገኘ ሊመስለን ይችላል፤ ሉቃ. 24፥35። ባለፈው ሐሙስና ዐርብ የነበረውን የጭንቀት ጊዜ ባሳለፉት፣ እሑድ በተፈጸሙ ከሥተቶችም በልዩ ልዩ ደረጃ በተሳተፉ ሰዎች መካከል የተለያዩ፣ የሚፃረሩ ስሜቶችም እንኳ ቢታዩ አያስገርምም። በዚህኛው እሑድ ማታ ለመጀመሪያ ጊዜ ለብዙዎች ሲታያቸው፣ ሉቃስ፣ “እነርሱም ከደስታ የተነሣ ገና ሰላላመኑ ሲደነቁ ሳሉ” ብሎ፣ አለማመን አንዳንድ ጊዜ በአሉታዊ ሳይሆን በአዎንታዊ መንፈስ የሚከሠት መሆኑን ያሳስበናል፤ ሉቃ. 24፥41።

እሑድ ማታ ስንት ሰዎች ተገኙ? ከአስቆሮቱ ይሁዳ በተጨማሪ ቶማስ በአንድ ምክንያት እንዳልተገኘ ዮሐንስ ያስረዳናል፤ የእርሱ አጻጻፍ በዐሥሩ ሐዋርያት ላይ ያተኮራል። ሉቃስ፣ ቀለዮጳና

ባልንጀራው ዐሥራ አንዱንና ከእነርሱ ጋር የነበሩትን በአንድነት ተሰብስበው እንዳገኙአቸው ገልጾአል። ሐዋርያው ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ዐሥር መግለጫ፣ ጌታ በኢየሩሳሌም ለሐዋርያት ሁለት ጊዜ መታየቱን አጣምሮ፣ “ለኬፋም ታየ በኋላም ለዐሥራ ሁለቱ” ይላል፤ 1ቆሮ. 15፥5። “ዐሥራ ሁለቱ” ወይም ከይሁዳ ሞት በኋላ በልዩ ልዩ ጊዜ “ዐሥራ አንዱ” የሚለው ሐረግ ሐዋርያትን በአንድነት የሚያመለክት አባባል መሆኑን መረዳት አለብን። የሚገኙት ዐሥራ ሁለት፣ ዐሥራ አንድ፣ ዐሥር ወይም በቢታንያ የተገኙት ዘጠኝ ቢሆኑ፣ አባባሉ የቡድን መግለጫ እንጂ አቈጣጠርን የሚያሳይ አልነበረም።

እሑድ ማታ ኢየሱስ ስለ መታየቱ በሉቃስና በዮሐንስ የተጻፉትን የተለያዩ ታሪኮች እዚህ ላይ ጨምረን እንመለከታለን:-

ሉቃስ 24፥36-43	ዮሐንስ 20፥19-23
ይህንም ሲነጋገሩ ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ:- ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ነገር ግን ደነገጡና ፈሩ መንፈስም ያዩ መሰላቸው። እርሱም:- ስለ ምን ትደነግጣላችሁ? ስለ ምንስ ዐሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፣ መንፈስ ሥጋና ዐጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው። ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው። እነርሱም ከደስታ የተነሣ ገና ሰላላመኑ ሲደነቁ ሳሉ:- በዚህ አንዳች የሚበላ አላችሁን? አላቸው። እነርሱም ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቍራጭ፣ ከማር ወለላም ሰጡት፤ ተቀብሎም በፊታቸው በላ።	ያም ቀን እርሱም ከሳምንቱ ፊተኛው በመሸ ጊዜ፣ ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበት፣ አይሁድን ስለ ፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ፣ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ:- ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ይህንም ብሎ እጆቹንም ጐኑንም አሳያቸው። ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው። ኢየሱስም ዳግመኛ:- ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው። ይህን ብሎ እፍ አለባቸውና:- መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኀጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቅርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው።

ሁለቱን ታሪኮች ስንመለከት፣ ቀለዮጳ ታሪኩን ከመጨረሱ በፊት የተቈለፉት በሮችም ሳይከፈቱ በድንገት ጌታችን ኢየሱስ መጥቶ በመካከላቸው ቆመና “ሰላም ለእናንተ ይሁን” አላቸው። ማርቆስ

“በማዕድ ተቀምጠው ሳሉ” ይላል፤ ማር. 16፥14። እነርሱ ግን ደንግጠው በፍርሀት ተዋጡ፤ መንፈስም ያዩ መሰላቸው። እርሱም ስላለማመናቸውና ስላለማስተዋላቸው ወቀሣቸው፤ እንዲህም አላቸው፣ “ስለ ምን ትደነግጣላችሁ? ስለ ምንስ ሐሳብ በልባችሁ ይነሣል? እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፣ መንፈስ ሥጋና ዐጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው።” ቀጥሎም እጆቹንና እግሮቹን ብቻ ሳይሆን ልብሱንም ከፍቶ የቈሰለውን ጐኑን አሳያቸው። እነርሱም በደስታና በድንጋጤ ገና ስላላመኑ፣ ኢየሱስ በተለመደው ድምፁ፣ “በዚህ እንዳች የሚበላ አላችሁን?” አላቸው። እነርሱም ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቍራሽ ሰጡት፤ እርሱም ተቀብሎ ቀስ ብሎ በፊታቸው በላ።

ሉቃስና ዮሐንስ ሁለቱም በኢየሱስ አካላዊነት ላይ ያተኵራሉ። ሊዳሰስ ይችል ነበር፣ ሥጋና ዐጥንት ነበረው በፊታቸውም በላ። ቢሆንም አካሉ የተለወጠ ነበረ፤ ሲፈልግ መታየትና መሰወር፣ በተቈለፉት በሮች በኩል ማለፍ፣ ስበትን አሸንፎ ወደ አየሩ መውጣት የሚችል አካል ነበረው። ቢሆንም የተቀበረው አካል በዐዲስ መልክ የተለወጠ እንጂ ሌላ አካል አልነበረም። የእግዚአብሔር ዐዲስ ፍጥረት በዓለም መጀመሪያ ከምንም የተፈጠረ ሳይሆን አስቀድሞ የተሠራው ነገር ግን የተለወጠው ፍጥረት ነውና። ቅዱስ ሉቃስ አሁን ከፋሲካ እስከ በዓለ ኀምሳ ያሉ ኀምሳ ቀኖችን በዐሥር ቍጥሮች በዐጭሩ ያጠቃልላል። በአንድ በኩል በዚያ ጊዜ ውስጥ ጌታችን የሰጠውን ትምህርትና ደቀ መዛሙርቱ በማስተዋል እያደጉ መሄዳቸውን በዐጭሩ ያቀርባል። ሁለቱም ማለት የጌታችን ትምህርትና የሐዋርያት የማስተዋል እድገት የተጀመሩት እሑድ ማታ፣ ኢየሱስ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ወደ ወንጌል ሥርጭት ስለሚመሩት መከራን ስለ መቀበሉና ከሙታን ስለ መነሣቱ የተጻፈውን እንዲያስተውሉ፣ አእምሮአቸውን በከፈተበት ጊዜ ሲሆን፣ ፍጻሜ ያገኙትም ከዕርገት ቀን በኋላ ከአብ የተላከውን ተስፋ መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ጎይልን እስኪያገኙ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቈዩ በሰጣቸው ትእዛዝ ነው። በሌላ በኩል ሉቃስ ስለ ጌታችን ዕርገትና በሚከተሉት ቀኖች ደቀ መዛሙርት ጊዜውን እንዴት እንዳሳለፉት በዐጭሩ ይናገራል፤

በክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት መካከል የሆነው ሁሉ በአንድ ቀን ወይም በአንድ ቀንና ሌሊት እንደ ተፈጸመ ግን አያስተምርም፤ ይህንም ሉቃስ ከጻፈው ሁለተኛ መጽሐፉ ከሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 1 ጋር አገናዝበን ልናስተውለው እንችላለን።

እሑድ ማታ ወደ ተሰበሰቡት ደቀ መዛሙርት እንመለስ። ወንጌልን መስበክ ማለት፣ ለአሕዛብ ሁሉ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ላይ የተመሠረተውን የኀጢአት ስርየት ንስሓ ለሚገቡት ማወጅ ማለት መሆኑን ካስረዳቸው በኋላ፣ ጌታችን ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በእርሱ የተላኩ ምስክሮች መሆናቸውን አሳሰባቸው፤ ቅዱስ ዮሐንስ ጌታ የተናገራቸውን ጽፎአል፤ “ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው”፤ ዮሐ. 20፥21። በኋላ የሚቀበሉት የእግዚአብሔር መንፈስ (እስትንፋስ) ምልክት እንዲሆንላቸው እፍ አለባቸው፤ ወንጌልን የሚሰብኩበት ጎይል የእርሱ ነውና። በመንፈስ ቅዱስ ጎይል ወንጌልን ለሚቀበሉት የኀጢአታቸውን ስርየት፣ ለማይቀበሉት ግን የኀጢአታቸውን ፍርድ ያቀርባሉ።

እሑድ ማታ የኢየሱስ በዚያ መታየት በዚህ ዘመን ለምንኖር ምን ያስተምራል?

- ክርስቶስ በተለወጠ ሁኔታ በአካል ከሙታን ተነሣ እንጂ አንዳንዶች እንደሚያስቡት፣ በመንፈስ ብቻ ሕያው አልሆነም።
- በፍርሀት ምክንያት ተቈልፎ ወደሚገኘው “እስር ቤት” ከሙታን የተነሣው ኢየሱስ ገብቶ፣ “ሰላም ለእናንተ ይሁን” ማለት ይችላል።
- ሐዋርያት መሪዎቻችን ቢሆኑ፣ ሁላችን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሆነን፣ ወንጌልን ለሌሎች ሰዎች እንድናቀርብ እንላካለን።
- የወንጌል ማስተማሪያ መጽሐፍ ቅዱስ፣ የወንጌል ማእከል ክርስቶስ፣ የወንጌል መሠረት የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ፣ የወንጌል ጥሪ ንስሓ መግባት፣ የወንጌል ተስፋ ቃል የኀጢአት ስርየት፣ የወንጌል ጎይል መንፈስ ቅዱስ፣ የወንጌል ኀላፊነት ሰዎች በዐጸፋ ምላሻቸው

መዳናቸው ወይም አለመዳናቸው እንደ ሆነ ካመንን፣ ምን ያህል የክርስቶስን ወንጌል ለሌሎች ሰዎች በማቅረብ ላይ ነን?

6. ከስምንት ቀን በኋላ ለ“ዐሥራ አንዱ” ሁለተኛ መታየቱ፤ ዮሐ. 20፥24-29

ቅዱስ ማቴዎስ ለሐዋርያት ስለ አንድ የጌታችን ኢየሱስ መታየት ጽፎአል፤ ይህም በገሊላ የሆነ ነበረ። ቅዱስ ማርቆስና ቅዱስ ሉቃስ ስለ ጊዜው ሁኔታ ምንም ሳይናገሩ፣ በኢየሩሳሌምና በአካባቢው ስለ መታየቱ ብቻ ተናግረዋል። ቅዱስ ዮሐንስ ግን፣ ዐሥራ አንዱ ወደ ገሊላ ከመሄዳቸው በፊት ቢያንስ ስምንት ቀን በከተማዪቱ ውስጥ እንደ ቈዩ ያስረዳናል። በፋሲካ ጊዜ ለሚገኙት መጻተኞች ይህ የተለመደ ነገር ነበረ፣ ፋሲካን ተከትለው የሚመጡ ስድስት የቂጣ ቀኖች ከበዓሉ ጋር አንድ ሆነው ይቈጠሩ ነበርና።

የሚከተለው የጌታችን የኢየሱስ መታየት ስለ እምነት ወደ ተሰጠ ትምህርት ማለት ወደ ቶማስ አለማመን የሚመራ ነው። “ጌታን አይተነዋል” ብለው ከሚመሰክሩ ሌሎች ሐዋርያት ጋር በተገናኘ ጊዜ ቶማስ፣ “የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጐኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው”፤ ዮሐ. 20፥25።

ቶማስ (በአራማይክ) ዲዲሞስ (በግሪክ) ሲሆን፣ ሁለቱም ቃላት “መንታ” የሚል ትርጕም ያላቸው ናቸው። በዮሐንስ ወንጌል ቶማስ የሚቀና፣ ለኢየሱስ ሲል ለመሞት ዝግጁ ሆኖ እንደሚቈጠር ቅን ሰው ይታያል፤ የነበሩትን ጥያቄዎችና ጥርጣሬዎች ለመናገር አይፈራም ነበር፤ ዮሐ. 11፥16፤ 14፥5። ትውፊት እንደሚመሰክረው፣ ቶማስ በኋላ በሕንድ አገርና ምናልባትም በጳርቴ አብያተ ክርስቲያናትን የሚያቋቁም ታላቅ ጎይል ያደረበት ሚስዮናዊ ሆነ። እንግዲህ ኢየሱስ ከሙታን የመነሣቱ እውነት ሲረጋገጥ፣ ቶማስ ገና ያልተገለጹ ታላላቅ ነገሮችን ከሌሎች ሐዋርያት ይልቅ የተረዳ መሆን ይችል ነበርን? ምናልባት ከእነርሱ ይልቅ፣ ታሪኩ ሁሉ ማለት ከመልእክት የተሰጠው መልእክት፣ የተጠቀሱት የኢየሱስ መገለጦች፣ እርሱን መዳሰስና ከእርሱም ጋር መነጋገር፣ ወይም አንድ ትልቅ ምናባዊ መገለጥ መሆኑ

ወይም ከሙታን ተነሥቶ ኢየሱስ ሕያው ከመሆኑ ይልቅ እጅግ በጣም ከፍ ያለ መገለጫን የሚያረጋግጥ እውነተኛ ክሥተት ነው፤ ይህም የሚያሳየው፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የተባለው መሲሑ ብቻ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን ነው። እንደዚህ ዐይነቱ እምነት፣ በሚዳሰስ፣ በማይጠረጠር ማስረጃ መሠረት ላይ ብቻ መሆን ይችላል፤ “የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጐኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው።” ጊዜው ሲደርስ፣ የተናገረውን ሁሉ የሰማው ኢየሱስ በፊቱ ሲታይ፣ ኢየሱስን ሳይዳሰሰውም እንኳ ነገሩ ተወሰነ፤ “ጌታዬ አምላኬም” ብሎ በአክብሮት በመናገሩ፣ በኢየሱስ ትምህርት ውስጥ ተደብቆ የቈየውን እውነት አሁን ገለጠው፤ የተናገረው የዐጸፋ ምላሽ የመጨረሻና እውነተኛ የክርስቲያን ሃይማኖት መግለጫ ነበረና! ስለ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ፣ “ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው” ተብሎ ሲጻፍ፣ የሰገደለት ቶማስ ብቻ ነበረ።

“ኢየሱስም:- ስላየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።” እምነት አስፈላጊ፣ የተባረከም መሆኑን በጕልሕ አስተማረ። እምነት የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ላይ የተመሠረተ ነው፤ ሮም 10፥17። በመቃብሩ ቦታ የታየው መልአክ ለሴቶች በሰጣቸው መልእክት፣ ኢየሱስ ስለ ራሱ በተናገራቸው ቃላት ላይ አተኰረ። ሕያው የሆነው ጌታችን ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ስለ ራሱ በተጻፉት በነቢያት ቃላት ላይ ትኵረት አድርጎ ለማመን በመዘግየታቸው ምክንያት ደቀ መዛሙርቱን ወቅሦአቸው ነበር። ይሁን እንጂ ቅዱሳት መጻሕፍትን ብቻ ሳይሆን፣ ከሙታን የተነሣውን ኢየሱስን እንዳዩ የመሰከሩትንም ስላላመኑ እንደ ወቀሣቸው ቅዱስ ማርቆስ፣ “ተነሥቶም ያዩትን ስላላመኑአቸው አለማመናቸውንና የልባቸውን ጥንካሬ ነቀፈ” ብሎ ጻፈ፤ ማር. 16፥14። ከቶማስ በቀር ሐዋርያት ሁሉ በመጀመሪያው እሑድ ማታ የተነሣውን ኢየሱስን አይተው ነበር፤ እርሱ ግን ካላየሁ አላምንም ብሎ ምስክርነታቸውንም አልተቀበለም። ኢየሱስ አሁን ነቢያት ስለ እርሱ በብሉይ ኪዳን የጻፉትን ብቻ ሳይሆን፣ ሐዋርያት የመሰከሩለትንም መቀበል እንደሚገባ ያሳያል፤ ቶማስንም፣ “ስላየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።”

እንግዲህ በትንቢታዊው ቃል ላይ የሐዋርያት ምስክርነት ተጨምሮአል፤ ከሐዋርያት በኋላ የምንኖር ሕያው የሆነውን ኢየሱስን በዚህ ጊዜ በአካላዊ ዐይናችን ማየት ባንችልም፣ የተሰጠን የነቢያት ቃልና የሐዋርያት ምስክርነት አለን፤ የእምነታችን መሠረት ይህ ነው። ከብዙ ዓመታትም በኋላ ሐዋርያው ጴጥሮስ በዘመኑ ለሚኖሩት በስደት ምክንያት ለተበተኑ ክርስቲያኖች፣ "እናንተም ለዚህ ቃል (ማለት በሐዋርያት ምስክርነት የተረጋገጠው የነቢያት ቃል) ብትጠነቀቁ መልካም ታደርጋላችሁ" አላቸው፤ 2ጴጥ. 1፥19 አ.መ.ት.።

ሐዋርያው ዮሐንስ በመግደላዊት ማርያም ታሪክ ውስጥ የሞተውን ክርስቶስን ብቻ ከምትወድ፣ ሕያው የሆነውን ክርስቶስን ወደምታምን ሴት እስከምትለወጥ ድረስ፣ የእምነትን ሙላት የሚገልጥልንን ምሳሌ እንዳገኘ ሁሉ፣ በቶማስ ታሪክም እንዲሁ ከሙታን የተነሣው ኢየሱስ ጌታና አምላክ መሆኑን ወደሚገልጽለትና ወደሚያሳየው ስግደት እስከሚመራው ድረስ ሐዋርያው እምነት የሚፈወስ ስለ መሆኑ የሚያስረዳ ሁለተኛ አስደናቂ ምሳሌ አግኝቶአል።

ዮሐንስ ስለ ቶማስ በተናገረው ታሪክ ወደ ክርስቶስ ማንነት ከሚያመለክቱት ስምንት ምልክቶች አክሊል ማለት ቁጥር ሐሳብ ደርሶአል፤ ይህም የሚመራው፣ ስለ ኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት፣ ሞትና ትንሣኤ የተሰጡአቸውን ልዩ ልዩ ማስረጃዎች የሰበሰበበትን ዐላማ ለመግለጥ ነው፤ "ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፣ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል" ብሎአል፤ 20፥31።

ይህ የኢየሱስ መታየት በዚህ ዘመን ለምንኖር እንዴት እንደሚናገር በአራት ጥያቄዎች አጠቃለን ልንመለከተው እንችላለን:-

1) በክርስቶስ ያለን እምነት እንዲፈወስ እንደ ምን ያስፈልጋል?

2) በብሉይ ኪዳን ስለ ክርስቶስ ለተጻፈው የትንቢት ቃልና በሐዋርያት ለተሰጠው የምስክርነት ቃል እንጠነቀቃለንን? እንተማመንበታለንን?

3) ሰላምን እንድናገኝ፣ ያለንን ፍርሀት፣ ጥርጣሬ ወይም ጥያቄ በሌሎች ፊት መግለጥ እንችላለን?

4) ቶማስ "ጌታዬ አምላኬም" በማለት የተናገረው ከሙታን ለተነሣው ኢየሱስ ክርስቶስ የምንሰጠው የራሳችን የዐጸፋ ምላሽ ነውን?

ለ. ጌታችን በገሊላ ሦስት ጊዜ መታየቱ

1. በባሕር ዳር ለደቀ መዛሙርት ጌታችን ለሦስተኛ ጊዜ ታየ

ሕያው የሆነው ጌታችን ኢየሱስ የታየበት ቦታ ከኢየሩሳሌም ወደ ገሊላ ይለወጣል፤ የቦታው መለወጥ አንዱ ምክንያት፣ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነው እያሉ በኢየሩሳሌም ውስጥ የነበሩት ባለሥልጣናት እንዳይጠራጠሩ ሳይሆን አልቀረም። ሆነም አልሆነም፣ ይህ በመላእክትና በጌታችን ለሴቶች ከተነገራቸው መልእክት ጋር ይስማማል፤ ማቴ. 28፥7፣10። የፋሲካና የቂጣ በዓሎች እስከሚያልፉ ድረስ፣ ደቀ መዛሙርቱ በንልጎታና ባዶ በነበረው በዮሴፍ መቃብር አካባቢ ስምንት ቀን አሳልፈዋል። አንድ ላይ ከቶማስ ጋር በተሰበሰቡበት ምሽት፣ ጌታችን ወደ ሰሜን ወደ አገራቸው (ገሊላ) እንዲመለሱ ሳያሳስባቸው አልቀረም። በኢየሩሳሌም የሚያስፈራውንና የሚያስደንቀውን ሁሉ ትተው፣ በማግስቱ ማለት ሰኞ ወደ ሰሜን ለመጓዝ ሳይነሡ አልቀሩም። ረቡዕ ቀን በገሊላ ከቤተ ሰቦቻቸው ጋር ተገናኝተው በተለመደው አገራቸው ውስጥ ተገኙ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ሌላ ተልእኮ ስላልተቀበሉ በእነርሱ መካከል ዓሣ አጥማጆች የነበሩ አንዳንዶች ዐብረው ወደ ባሕር ዳር ሄዱ። እዚያም የተከሠተውን ተአምራዊ ታሪክ በአራት ከፍለን ማየት እንችላለን:-

ሀ) በጴጥሮስ አስተሳሰብ ሰባቱ ዓሣ ለማጥመድ እንዲሄዱ ተስማምተው፣ ሌሊቱን በሙሉ ቢንቀሳቀሱም ምንም አላጠመዱም።

ለ) በመጀመሪያ ማን መሆኑን ሳያውቁ፣ ደቀ መዛሙርቱ በባሕሩ ዳርቻ ቆሞ በነበረው በጌታችን ኢየሱስ ትእዛዝ መረባቸውን ጥለው ብዙ ዓሣ አገኙ።

ሐ) መረባቸውን ጐትተው ወደ ውጭ ካወጡ በኋላ፣ ደቀ መዛሙርት በከሰል ፍም ላይ ጌታ ኢየሱስ ያዘጋጀላቸውን ቁርስ (ቁ.12 አ.መ.ት.) ዐብረውት በሉ።

መ) ከቁርስ በኋላ በከሰል ፍም ዙሪያ ተቀምጠው ንግግር ተካሄደ።

ታሪኩ በሙሉ በቅዱስ ዮሐንስ ወንጌል ም.21 ላይ ተጽፎ ይገኛል። ጌታ ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርት የታየው ለሦስተኛ ጊዜ መሆኑ ነው (ቁ.14)፤ ሐዋርያው ዮሐንስ ለደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ስለ ሆነው የኢየሱስ መታየት ይናገራል እንጂ ለጴጥሮስ ወይም ለቀለዮጳና ለጓደኛው በግል የታየ መሆኑን አያውቅም ማለት አይደለም።

አስቀድሞ እንደ ተመለከትነው ሐዋርያው ዮሐንስ ምዕራፍ 20 ላይ ወደ ወንጌሉ አክሊል ማለት ቀኑጮ ሐሳብ ደርሶ ነበር። ታዲያ ም.21ን እንደ መደምደሚያ ለምን ጨመረው? ለዚህ ቢያንስ ሦስት ምክንያቶችን ልናገኝ እንችላለን፤ እነርሱም:-

1) ጴጥሮስን ወደ ቀድሞ ቦታው ስለ መመለስ ለመዘገብ

በባሕር ዳር የተካሄደው ሁሉ፣ አስቀድሞ በሕይወቱ ስላለፉ ሁለት ዋና ዋና ወቅቶች ጴጥሮስን ማስታወስ ነበረበት፤ ቀደም ብሎ ተአምራዊ በሆነ መንገድ የብዙ ዓሣዎችን መጠመድ ባየ ጊዜ ጴጥሮስ ምን አደረገ? "በኢየሱስ ጕልበት ላይ ወድቆ:- ጌታ ሆይ፣ እኔ ኀጢአተኛ ነኝና ከእኔ ተለይ" ብሎ ነበር። ጌታችን ግን ጴጥሮስን (ስምዖንን):- "አትፍራ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ" አለው፤ ሉቃ. 5፥8፡10። በዚያን ጊዜ ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ጋር ጴጥሮስ ሁሉን ትቶ ኢየሱስን ለመከተል ወስኖ ነበር። ይህ የመጀመሪያ ወቅት የሚያስደስት ቢሆንም፣ ሁለተኛው ግን የሚያሳዝን ነው፤ ጴጥሮስ በከሰል ፍም አጠገብ ቆሞ ይሞቅ የነበረው መቼ ነው? በሊቀ ካህናቱ ግቢ ጌታውን ባሰሩት ጊዜ በወታደሮች መካከል እሳት ሲሞቅ ነበር፤ ዮሐ. 18፥18። እዚያ ቆሞ ሳለ ምን አድርጎ ነበር? ሰዎች ስለ ኢየሱስ ሲጠይቁት "አላውቀውም" በማለት ጌታውን ሦስት ጊዜ ክዶታል። ነገር ግን በሌሎች ደቀ መዛሙርት ፊት፣ "ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ ከቶ አልሰናከልም... ከአንተ ጋር መሞት እንኳ የሚያስፈልገኝ ቢሆን፣ ከቶ አልክድህም" አላለም ነበርን? ማቴ. 26፥33፡35።

አሁን በባሕር ዳር ጌታችን ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ጋር በከሰል ፍም ዙሪያ ተቀምጦአል፤ ጴጥሮስም ጭምር በእነርሱ መካከል ይገኛል።

እውነት ነው፤ ጴጥሮስ ስለ ውድቀቱ መራራ ልቅሶ አልቅሶአል፤ ልቡን የሚያውቀው ጌታ ኢየሱስ ከሙታን ሲነሣ ከልብ ዐዝኖ ያለቅስ ከነበረው ደቀ መዝሙር ጋር በግል እንደ ተገናኘ አይተናል፤ በጎይል ከሙታን የተነሣው ጌታ የወደቁትን በጎች የሚያነሣ ርኅሩኅ እረኛ ነው። አሁንም በሌሎች ሰዎች ፊት ከኢየሱስ ጋር ስለ ነበረው ግንኙነት እንዲናገር ጌታችን ለጴጥሮስ ዕድል ሰጠው። "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው።" "ትወደኛለህን?" ብሎ የግሪኩን ቃል agapao (አጋፓው) በመጠቀም፣ ጴጥሮስ ራሱን አሳልፎ እስከሚሰጥ ድረስ ኢየሱስን እንደሚወደው ጠየቀው። ጴጥሮስም፣ "አዎን ጌታ ሆይ፣ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ" ሲል መመለሱ፣ ጓደኛነትን የሚያመለክት "phileo" (ፊሌው) የተባለውን ሌላ ቃል መረጠ። የራስ መተማመንና የኵራት መንፈስ ጠፍቶአል፤ ጴጥሮስ እስከ ሞት ድረስ ጌታውን እንደሚወድ ለመናገር አልደፈረም። ለሁለተኛ ጊዜ ሲጠይቀው፣ የጌታችንና የጴጥሮስ የቃል አጠቃቀም ያው ነበረ። ለሦስተኛ ጊዜ ግን ኢየሱስ፣ "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፣ ትወደኛለህን?" ሲል ጴጥሮስ መልስ ሲሰጥ በተጠቀመበት ቃል ጥያቄ አቀረበለት። ጴጥሮስ ዐዝኖ፣ "ጌታ ሆይ፣ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንድወድህ (phileo) አንተ ታውቃለህ አለው"፤ ቁ. 17። በየጊዜው ጴጥሮስ ጌታውን እንደሚወደው በማመን፣ ኢየሱስ በሌሎች ደቀ መዛሙርት ፊት ዐዲስ ሹመት ሰጠው፤ "ግልገሎቼን አሰማራ"፤ "ጠቦቶቼን ጠብቅ"፤ "በጎቼን አሰማራ"። ለጌታው የነበረውን ፍቅር ለጌታው መንጋ በሚያደርገው አገልግሎት እንዲገልጥ ይፈልግ ነበር፤ ለሁላችንም ትልቅ ትምህርት ሊሆን ይችላል። በስብከት፣ በምስክርነትና በኋላም መልእክት በመጻፍ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ጎይል የጌታውን ትእዛዝ በጥሩ አኳኋን እንደ ፈጸመ ስናይ ያስገርማል። ይህ ክሥተት ከበዓለ ኀምሳ ቀን ጀምሮ ጴጥሮስ ወደሚፈጽመው አገልግሎት እንድንገባ ያዘጋጀናል። ይልቁንም ጌታችን ስለ ጴጥሮስ አሟሟት የጨመረው ትንቢታዊ ቃል በመጨረሻ እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ሆኖ እግዚአብሔርን እንደሚያከብረው በማሳየት፣ ምንም እንኳ በወቅቱ ቃሉን ለመቀበል ለጴጥሮስ ከባድ ቢሆንም፣ በኋላ በጣም የሚያጽናናው ቃል እንደሚሆን ልንገምት እንችላለን።

2) የተወደደው ደቀ መዝሙር (ዮሐንስ) አይሞትም የሚለውን ወሬ ከመሠራጨት ለማስቆም

ጴጥሮስ ምናልባት ስለ ራሱ ሞት መስማት ስላልወደደ፣ ዮሐንስን አስመልክቶ፣ "ጌታ ሆይ፣ ይህስ እንዴት ይሆናል?" ብሎ የኢየሱስን ሐሳብ ከእርሱ ወደ ሌላ ሰው ለማዞር የፈለገ ይመስላል። ጌታችንም:- "እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ፣ ምን አግዶህ? አንተ ተከተለኝ" ሲለው፣ ዮሐንስ አይሞትም የሚል ወሬ መስፋፋት ጀመረ። ኢየሱስ የተናገረውን አስተውሎ በመተርጐም ዮሐንስ ወሬውን ለማስቆም በዚህ ታሪክ መጨረሻ ላይ ዕድል አገኘ። እያንዳንዱ ደቀ መዝሙር በሌሎች ደቀ መዛሙርት ሕይወት ጣልቃ ሳይገባ ጌታ ኢየሱስን ለመከተል መትጋት አለበት።

3) ለሚከተለው የኢየሱስ መታየት ለመዘጋጀት ናቸው።

2. በተራራ ላይ ታላቁን ተልእኮ ለመስጠት ጌታችን ተገለጠ

ጌታችን ስለ መታየቱ በጻፈው ዝርዝር ሐሳብ ሐዋርያው ጳውሎስ ቀጥሎ ወደ አንድ ትልቅ ስብሰባ ያመራል:- "ከዚያም በኋላ ከዐምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል"፤ 1ቆሮ. 15፥6። ከተገኙት ሰዎች ብዛት አንጻር ይህ ስብሰባ ዋና ስብሰባ መሆኑን ልንገምት እንችላለን። ጌታችን ከሙታን ከተነሣበት ቀን ጀምሮ ወደ ሰማይ እስከሚያርግ ድረስ እንደዚህ ዐይነት ስብሰባ በድንገት ስለ መደረጉ አይታሰብም። በፋሲካ በዓል በኢየሩሳሌም አካባቢ መሆን አይችልም ነበር፤ ሐዋርያው ዮሐንስ በመጀመሪያ ጌታ ኢየሱስ ሦስት ጊዜ የታየበትን ሁኔታ ዘርዝሮ ይገልጣልና። ለሦስተኛ ጊዜ የታየው በገሊላ ነበረ። እንግዲህ ጌታችን ከዐምስት መቶው ጋር የተገናኘው ከፋሲካ በኋላ ምናልባትም በኢየሩሳሌም ሳይሆን በገሊላ እንደ ነበረ መረዳት እንችላለን። በኢየሩሳሌም የሚከበረው የሚቀጥለው በዓል በዓለ ኀምሳ ሲሆን፣ ጌታችን በመጨረሻ ከታየ ዐሥር ቀን በኋላ ስለሚከበር፣ ያ ጊዜ ታላቁ ስብሰባ የተደረገበት ወቅት መሆን አይችልም። እንደዚህ ዐይነት ስብሰባ በአጋጣሚ በገሊላ እንደሚደረግ ለማሰብም በይበልጥ

ይከብዳል። እንግዲህ ጌታችን ከ500 በላይ ለሚሆኑ ወንድሞች በአንድ ጊዜ የታየበት ይህ ስብሰባ ታስቦበት የተካሄደ ጉባኤ መሆን አለበት።

በተጨማሪ ይህ ጉባኤ፣ ቅዱስ ማቴዎስ ትኵረት ያደረገበት በገሊላ የተካሄደ ስብሰባ ሳይሆን አልቀረም:-

ማቴዎስ 28፥16-20

ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ግን ኢየሱስ ወዳዘዛቸው ተራራ ወደ ገሊላ ሄዱ፣ ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት የተጠራጠሩ ግን ነበሩ። ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው:- ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።

ማቴዎስ፣ ከገሊላው ስብሰባ በቀር ለወንዶች በሌላ ወቅት እንደ ታያቸው ባይጠቅስም፣ አጻጻፉ አስቀድሞ በሌላ ጊዜ ከእነርሱ ጋር እንደ ተገናኘ ያወሳል፤ "ዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ግን ኢየሱስ ወዳዘዛቸው ተራራ ወደ ገሊላ ሄዱ"፤ 28፥16። ከዚህ በፊት ማቴዎስ በመልእኩ አማካይነት፣ ደቀ መዛሙርቱ በገሊላ ወዳልተወሰነ ቦታ እንዲሄዱ የተነገራቸው መሆኑን ጽፎ ነበር። እዚህ ላይ ግን ኢየሱስ ራሱ ወደ ተወሰነ ተራራ እንዲሄዱ ያዘዛቸው መሆኑ ተጽፎአል። እውነት ነው፣ ማቴዎስ ሳይገልጥልን፣ ትእዛዙ በመልእኩ አንደበት መሰጠት ይችል ነበር፤ ጌታችን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር እንደ ተገናኘ ስለምናውቅ፣ ራሱ የሰጠው ትእዛዝ ሳይሆን አልቀረም። በገሊላ የነበሩት የሃይማኖት ባለሥልጣናትና የሄሮድስ ሰላዮች እንዳያውቁ፣ ስብሰባው የሚደረግበት ቦታና ጊዜ ባይታወቅ ይሻል ነበር። ጌታችን በገሊላ ባሕር ዳርቻ ለሰባት ዓሣ አጥማጆች የታየበት፣ ትእዛዙን ለመስጠት ምቹ ጊዜ የሆነለት ይመስላል። እነዚህ ሰባት ደቀ መዛሙርት የጉባኤ ሰብሳቢዎች ቢሆኑ ተስማሚ ነው፤ በእነርሱ መካከል ከቤተ ሳይዳ፣ ከቃና ዘገሊላና ከቅፍርናሆም ማለት ከሦስት የጌታችን አገልግሎት ማእከሎች የመጡ ይገኙ ነበርና። ወደ ልዩ ልዩ የገሊላ መንደሮች መጓዝና በእያንዳንዱ ስፍራ ያሉ ጎረቤቶቻቸውን ሳይጠራጠሩ ታማኝ የነበሩትን ምእመናን መጥራትና መሰብሰብ ቀላል አልነበረም።

ታላቁ ቀን ሲደርስ የተጠሩት በመቶ በመቶ ሆነው በተራራ ላይ ተሰብስበው ከሙታን የተነሣውን ጌታቸውን በጉጉት ይጠባበቁ ነበር። ሳይደነግጡ መንፈስ እንዳዩ እንዳያስቡ ቀስ ብሎ ከሩቅ የቀረበላቸው ይመስላል። በፊት ያዩት ሐዋርያትና ደቀ መዛሙርት ሲሰግዱለት፣ በሌሎች ደቀ መዛሙርት መካከል ኢየሱስ መሆኑን የሚጠራጠሩ ነበሩ። በ500 ሰዎች መካከል ልዩ ልዩ ባሕርይና የእምነት ደረጃ ያላቸው ሰዎች ቢኖሩ አያስገርምም፤ ሐዋርያት ራሳቸው በመጀመሪያ በፍርሀት፣ በኋላ ደግሞ በደስታ ተውጠው አልተጠራጠሩም ነበርን? በዚህ ስብሰባ ላይ በሐዋርያት መካከል ገና የሚጠራጠሩ ሰዎች መኖራቸውን ማቴዎስ መናገር የሚፈልግ አይመስልም፤ የእነርሱ ጥርጣሬዎች በኢየሩሳሌም በነበሩ ጊዜ ተወግደው ነበርና፤ ኢየሱስ ሲታያቸው ማቴዎስ ራሱ ሁለት ጊዜ ዐብሮ ተገኝቶአል።

በኢየሩሳሌም ለሐዋርያት የሰጣቸውን ተልእኮ በገሊላው ስብሰባ በሌላ ሰፊ አነጋገር ደገመው። በሰማይና በምድር ሥልጣን ሁሉ እንደ ተሰጠው ነገራቸው። በዚህ ሥልጣን መሠረት አስቀድመው ዐሥራ አንዱ ሄደው ከአሕዛብ ሁሉ ደቀ መዛሙርት እንዲያደርጉ አዘዛቸው። ጌታችን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስለሚኖረው አንድነት አሳስቦ "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ (አንድ አምላክ) ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" በማለት ተልእኮውን አብራራላቸው። የክርስቲያን እንቅስቃሴ ጎይል ጌታችን ባደገበት በገሊላ ስለ ነበረ፣ ጌታችን የተበተነውን መንፈሳዊ ሰራዊት እዚያ ለመሰብሰብ ወሰኖ ነበር። ጌታችን ስብሰባውን በገሊላ ያዘጋጀበት ሁለተኛ ምክንያት፣ በሐዋርያት መካከል አንዳንዶች እንዳሰቡት፣ ጌታችን በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም እስራኤልን ከሮም መንግሥት ነጻ ለማውጣት የፖለቲካን (ምድራዊ) መንግሥት ለማቋቋም ዐቅዶአል የሚለውን ሐሳብ ለማስቆም ነበረ። ከዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር በገሊላ የሚኖሩና የሚያገለግሉ ምእመናን በዓለም ዐቀፍ ደረጃ የምትቋቋመዋ ቤተ ክርስቲያን "ግንባር ቀደም ጦር" ይሆናሉ። ከሃያ ዐምስት ዓመት በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ ከእነዚህ ምስክሮች አብዛኞች ገና በሕይወት እንዳሉ በማወቁ፣ በአብያተ ክርስቲያናት የታወቁና የጸኑ አባሎች እንደ ነበሩ ያሳያል።

ቅዱስ ማቴዎስ ወደ ወንጌሉ አክሊል ማለት ቍንጮ ሐሳብ ወደ ታላቁ ተልእኮ ሲቃረብ፣ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ ሁለት ከሥተቶችን ብቻ እንደ ጠቀሰ እንገነዘባለን፤ እነርሱም፣ የሴቶች ምስክርነትና የአይሁድ ባለሥልጣናት ያዘጋጁት ሐሰተኛ ምስክር መገለጥ ናቸው። የማቴዎስ ዋና ትኵረት፣ ምስክሮች ደካሞች፣ የተናቁ ወይም በመጠኑ ግራ የገባቸው ቢሆኑም፣ ሕያው የሆነው ጌታችን ኢየሱስ የወንጌልን ትክክለኛ መታወጅ የሚደግፍና ሁልጊዜ በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ ላይ ነው፤ "እነሆም ኢየሱስ አገኛቸውና..."፤ ማቴ. 28፥9። "እንግዲህ ሂዱ" የሚለውን ዐዋጅ ለማስፋፋት ከሚታዘዙ ተከታዮች ጋር የሚሄደው ሕያው የሆነው ኢየሱስ ራሱ ነው፤ "እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" ብሎ ቤተ ክርስቲያኑን ይመሠርት ዘንድ ባለው ሙሉ ሥልጣን የተሰፋ ቃሉን ሰጥቶአቸዋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ተልእኮ በዚህ ዘመን ወደምንኖር ተከታዮቹ ደርሶአል፤ የተልእኮው ዐላማ፣ ለጌታችን የሚታዘዙትን ምእመናን ደቀ መዛሙርት ማድረግ እንጂ በጎ ፈቃደኞችን ማሳመን አይደለም። የሚያምኑት ወደ ደቀ መዝሙርነት እንዲደርሱ ጥምቀት ብቻ ሳይሆን፣ ተከታታይ የሆነ ሰፊ የወንጌል ትምህርት ያስፈልጋል፤ የክርስቶስን በጎች፣ ጠቦቶችና ግልገሎች የመመገብ ግዴታ መኖሩን ማወቅ እጅግ አስፈላጊ ነው። "የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለሁና፣ ምንም አላስቀረሁባችሁም" ብሎአል ሐዋርያው ጳውሎስ ከኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተሰናበተ ጊዜ፤ ሐ.ሥ. 20፥27። አርአያነቱን ብንከተል፣ ወደፊት ለሚነሣው ትውልድ ከፍ ያለ አገልግሎትን እንሰጣለን።

3. ለሐዋርያው ያዕቆብ ታየ

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ... ታየ" ብሎ ሕያው ስለ ሆነው ክርስቶስ የጻፈውን ዝርዝር ሐሳብ መግለጥ ይቀጥላል። ይህ ያዕቆብ የተባለው ሰው ከዐሥራ ሁለቱ አንዱ የነበረ አይመስልም፤ የዘብዴዎስ ልጅ የሐዋርያው ዮሐንስ ወንድም የተባለው ያዕቆብ በ34 ዓ.ም. በንጉሥ ሄሮድስ ተገድሎ ነበር፤ ስለ ቀለዮጳና ስለ

ሁለተኛዱቱ ማርያም ልጅ ስለ ያዕቆብ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሌላ የሚታወቅ የለም። ሐዋርያው ጴጥሮስ ከታሰረ በኋላ ግን የ"ጌታ ወንድም" ያዕቆብ በኢየሩሳሌም የነበረች ቤተ ክርስቲያን መሪ ስለ ሆነ፣ ጌታችን ኢየሱስ የተገለጠለት ያዕቆብ እርሱ እንደ ሆነ ይታሰባል። በሕግና በእምነት መካከል ለተነሣው ክርክር መፍትሔ ለማስገኘት የተሰበሰበው ጉባኤ ሊቀ መንበር ይህኛው ያዕቆብ ነበረ፤ በገላትያ መልእክትም ሐዋርያው ጳውሎስ ያዕቆብን፣ ኬፋን (ጴጥሮስ)፣ ዮሐንስንም "እንደ አዕማድ የሚቈጠሩት" ይላቸዋል፤ ገላ. 2፥9 አ.መ.ት.። አስቀድሞ ከቤተ ሰባዊ ግንኙነት አኳያ፣ ከኢየሱስ ጋር አንድ ላይ ያደገ ሲሆን፣ እንደ ሌሎቹ የጌታችን ወንድሞች በኢየሱስ ማንነትና ተልእኮ አላመነም ነበር፤ ዮሐ. 7፥5። ቄይቶ ግን ወንድሙ ኢየሱስ የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ መሆኑን ማመኑ ሕይወቱን ሁሉ የሚለውጥ እንደ ምድር መናወጥ የሚቈጠር መሆን ነበረበት።

አስቀድሞ ለጴጥሮስ እንደ ታየው ጌታችን ለያዕቆብ ሲታየው፣ በግል የታየው እንደ ሆነ ልናስብ እንችላለን። ይህም የተፈጸመው፣ ጌታችን ከ500 ወንድሞች ጋር ከተገናኘ በኋላና ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ነበረ። በሚቀጥለው ጊዜ የገሊላ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም የሚመጡበት ምክንያት፣ ከዕርገቱ ዐሥር ቀን በኋላ በዓለ ኀምሳን ለማክበር ስለ ሆነ፣ ጌታችን ለያዕቆብ የታየው በአገራቸው በገሊላ ሳይሆን አልቀረም። ሳያምንበት ለብዙ ዓመታት በኢየሱስ አጠገብ መኖሩን በሐዘን ሲያስቡት፣ ያዕቆብ የተሰማውን ኀፍረት መገመት እንችላለን። ጌታችን ይቅር አለውና በኋላ ለሚሰጠው የዐደራ ኀላፊነት አዘጋጀው። አስቀድመው ኢየሱስን የነቀፉት ወንድሞቹ ሁሉ መንፈስ ቅዱስን እየተጠባበቁ ከሐዋርያት ጋር በአንድነት ሲጸልዩ እናገኛቸዋለን። ከብዙ ዓመታት በኋላ በመልእክቱ ስለ ራሱ የጻፈው "የእግዚአብሔርና የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ያዕቆብ" የሚለው ሐረግ በውስጡ የተደረገው ለውጥ ምን ያህል ታላቅና መሠረታዊ መሆኑን ያረጋግጣል።

ጌታችን ለያዕቆብ መታየቱ ምን ሊያስተምረን ይችላል? ምናልባት አንዳንዶቻችን ለረጅም ጊዜ ሳናምን ለወንጌል ቅርብ ሆነን ኖረናል፤ በቤተ ሰባችን ውስጥ አንድ ጌታችንን የሚከተል ሰው አለ፤ ምንም

እንኳ እምነቱ ሕያውና ትክክል ቢሆንም፣ መስማት አንፈልግም። አሁን ጊዜው ዐልፎአል? ገና ንስሓ መግባት እንችላለንን? ከሐዋርያው ያዕቆብ ተመክሮ ዐዲስ ተስፋ እናገኛለን፤ ጌታችን በጸጋ ወደ እኛ ቀርቦ፣ ከአንደበቱ ይቅርታ የሚለውን ሰው ቃል ሲሰማ መረዳት እንችላለን፤ ይልቁንም ለዐዲሱ ኀላፊነት ወይም ሹመት እንዲያዘጋጀንና እንዲዳስሰን በእኛ ላይ እጁን መጫን ይችላል። እንደ ሐዋርያው ጴጥሮስ፣ እንደ ሐዋርያው ያዕቆብም ሁሉ በንስሓ በጌታችን ኢየሱስ እግር ሥር ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ሰው ዛሬም እንኳ ለእግዚአብሔር ታላቅ ጸጋ ሕያው የሆነ ሐውልት ሊሆን ይችላል።

የክርስቶስ ትንሣኤ ታሪክ በሰው ሕይወት ውስጥ እግዚአብሔር ጣልቃ ከገባባቸው ታሪኮች ሁሉ ይልቅ እጅግ የሚያስደንቅ ነው። ሊቀበሉት እንዲችሉ ለምእመናን ቀስ በቀስ የተሰጠ መገለጥ ነበረ። ምእመናት ሴቶች ከወንዶች በፊት የትንሣኤውን መልእክት ለመቀበል ዝግጁዎች ነበሩ። እነዚህ ሴቶች መጀመሪያ የተከፈተ መቃብር፣ በኋላ ባዶ የሆነ መቃብር፣ ቀጥሎም መላእክትን በራእይ አዩ። የሚከተለው የመላእክት መልእክት ነበረ፤ በመጨረሻ ጌታችን ኢየሱስ ራሱ ለአንዲት ሴት፣ በኋላም ለሌሎች ሴቶች ታይቶ ተናገረ። ከዚህ ሁሉ በኋላ ለወንዶች በተከታታይ እያደጉ የሚሄዱ መገለጫዎችን ተቀበሉ። መጀመሪያ ሴቶች የሚተርኩትን ታሪክ ሰሙ፤ ከእነርሱ አንዳንዶች ባዶ የነበረውን መቃብር አዩና የተልባ እግር ልብሱን አቀማመጥ ተመለከቱ። ቀጥሎም ጌታችን ኢየሱስ ራሱ ወደ ኤማሁስ ይጓዙ ወደ ነበሩ ደቀ መዛሙርት ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ዐብሮ ሄደ። የሕማማትን ትርጕም ይገልጥላቸው ጀመር። ለረጅም ጊዜ ማንነቱን ሲደብቅ ቈይቶ፣ በመጨረሻ ለጥቂት ጊዜ ራሱን ገለጠላቸው፤ ወዲያውም ከእነርሱ ተሰወረ። ይህ ጊዜ መሪ የሚሆኑትን ምስክሮች ለመሾም የዝግጅት ጊዜ ነበረ፤ ምስክሮችም፣ ጴጥሮስ፣ ዐሥራ አንዱ፣ ቶማስ፣ 500 ወንድሞች በመጨረሻም አንድ ቀን የኢየሩሳሌምን ቤተ ክርስቲያን እንዲመራ የሚሾመው የጌታችን ወንድም ያዕቆብ ነበሩ።

እንግዲህ በገሊላ ሦስት ጊዜ በመታየት ከሙታን የተነሣው ጌታችን ኢየሱስ፣

- በባሕር ዳር አገልግሎቱን እንደ ገና አጠናከረ፣
- በተራራ ላይ የተበተኑትን ምእመናን ሰበሰበ፣
- ከወንድሙ ከያዕቆብ ጋር በመገናኘት ቤተ ሰቡን ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ አደረገ።

"ኢየሱስ ደጋግሞ የታየበት ምክንያት፣ ለደቀ መዛሙርቱ የትንሣኤውን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን፣ የማይታይ ቢሆንም በእውነት ዐብሯቸው የሚኖር ወዳጅ በሆነው በመተማመን እንዲኖሩ ለማዘጋጀት ነው።"[13]

ከመሞቱ ጥቂት ጊዜ በፊት ጌታችን ኢየሱስ፣ "ልጅህ ያከብርህ ዘንድ አክብረው" ብሎ ጸልዮ ነበር። እግዚአብሔር አብ የተወደደውን ልጅ ከሙታን ሲያስነሣው፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳከበረው ግልጽ ነው። ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ወደ ክብሩ እንዲገባ ሌላ ርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ በሚከተለው ምዕራፍ እንመለከታለን።

[13] "Man Alive" Michael Green, IVP, 1967 ገጽ 49።

ምዕራፍ 6

የትንሣኤ ክርስቶስን ትክክለኛነት የሚያረጋግጡ ተጨማሪ ምስክሮች

ክርስቶስ ከሙታን እንደ ተነሣ የተሰጡንን ማስረጃዎች ስንፈልግ፣ እስካሁን ድረስ ወደ ሁለት አቅጣጫዎች ተመልክተናል፤ እነርሱም፣ ጌታችን የተቀበረበት መቃብርና ሕያው የሆነውን እርሱን ያዩት የዐይን ምስክሮች ናቸው። በመቃብሩ ውስጥ ካየነውና ከምስክሮቹ አንደበት ከሰማነው በተጨማሪ የትንሣኤ ክርስቶስን ርግጠኛነት የሚያመለክቱ ሌሎቹ ነገሮች መኖራቸውን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንመለከታለን።

ሀ. ክርስቶስ ወደ ክብሩ መግባቱ

በተከታታይ ክርስቶስ መታየቱን ዘርዝሮ የገለጸው ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ከገሊላ ስብሰባ በፊት ጌታችን ለዐሥራ ሁለቱ፣ ከስብሰባው በኋላ ደግሞ ለያዕቆብ "ኋላም ለሐዋርያት ሁሉ ታየ" ብሎአል፤ 1ቆሮ. 15፥7። ከምድር ከመሄዱ በፊት ጌታችን በመጨረሻ የታየው በገሊላ ሳይሆን በኢየሩሳሌም አካባቢ ለዐሥራ አንዱ ሐዋርያት ብቻ መሆኑን ተረድተናል። የእንደዚህ ዐይነቱ ታላቅ ክሥተት እውነተኛነት ሁነኛ በሆኑ የዐይን ምስክሮች እንዲረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነበረ።

ከገሊላ ስብሰባ በኋላ ዐሥራ አንዱ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ ከትንሣኤው ቀን ጀምሮ እስከ ዐርባ ቀን ድረስ ጌታችን ኢየሱስ፣ "እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው፣ በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው"፤ ሐ.ሥ. 1፥3። ሐዋርያው ጳውሎስም በጲስድያ ውስጥ በነበረው አንጾኪያ በሰበከ ጊዜ፣ "እግዚአብሔር ግን (ክርስቶስን) ከሙታን አስነሣው በሕዝብም ዘንድ ምስክሮች ለሆኑት ከእርሱ ጋር ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ለወጡት ብዙ ቀን ታያቸው" ብሎአል፤ ሐ.ሥ. 13፥30-31። በቅዱስ ሉቃስ የተጠቀሰው የሐዋርያው ጳውሎስ ስብከት ሉቃስ ራሱ አስቀድሞ የጻፈውን እንደሚደግፍ ይታያል።

የቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ም.16፥15-20 ወደ ሰማይ ከማረጉ ጥቂት ጊዜ በፊት የጌታችን ትምህርት አንድ ክፍል ሊሆን ይችላል፤